ምዕራፍ ፪

"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው?

ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ።

ጥያቄ፦ *"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው?*

መልስ፦ ይህን ጥያቄ፡ ማናቸውም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚል፡ ሰው፡ ሊጠይቀው የሚገባ፡ ቀዳሚ ጉዳይ ነው። አዎን! እንኳንስ፡ የእኹኑን በመሰለ፡ ቀውጢ ሰዓት ይቅርና፡ በማናቸውም ጊዜ ቢኾን÷ በተለይም፡ ዛሬ ያለው፡ ሕፃኑና ወጣቱ፡ እውነተኛ መልሱን አግኝቶ እስኪረካ ድረስ፡ ሊጠይቀው የሚገባ ጥያቄ ነው። ባገኘውም እውነተኛ መልስ ተደራጅቶና ተሟልቶ፡ የተረከበውን ነጻ የህልውና ቅርሱን፡ በንቃትና በትጋት ለመጠበቅ፡ ቊርጥ ውሳኔን የሚሰጥበት፡ <u>የመኖር ወይም የአለመኖር</u> ታሳቅ ቁም ነገር ነው። "በተለይ፡ ሕፃናቱና ወጣቶቹ ሊጠይቁት የሚገባ ጥያቄ ነው!" ያልሁት፡ ያለምክንያት አይደለም፤ "ኢትዮጵያ" የተሰኘች አገራቸውን÷ "ኢትዮጵያዊ" የተሰኘ ማንነታቸውንም፡ ከነጻነት ህልውናቸው ጋር ተረክበው፡ በመልካም ሕይወት እንዲቀጥል የሚያደርጉ፡ እነርሱ በመኾናቸው ነው። መቼም፡ እነርሱም፡ ከኢትዮጵያውያን ወላጆቻቸው ስለተወለዱ፡ የ"ኢትዮጵያዊነቱ" ስሜት ተቀርፆባቸዋልና፡ ሳይታወቃቸው፡ በውስጣቸው በሚሰማቸው፡ በዚሁ "ኢትዮጵያዊ ምንነት" ግራ በመጋባት÷ ካለማወቅም የተነሣ፡ ይህን ጥያቄ፡ ለጊዜው፡ ከአንደበታቸው አውጥተው ባይጠይቁትም፡ በእየኅሊናቸው፡ የሚያወጡትና የሚያወርዱት ዋና ጥያቄ መኾኑ አይጠረጠርም። በእነርሱ ብቻ ሳይኾን፡ በወላጆቻቸውና በኹሉም ኢትዮጵያውያን አዋቂዎችና አዛውንት፡ በወንዶቹም፡ በሴቶቹም ዘንድ፡ ሊጠየቅና መልስ ሊያገኝ የሚገባው አሳሳቢና አስቸኳይ ጉዳይ መኾኑን፡ አስተዋይ ተመልካች ይገነዘበዋል።

ታዲያ! እናንተ፡ በመሠረቱ፡ ይህን ጥያቄ፡ ሳትፈሩ፡ እንዲህ፡ ለእኔ ለማቅረብ፡ ድፍረቱን፡ እንዴት አገኛችሁ? አደንቃችኋለሁ። የአድናቆቴም ምክንያት፡ ለዚህ ጥያቄ፡ መልስ የመስጠቱን ከባድ ተግባር ትተን፡ ራሱን ጥያቄውን ለማቅረብ የሚቃጣ ግለሰብ መኖሩን መስማቱ እንኳ፡ ብርቅ በኾነበት ዘመን የምንኖር በመኾናችን ነው። ጥያቄውን፡ እንዲህ፡ ዕርቃኑን፡ በቀጥታ ማቅረቡን፡ ለጊዜው ወደጎን አድርገን፡ በመሠረቱ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ <u>ስለ'ኢትዮጵያዊነት'፡ እውነቱን ለማወቅ፡ ከልቡ ፈልጎ፡ "'ኢትዮጵያዊነት' ምንድር ነው?" ብሎ፡ ሳይፈራ፡ በይፋ ቀርቶ፡ በግል፡ የሚጠይቅ አለወይ?"</u> የሚለውን፡ ሌላውን፡ የቀለለውን ጥያቄ እንኳ፡ አስቀድመን ብንመለከት፡ አጥጋቢውን መልስ ለመስጠት፡ በራሴ በኩል፡ አስቸጋሪ ኾኖ አገኘዋለሁ።

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት
"'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?"

በእርግጥ፡ በእኔ በኩል፡ ይኸው አኹን፡ እናንተን እስካገኘሁ ድረስ፡ "ይኖራል" ብዬ፡ አፈን ሞልቼ መናገር አዳግቶኝ ቆይቷል፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ከሚለው ዜጋ መካከል እንኳ፡ ቁጥሩን፡ በትንሹም ቢኾን፡ ገምቼ ላውፍር ይከብደኛል፡ እስከመኖሩም፡ እንድጠራጠር ወዳስገደደኝ ደረጃ ማዘቅዘቁን ስገልጽ፡ ትካዜ ይመጣብኛል።

ይህንም ስል፡ ጥንት፡ በብሉዩ፡ የነቢዩ ኤልያስ ዘመን ደርሶ ስለነበረ፡ ተመሳሳይ ኹኔታ፡ ተጽፎ የሚነበበውን የመጽሐፍ ቃል ባለመዘንጋት ነው። ይኸውም፡ ኤልያስ፡ ሊገድሉት ከሚሹ፡ የእግዚአብሔር ተቃዋሚዎች ይድን ዘንድ፡ አምላኩ ወዳዘጋጀለት የኮሬብ ተራራ፡ አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት በጾም ተገሣ ከደረሰ በኋላ፡ በዚያ ባነበረ፡ አንድ ዋሻ ውስጥ አድሮ ሣለ፡ "*ኤልያስ ሆይ! በዚህ ምን ታደርጋለህ?*' የሚል፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደአርሱ መጣ። እርሱም፡ '*የእስራኤል ልጆች፡ ቃል ኪዳንህን ትተዋልና፡ መሠዊያዎችህንም አፍርሰዋልና፡ ነቢያትህንም በሠይፍ ገድለዋልና፡ ለሠራዊት አምላክ፡ ለእግዚአብሔር፡ እጅግ ቀንቻለሁ፡ እኔም፡ ብቻዬን ቀርቻለሁ፡ ነፍሴንም፡ ሊወስዷት ይሻሉ!*' አለ።"

"እግዚአብሔርም፡" ኤልያስ ሊያደርግ የሚገባውን ትእዛዝ ከሰጠው በኋላ፡ እንዲህ "*አለው፡- 'ከእስራኤል ሕዝብ መካከል፡ ገላቢታቸውን፡ በሓል ለተባለው ጣዖት ያላንበረከኩትን ኹሉ፡ በአፋቸውም ያልሳሙትን ኹሉ፡ ሰባት ሽህ ሰዎችን፡ ለእኔ አስቀራለሁ!*'" የሚለው ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም፡ ይህንኑ የብሉዩን ቃል ከጠቀሰ በኋላ፡ "*እንደዚሁም፡ በአኹኑ ዘመን ደግሞ፡ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ።*"[፲፮] ብሏል። ስለዚህ፡ "ስለኢትዮጵያዊነት" ለማወቅ ያህል እንኳ፡ ደፍሮ የሚጠይቅ ጐበዝ ስለመኖሩ እስከመጠራጠር መድረሴን የሚገልጽ አስተያየቴን፡ ከላይ የሠነዘርሁት፡ እኔ የማላውቃቸው፡ ነገር ግን፡ እግዚአብሔር ብቻ የሚያውቃቸው፡ ብዙዎች "እውነተኞች ኢትዮጵያውያን" እንደሚኖሩ በማመን መኾኑን ላሳስባችሁ እወድዳለሁ።

ደግሞም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ሳይቀር፡ በፍርሃትና ጊዜውን በመምሰል፡ በሌላ ሌላም ሰበብ አስባብ፡ ሊጠይቀው የማይደፍረውን፡ ዛሬ፡ እናንተ የጠየቃችሁትን፡ ይህን ጥያቄ እኮ፡ ነገ፡ በይበልጥ፡ በአገር ያሉት ልጆቻችሁና የልጅ ልጆቻችሁ፡ በተለይም በልዩ ልዩ ምክንያት፡ ከአገር ወጥተው፡ በባዕዳን አህጉር የሚኖሩት፡ በዚያ የተወለዱትና ወደፊት ተወልደው የሚያድጉት፡ መጠየቃቸው እንደማይቀር፡ የተረጋገጠ ነው፡ አምን! እነዚህ ልጆች፡ ነፍስ ሲያውቁ፡ በአገራቸው፡ በኢትዮጵያም ኾነ፡ በየትኛውም ክፍለ ሀገር፡ ወይም፡ ክፍለ ዓለም፡ የተለያየ፡ የዘርና የነገድ፡ የብሔርና የጐሣ ወገን በሚርመሰመስበት፡ ዘረኝነትና ጐሠኝነትም በተጠናወተው ጎብረተሰብ መካከል ተከብበው፡ ራሳቸውን ስለሚያገኙ፡ <u>የእየራሳቸውን ማንነት፡ ከእነዚያ ወገኖች ለይተው ለማወቅ፡ እያንዳንዳቸው፡ "እኔ ምንድር ነኝ?" ብለው እንደሚጠይቁ የታመነ ነው፤ በዚህ ጊዜ፡ እናንተ፡ ያለጥርጥር፡ "ኢትዮጵያዊ ነህ!" ወይም፡ "ኢትዮጵያዊት ነሽ!" ብላችሁ፡ ለጊዜው፡ ቀላል የሚመስለውን መልስ፡ ለጠያቂ ልጃችሁ፡ ወይም የልጅ ልጃችሁ ትሰጣላችሁ።</u>

ምዕራፍ ፪፡
“ኢትዮጵያዊነት” ምንድር ነው?
ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ።።

ጉዱ፡ ከዚህ የሚቀጥለው ጥያቄያቸው ነው፤ መቼም፡ የዛሬ ልጆች፡ ኹሉን ለማወቅ የሚፈልጉ፡ ብርቱ ጠያቂዎች ናቸውና፡ ታዲያ፡ “ኢትዮጵያዊነት ምንድር ነው?” ብለው አከታትለው ይጠይቃሉ።። ዐጥያቄያቸው፡ የማይለቁና የማይሰለቹ፥ አፋጥጠው የሚይዙና ዕረፍት የማይሰጡ ስለኾነ፡ ፍጹም የሚያረካቸውን፡ እውነተኛውን መልስ እስኪያገኙ ድረስ፡ ጥያቄያቸውን፡ እንዲህ፡ እንዲህ እያሉ ይቀጥላሉ።።

እናንተ፡ ለዚህ ዋና ጥያቄ የምትሰጡት መልስ፡ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ይኾናል፤ ምክንያቱም፡ የማንነትና የምንነት፡ ማለትም፡ የዘለዓለም ህልውናን የሚመለከት፡ የሕይወት ወይም የሞት ጉዳይ ስለኾነ፡ በፍጹም እውነት ላይ የተመሠረተ፡ ትክክለኛ መኾን ይኖርበታልና ነው።።

አለዚያ፡ ያልኾነውን፡ “ነው” ብሎ፡ በማስመሰል የተቀነባበረውን፥ ወይም፡ ሰዎች ላሉበት ኹኔታ፡ እንደሚስማማቸው አድርገው፡ በራሳቸው የፈለሰፉትን፡ ወይም፡ ሰው-ሠራሽ ወይም ዘመን-አመጣሽ ኾኖ፡ ጊዜ የፈጠረውን፡ ወይም፡ ሓሰተኛውን፥ ወይም፡ “አላውቅም!” ብላቸው፡ “ልጆቼ ምን ይሉኛል?” በሚል የጎሊና ነውጥ፡ ስሜት አስገድዷችሁ፡ ድንገት፡ ከአእምሮአችሁ ያፈለቃችሁትን፥ ወይም በቀልድና በተረት፥ በልብ ወለድና በመላምት መልክ፡ የሚነገረውን፡ የ“ኢትዮጵያዊነት” ነገር ብትንግሩዋቸው፡ በወደፊት ሕይወታቸው ላይ የሚያስከትለው ጉዳት፡ ጠንቁ፡ ምንጊዜም ሊወገድ የማይችል ባለመኾኑ፡ በዚህ ረገድ፡ “የምትሰጧቸው መልስ፡ ብርቱ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ይኾናል!” ያልኋችሁ፡ ስለዚህ ነው።። “ኢትዮጵያዊነት፡ ይህ ነው!” ብላችሁ፡ በእርግጠኛነት የምትሰጧቸው መልስ፡ እውነተኛና ትክክለኛ መኾን አለበት።።

“ኢትዮጵያዊነት”፡ ወደፊት እንደምትገነዘቡት፡ በእግዚአብሔር የተሠራ በመኾኑ፡ በሰብአዊ ፍላጎት ሊለዋወጥ የማይቻል፥ እውነተኛው ሕይወት የሚኖርበትና ተገቢው አገልግሎት የሚሰጥበት ህልውና ነው።። ስለዚህ፡ በዚህ ረገድ፡ ለአጠቃላዩ ጎብረተሰብ ከምታበረክቱት የአስተዋጽዖ ግዳጃችሁ ጋር፡ በተለይ፡ በወላጅነታችሁ፡ ልጆቻችሁና የልጅ ልጆቻችሁ፡ ስለ“ኢትዮጵያዊነት”፡ እውነቱንና ትክክሉን እንዲያውቁ የማድረግ ኀላፊነት አለባችሁ።። እውነተኛውንና ትክክለኛውን “ኢትዮጵያዊነት” በማሳወቁ ረገድ፡ ከአባቶቻችሁና ከእናቶቻችሁ የተረከባችሁት የኢትዮጵያዊነት ግዳጅ፡ ለተወለዱትና በኀላፊነት ለምትጠየቁባቸው ልጆቻችሁ ብቻ አይደለም፡ “ኢትዮጵያዊ ነኝ!” ለሚለውም ኾነ፡ ለማይለው ኹሉ ጭምር ነው እንጂ።። በዚህ ረገድ፡ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሕፃን፡ ወላጅ አባትና እናት፥ አሳዳጊም፡ ኹላችንም፡ ዛሬ፡ በአየኀሊናችን፥ ነገም፡ በእየወገናችን፥ በመጨረሻው ጊዜ ግን፡ ላበረከትነው የተግባራችን ትርፍ፡ ዋጋን፥ ወይም፡ ላደረስነው የጥፋት በደል፡ ፍዳን በሚያስረክበን፡ በባለመክሊቱ ፈጣሪያችንና አምላካችን ዘንድ፡ የምንጠየቅበት መኾኑን፡ በብርቱ ልትገነዘቡት ይገባል።።

ዛሬ፡ እናንተ የጠየቃችሁትና ነገ፡ ልጆቻችሁና የልጅ ልጆቻችሁ የሚጠይቁት÷ እኔም፡ እነሆ፡ መልሱን የምሰጣችሁ፡ ይህ፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ጥያቄ፡ በአያሌ ሺህ ዓመታቱ የፈተና እሳት ጠርቶና በመከራ ማዕበሎቱ ተንገላትቶ፡ ከመሠረቱ ሳይናወጽ፡ በህልውናው ጸንቶ፡ ለዛሬዪቱ ቀን፡ ስለበቃው÷ እግዚአብሔር አምላክ፡ ከፈጠረው፡ ከመጀመሪያው ሰው ጋር ስለሠራው÷ ስለእውነተኛውና ትክክለኛው "ኢትዮጵያዊነት" መኾኑን እንድታውቁት እፈልጋለሁ፡፡ ይህንም፡ በዚህ ውይይታችን ውስጥ፡ በሰፊው ተብራርቶ ታገኙታላችሁ፡፡

ከዚህ ጋር፡ እንድታውቁትና እንድትገነዘቡት÷ እንድታስተውሉትም የምፈልገው፡ ሌላ፡ ዋና ቁም ነገር አለ፡፡ ይኸውም፡ የዚህ ውይይታችን መልእክት፡ አቀራረቡ የተመቸ እንዲኾን በማሰብ፡ በጥያቄና መልስ ሥርዓት ይዘጋጅ እንጂ÷ ደግሞም፡ በውይይታችን ውስጥ፡ የተገለጹትን ጥያቄዎችና መልሶች የምንለዋወጠው፡ "እናንተ" እና "እኔ" የምንባባለው፡ እኛ፡ ሦስት ሰዎች መስለን እንታይ እንጂ፡ ***<u>ጠያቂዎቹ፡ እናንተ÷ መላሹም፡ እኔ ባልኾን፡ ጠያቂውም፡ መላሹም፡ አንተና አንቺ፡ እያንዳንዳችሁ፡ "እኔ" የምትሉት እየራሳችሁ መኾኑን፡</u>*** ካሁኑ፡ ልታውቁትና ልትገነዘቡት ይገባችኋል፡፡ ይህም ማለት፡ ምናልባት፡ ከውይይታችን ውጭ በምንኾንበት ጊዜ፡ አንድ፡ ጥያቄ፡ በእየኅሊናችሁ ውስጥ ቢነሣ÷ ያም ጥያቄ፡ በውይይታችን ላይ ያልተወሳ ቢኾን፡ ጥያቄውን፡ እዚያው፡ እናንተው ራሳችሁ፡ እየራሳችሁን ጠይቃችሁ፡ መልሱን፡ እዚያው፡ እናንተው ራሳችሁ፡ ልታገኙት የሚቻላችሁ መኾናችሁን ታውቃላችሁ÷ ትገነዘባላችሁም ማለት ነው፡፡ የዚህም ማጠቃለያው፡ እየራሳችሁን፡ በእየራሳችሁ ለማወቅ፡ ከውጫችሁ፡ ሌላ ሰው መጥቶ፡ "አንተ/አንቺ እኮ፡ 'እንዲህ፡ እንዲህ' ያለህ/ያለሽ ነገር ነህ/ነሽ!" ብሎ፡ ስለእናንተነታችሁ ሊነግራችሁ የማያስፈልግ መኾኑን ተረድታችሁ፡ እየራሳችሁን፡ በእየራሳችሁ፡ ወደማወቁ÷ ከዚያ፡ እግዚአብሔርን ወደማወቁ÷ በመጨረሻ፡ የተፈጥሮ ባልንጀራችሁ የኾነውን፡ ሌላውን ሰው ወደማወቁ ብቅዓት ትደርሳላችሁ ማለት ይኾናል፡፡ በዚህ ጊዜ፡ *"'እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን÷ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!" ይላል እግዚአብሔር::"* የሚለው፡ የነቢዩ ቃል፡ በእናንተ ይፈጸማል፡፡[፩፭]

ጥያቄው፡ ለምን እንደሚያስፈራና እንደማይፈለግ!

ጥያቄ፡- *የዛሬው ትውልድ÷ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ሳይቀር፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ጥያቄን፡ ማንሣት የሚፈራው፡ ለምንድር ነው?*

መልስ፡- የሚፈራው፡ ሌላውን ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ ራሱን ጭምር ነው፡፡ ለምን? ቢባል፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት"፡ እውነቱን ያወቀ እንደኾን፡ በዚያች "እውነት" ምክንያት፡ በራሱ ውስጥ፡ ችግር እንደሚፈጠር ያውቃል! አዎን! ያች እውነት፡ በኅሊናው ውስጥ፡ ሁከትን ትቀሰቅስበታለች፡፡

ምዕራፍ ፪፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ ጥያቄው፡ ለምን እንደሚያስፈራና እንደማይፈለግ!

ስለዚህ፡ በልቦናው ውስጥ ተዳፍኖ ያለው ኢትዮጵያዊ መንፈሱ፡ ይህ ሊደርስ እንደሚችል አስቀድሞ፡ ለጎሊናው ስለሚነግረው፡ ጥያቄ፦ን የማንሣቱን ነገር፡ ገና ሲያስበው፡ በባዕዳን አስተሳሰብ የተቀረፀው ሥጋዊ አእምሮው ይበረግጋል፤ ሥጋት ያድርበትና፡ ዝም ይላል፤ ከቅርብ ምሥጢረኛው ጋር እንኳ፡ ጥያቄውን አንሥቶ ሊነጋገርበት ይፈራል። በዚህ ረገድ፡ ከሚያስፈሩት ነገሮች መካከል፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ "ሥጋዊነት"ን፡ በቅዱሱ "መንፈሳዊነት" ላይ መሥርቶ የመኖርን ሥርዓት የሚያስቀድምና የሚያረጋግጥ ህልውና ስለኾነ፡ ትውልዱ ደግሞ፡ በባዕዳኑ ዘመናዊ ሥልጣኔ ምክንያት፡ "ሥጋዊነት" ስለሚያጠቃው፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ከእርሱ ከሚጠይቀው መንፈሳዊ ግዳጁ ለመራቅ ሲል፡ በራሱ ደካማነት የሚፈጥረው ፍርሃት፡ አንዱ ነው።

በዚህ መልክ፡ ራሱ፡ በውስጡ ከፈጠረው ሁከት ጋር፡ ሌላ ችግር ደግሞ አብሮ ይመጣል፤ ይኸውም፡ ገና ለገና "ከውጭ ሊደርስብኝ ይችል ይኾናል!" ብሎ፡ በአሳቡ የሚፈጥረው የችግር ፍርሃት ነው። የዚህ ፍርሃት መንሥዔ፡ ብዙ ገጽታ አለው፤ ከእነዚህ መካከል፡ የሚከተሉትን፡ ለዓይነት ያህል ማቅረብ ይቻላል፦ "በጊዜው ሠልጥኖ የሚገኘው ሰብኣዊ መንግሥት፡ ስለዚህ፡ 'ኢትዮጵያዊነት' ጥያቄ፡ ተጻራሪ አቋም፡ ወይም ርእዮተ ዓለም ያለው ከኾነ፡ ጥያቄውን ማንሣቱ፡ እንኳንስ ትላልቁን፡ አነስተኛዋንም ብትኾን፡ ያችኑ፡ 'ለግልና ለቤተሰብ ኑሮዬ ማቆያ የያዝኋትን÷ ወይም አቋቁሜ የማካኺዳትን ሥራ÷ ወይም፡ የማገኛትን ጥቅሜን፡ ወይም ሀብቴን÷ ወይም፡ ክብሬን÷ ወይም፡ ጡረታዬንና ሌላውን ይዞታዬን፡ ካለችኝ የተወሰነች ነጻነቴና መብቴ ጋር የሚያላጣ ችግር ያመጣብኝ ይኾናል!'" የሚለው አንዱ ገጽታው ነው። ከዚያም አልፎ፡ ለግዞት÷ ለእሥራትና ለሞት የሚያበቃ መከራ ቢያደርስብኝስ?" ብሎ፡ የሌለውን ፍርሃት፡ ራሱ፡ በራሱ ውስጥ በመፍጠር፡ ሥጋቱና ጭንቀቱ፡ በበለጠ እየጨመረ እንዲኼድ የሚያደርገውም ኹኔታ፡ ሌላው ገጽታ ነው።

ከእነዚህ ምክንያቶች የተነሣ፡ "እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት" ስለሚጠላው፡ ስለእርሱ፡ ማወቅ ቀርቶ፡ ማሰብም እንኳ አይፈልግም። ጠይቆ እንዳያውቅ፡ እንደምትሉት ከሚያስፈራሩት ምክንያቶች መካከል፡ አንዳንዱን፡ ግልጹንና የቅርቡን ልጠቃቅስላችሁ ብዬ ነው እንጂ፡ ሌሎችም አሉ፤ እነዚያም፡ ባለፉት ድርሰቶቼ ውስጥ ስለተጠቃለሉ÷ በዚህ ውይይትም ውስጥ፡ አግባብነት ያላቸው፡ በእየመልኩ ስለሚቀርቡ፡ እዚህ ላይ መዘርዘሩ አስፈላጊ አልመሰለኝም፤ በእየቦታቸው ልታገኟቸው ይቻላል።

እናንተ እየራሳችሁ ግን፡ አኹን እንዳደረጋችሁት፡ እግዚአብሔር በሰጣችሁ የተፈጥሮ እውቀትና እንደቃል ኪዳኑ፡ በሕይወታችሁ ባስተማራችሁ ትምህርት፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት"፡ እውነቱን ለማወቅ፡ መጠየቅንና መመራመርን÷ ካወቃችሁም በኋላ፡ በይፋ መናገርን አትፍሩ! በማናቸውም ኹኔታ፡ ስለእውነት÷ ያውም፡ **ስለእግዚአብሔር እውነት**፡ ለማወቅና ለመናገር ደፋርና ቆራጥ÷ ጨካኝም ኹኑ! ልትሠቀቁ÷ ልትጠሉትና ልትርቁት የሚገባችሁ፡ **የዲያብሎስን ሐሰት** ነው።

እንደደግነትና ክፋት፥ እንደፍቅርና ጥላቻ፥ እንደብርሃንና ጨለማ ኹሉ፡ "ድፍረት" እና "ፍርሃት"ም፡ አንዱ፡ የእግዚአብሔር፥ ሌላው፡ የዲያብሎስ ነው፤ "ድፍረት"፡ የእግዚአብሔር ወገን መኾኑ የሚታወቀው፡ "እውነት"ን የያዘ ሰው፡ በውስጡም፡ በውጪውም፡ ደፋር ነው፤ አይፈራም። "ደግ ሰው"፡ የውስጥ ሥራውን፡ በግልጥ ያደርጋል፤ ደፋር ነው። "ፍቅር" ያለው ሰው፡ ኹሉን ሲያደርግ፡ በብርሃን ነው፤ አይፈራም።

በዚህ አንጻር ደግሞ፡ "ፍርሃት"፡ የዲያብሎስ ወገን መኾኑ የሚታወቀው፡ "ሐሰት"ን የያዘ ሰው፡ በውስጡ፡ ፈሪ ነው፤ ያፍራል፤ ስለዚህ፡ በግልጥ የሚያደርገው፡ ምንም ነገር የለም። "ክፉ ሰው"፡ ስለሚፈራና ስለሚሠጋ፡ ሥራውን፡ በሥውር ያደርጋል። "ጥላቻ"፡ ያለበት ሰው፡ ክፉቱን ኹሉ የሚያደርገው፡ በምሥጢር፥ በጨለማ ነው፤ በጣም ይፈራል። ለዚህ ነው፡ ሐዋርያው፡- *"ፍጹም ፍቅር፡ ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ፡ በፍቅር፡ ፍርሃት የለም! ፍርሃት፡ ቅጣት አለውና፤ የሚፈራም ሰው፡ ፍቅሩ፡ ፍጹም አይደለምና።"* ሲል የጻፈው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ *"ብርሃን ወደዓለም ስለመጣ፥ ሰዎችም፡ ሥራቸው ክፉ ነበርና፥ ከብርሃን ይልቅ፡ ጨለማን ስለወደዱ፡ ፍርዱ ይህ ነው። ክፉን የሚያደርግ ኹሉ፡ ብርሃንን ይጠላልና፤ ሥራውም እንዳይገለጥ፡ ወደብርሃን አይመጣም። እውነትን የሚያደርግ ግን፡ ሥራው፡ በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ኾነ ይገለጥ ዘንድ፡ ወደብርሃን ይመጣል።"*[፳፱] ብሎ የተናገረው፡ ስለዚህ ነው።

ኢትዮጵያዊ፡ ስለእግዚአብሔር እውነት፡ ደፋር ነው፤ ምንም ነገር አይፈራም፤ ጀግና የኾነውም፡ ስለዚህ ነው። ለእግዚአብሔር እውነት፡ ፈሪዎች ከኾናችሁ፥ ወይም፡ በውስጣችሁ፡ ፍርሃት የሚሰማችሁ ከኾናችሁ፡ ጊዜው የወለዳችሁ፡ "ኢትዮጵያውያን" እንጂ፡ "እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን" አለመኾናችሁን፡ በዚህ ስሜታችሁ፡ እየራሳችሁን፡ እየራሳችሁ፡ በውስጣችሁ ታውቁታላችሁ። ፍርሃት፡ በውስጣችሁ እስካለ ድረስ ደግሞ፡ በውስጣችሁ፡ ሰላምና ጸጥታ፥ ደስታና ዕረፍት ሊኖሩ አይችሉም። እነዚህ፡ የመልካም ሕይወት ሀብታት፡ እንዲኖሩዋችሁ ከፈለጋችሁ ደግሞ፡ ስለ"እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት" ትክክለኛው እውቀት ሊኖራችሁ ይገባል።

አኹንም እናንተ፡ አትፍሩ! *"ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ ላመኑበት አይሁድ፡ 'እናንተ፡ በቃሌ ብትጸኑ፡ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቁታላችሁ፤ እውነትም፡ ነጻ ታደርጋችኋለች።'"*[፴] ያላቸውን እያስታወሳችሁ፡ ራሳችሁን፡ የእግዚአብሔር እውነት በኾነው፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ከፍርሃት እሥረኛነት፡ ነጻ አድርጉ!

ጥያቄ፡- *ስለጠቃሚ ምክርህ፡ "እግዚአብሔር ይስጥልን!" እያልን፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ሳይቀር፡ እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት የሚጠላው ለምን እንደ ኾነ ብትገልጥልን?*

መልስ፡- "እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት"፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የሰጠው፡ የመጨረሻው ዘለዓለማዊና ፍጹም የኾነው፡ መልካሙ የሕይወትና የህልውና ሥርዓት ስለኾነ፡ አንድ ግለሰብ፡ ይህንኑ፡ ታላቅ መለኮታዊ ስጦታ፡ በሃይማኖት ተቀብሎ ለመኖር፡ የታወቀውን መሥዋዕትነት እንዲከፍል ይጠየቃል፡ ነገር ግን፡ ይኸው ግለሰብ፡ በዓለማውያን ባዕዳን ሥርዓተ ትምህርትና ሥርዓተ ሕይወት ታንፆ ያደገ ከኾነ፡ የአእምሮው ሥጋዊ አቋም፡ በመሠረቱ፡ "እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት" በሃይማኖት እንዲቀበለው፡ ከዚያም፡ በእርሱ ለመኖር፡ የሚጠየቀውን መሥዋዕትነት እንዲከፍል ስለማይፈቅድለት፡ በዚህ ምክንያት፡ "ኢትዮጵያዊነት"ን፡ ገና ሲያስበው ይጠላዋል። ከዚህ የተነሣ፡ ቀደም ብዬ እንዳወሳሁት፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት"፡ በገሃድ የሚመሰክር ቀርቶ፡ ከዚያ በመለስ፡ እንዲህ፡ እንደእናንተ፡ በይፋ የሚጠይቅ፡ ያም "በዛ!" ቢባል፡ እውነቱን በጽሙና ለማወቅ የሚፈልግ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚል ዜጋ፡ በአኹኑ ጊዜ ለመኖሩ፡ እጠራጠራለሁ።

ይኹን እንጂ፡ እንዲህ ያለው ዜጋ፡ ይኑርም፡ አይኑርም፡ ወደደም፡ ጠላም፡ እርሱና ሊላው፡ ማንኛውም ሰው፡ ሴቱም፡ ወንዱም፡ ወጣቱም፡ አዛውንቱም፡ በተለይ በዛሬው ዘመን፡ ይህን፡ "የኢትዮጵያዊነት" ጥያቄ፡ ሊጠይቀውና እውነተኛውን መልስ አግኝቶ ሊያውቀው የሚገባ፡ የህልውና፡ ግለትም፡ የሕይወት ወይም የሞት ጥያቄ ስለኾነ፡ መልሱ፡ ተሟልቶ፡ በዚህ፡ በጀመርነው ውይይት አማካይነት ቀርቦለታል።

ሦስት ተከታታይ ክፍሎች ያሉት፡ ይህ ውይይት፡ ለዚህ ታላቅ ጥያቄ፡ ምላሽ እንዲኾን የተዘጋጀ መኾኑን ስገልጽላችሁ፡ ደስ ይለኛል። በዚህ ውይይት ውስጥ የሚያነጋግረን፡ ዋናው ቁም ነገር፡ "ኢትዮጵያ" የሚለው መጠሪያ ስም፡ ወይም፡ ከእርሱ የሠረፀው፡ "ኢትዮጵያዊነት" የሚለው የቃሉ ምንጭና ትርጉሙ አይደለም፡ ለአንድ አካል፡ የተለያየ ብዙ ስም ሊወጣለት ይችላል፡ ያም አካል፡ በማናቸውም ስም ቢጠራ፡ በባሕርዩ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ እንደሌለ ታውቃላችሁ፤ ስለዚህ፡ የመነጋገሪያችን ወቢይ ቁም ነገር፡ በይበልጥ፡ ረቂቅ የኾነው፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" የተፈጥሮ ባሕርይ፡ ማለትም፡ የ"ኢትዮጵያዊነት"፡ እውነተኛ ምንነቱ፡ ምን እንደኾነ፡ በትክክልና በግልጽ የሚሳወቁና የማወቁ፡ የመታወቁም ጉዳይ እንጂ፡ የመጠሪያ ስሙና የቃሉ ትርጉም አለመኾኑን እንድትገነዘቡልኝ፡ በቅድሚያ አሳስባችኋለሁ።

በ"ኢትዮጵያዊነት" ላይ፡ ለምን ማተኮር አስፈለገ?
ስለእርሱስ፡ ምን የሚነገር፡ መልካም ነገር አለ?

ጥያቄ፡- *ስማቸውን፡ ከላይ እንደጠቀስኻቸው፡ እንዳለፉት ድርሰቶችህ ኹሉ፡ ሣራም፡ በዚህ ውይይታችን፡ ለምን፡ በ"ኢትዮጵያዊነት" ላይ አተኰርህ?*

መልስ፡- በ"ኢትዮጵያዊነት" ላይ ያተኰርሁት፡ ያለበቂ ምክንያት እንዳይመስላችሁ!

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት
"'እኔ' የምለው እኔነቴ፡ ማነው?"

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ደመኞች ጠላቶች የኾኑት፡ ሥጋውያንና መንፈሳውያን ኃይላት፡ ባለፈውም ኾነ አኹን፥ ወደፊትም፡ አተኵረውና አጠንክረው የሚረባረቡት፡ ይህን 'ኢትዮጵያዊነት' ደምስሰው ለማጥፋት በመኾኑ ነው። 'ኢትዮጵያዊነት' ደግሞ፡ የእግዚአብሔር ሥራ ከመኾኑ የተነሣ፡ ሊጠፋ የማይችል 'ልዩ ህልውና' መኾኑን፡ ለእኒህ ጠላቶች ብቻ ሳይኾን፡ 'ወዳጅ ነኝ!' ለሚለው ጭምር፡ አረጋግጠ ማሳየት፡ እጅግ አስፈላጊ ከኾነበት፡ ከመጨረሻው ዘመንና ደረጃ ደርሰናል፣ እኔም፡ ይህን ተልእኮ እፈጽም ዘንድ፡ የ"ኢትዮጵያዊነቴ" ግዳጅ እየጠራ ያሳስበኛል።

የኢትዮጵያዊነት ህልውናና በህልውናው ለመቀጠል የመቻሉ ምሥጢር የሚገኘው፡ የት መሰላችሁ? ይህንኑ፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ ደምስሰው ሊያጠፉት ባላቸው ክፉ ዓላማ፡ ከተነሣሡት የጠላቶቹ ኃይላት፡ ያለማቋረጥ የሚደርስበትን ግዙፍና ረቂቅ ጥቃት ተቋቁመው በሚታገሉለት፡ በታማኞቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ነው! አዎን፥ እነርሱ፡ በሃይማኖት በሚያደርጉት፡ ሥጋዊና መንፈሳዊ የትንንቅ ጦርነት፡ ሲከፍሉለት በኖረውና ዛሬም እየከፈሉለት ባለው የመሥዋዕትነት ዋጋ ነው። ይህን እውነታ፡ እናንተም፥ ሌላውም ኹሉ ፡ በግልጽ ልታውቁት ይገባል።

በአኹኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ላይ እንዳተኮር የተገደድሁበት ሌላም ምክንያት አለ፤ ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ፡ ይህ ትውልድ፡ ስለኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ፡ ጨርሶ እንዳያውቅ፡ በጠላቶቹ የተተለመለት ዕቅድ ተፈጽሞበት፥ ከዚሁ አላዋቂነቱ የተነሣ፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ ከአለበት ውርደቱና ውድቀቱ አድርሶት እንደሚገኝ እንመለከታለን። ይህም የኾነው፡ ትውልዱ፡ በቃል ይማረው ዘንድ፥ በጽሑፍም ያነብበውና ያውቀው ዘንድ፡ ይህን፡ የማንነቱን ዋና ቁም ነገር፡ በትክክልና በግልጽ ሊገነዘብ የሚችልበት መመሪያ፡ ኾን ተብሎ እንዳይዘጋጅ በመደረጉ መኾኑ፡ ይታመናል። ስለዚህ፡ በአገር ውስጥ ላለው ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ በዚህ የመከራው ዘመን፡ በመላው ዓለም ተበትኖ ለሚገኘው፡ ለዚሁ፡ በአላዋቂነት ለባዘነው ትውልድ፥ ከእርሱም ለሚፈጠሩት የወደፊት ልጆቹ፡ ***<u>ይህንኑ፡ በቃል እየተላለፈ የኖረውን፡ የማንነቱ ማሳወቂያ የኾነውን፡ የኢትዮጵያዊነት መመሪያ፡ በቃል ብቻ ሳይኾን፡ በጽሑፍ ለጠናቅሮና ለከናውኖ ማቅረብ አስፈላጊ ኾነ!</u>***

ይህ ችግር መኖሩን በይበልጥ የተረዳሁት፡ በተለይ፡ ከደርግ፡ የአገዛዝ ዘመን አንሥቶ፡ በእሥራትና በግዞት በቆየሁባት፡ በአገሬ፥ ኋላም፡ በፈቃዴ በገባሁበት የስደት ኑሮ፡ በባዕዳኑ አህጉር፡ በተዘዋወርሁባቸው ዓመታት፡ ለዘመኑ ትውልድ፡ ስለማንነታችን ለማሳወቅና ለማስተማር በምጥርበት ጊዜ፡ በዚህ ረገድ፡ ይገጥመኝ ከነበረው፡ ከባድና አጣብቂኝ ችግር ነበር፣ ለዚህም ችግር፡ መውጫ ኾኖ ያገኘሁት ብቸኛው መፍትሔ፡ ይህንኑ፡ የኢትዮጵያዊነት መመሪያ፡ በጽሑፍ ማዘጋጀት መኾኑን፡ እዚህ ላይ ሳልጠቅሰው አላልፍም።

ጥያቄ፡- ስለ"ኢትዮጵያዊነት" መልካምነት፡ በአኹኑ ዘመን ላለው ትውልድ መናገር የሚከብድና የሚያስቸግር አይመስልህም? ምክንያቱም፡ ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከት፡ በጊዜያችን፡ የምንሰማውና የምናየው፡ ከክፉው ገጽታው በስተቀር፡ አንዳችም በጎ ነገር ወይም ሥራ ስለሌለ ነው!

መልስ፡- አዎን! እውነታችሁን ነው፤ ታላላቅ ተጋድሎዎችን እያለፈ፡ ለዚህ ያልተቋረጠ ህልውናው ስለበቃው "ኢትዮጵያዊነት"፡ ስለመልካምነቱ፥ በተለይ፡ ለአኹኑ ዘመን ትውልድ ለመናገር፡ በእርግጥ፡ እጅግ ይከብዳል፤ የሚከብድበትንም ምክንያት፡ እዚህ ላይ፡ በሰፊው መዘርዘር ያዳግታል፤ ነገር ግን፡ አግባብነት ያላቸውን፥ ግልጽና የቅርብ የኾኑትን ብቻ፡ ከዚህ እንደሚከተለው ልጥቀስላችሁ!

የመጀመሪያው ምክንያት፡ ከግለሰብ አልፎ፡ በዓለሙ ኹሉ ዘንድ የታወቀውና በትውልዱ ላይ፡ እነሆ፡ ዛሬ እየወረደበት ያለውን መቅሠፍት ያስከተለው ክፉው ኹኔታ መስፈኑ ነው፤ ይኸውም፡ ከደርግ መምጣት በፊትም ኾነ በኋላ፡ በሃይማኖታዊው አምልኮና ምግባር ሳይቀር፡ በኢትዮጵያ ምድርና በኢትዮጵያውያን መካከል፡ በሥውርና በገሃድ፡ የተካኼደውና የሚካኼደው፡ የከህደትና የዓመፅ፥ የአመንዝራነትና የበደል፥ የግፍና የጭካኔ፥ በጠቅላላ፡ የዲያብሎስ ተግባር ነው።

ኹለተኛው ምክንያት ደግሞ፡ ይኸው ትውልድ ከታነፀበት፡ ከባዕዳኑ ሥጋዊ ሥርዓተ ትምህርትና ዓለማዊ አስተሳሰብ የተነሣ፡ "ኢትዮጵያዊነት"ን በሚመለከት፡ ሊያውቅ ስለሚገባው፡ ስለእውነተኛ ባሕርዩና ገጽታው ቀርቶ፡ ስለጥቃቅን ይዞታዎቹ እንኳ፡ እንዳይነገረው፡ እስካኹን ተከልክሎ መኖሩ ነው፤ ለትውልዱ፡ በአብዛኛው የተነገረው፥ እንዲያውቅና እንዲያይ የተደረገው፥ በአሉታዊ መልኩም፡ ደርሶ ያየው ነገር ቢኖር፡ "የኢትዮጵያዊነት"ን፡ ጎጂነቱንና መጥፎነቱን፥ አድኃሪነቱንም፡ ማለትም፡ ከሥጋዊው ሥልጣኔ፡ ወደኋላ የማስቀረት ተቃራኒ ኃይል ያለበት በማስመሰል፡ ጎታችነቱን ብቻ እንጂ፡ መልካም ገጽታውን አልነበረም፤ አይደለምም።

ሌላው ቢቀር፡ በጎጂነትና በጥፉነት፥ በአድኃሪነትም ተፈርጆና ተሥሎ ከቀረበበት፡ ከዚህ መልኩ ጎን፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ለአያሌ ሽህ ዓመታት፡ <u>በነጻ ህልውናው ለመቆየት</u> ያስቻለው፡ አንድ ልዩ ምሥጢራዊ ኃይል መኖሩን እንዲገነዘበው፥ ያም ምሥጢራዊ ኃይል፡ ምን እንደኾነ፡ እንዲጠይቅ እንኳ የሚያነቃቃ የትምህርት ፍንጭ፡ በአምንታዊ መልኩ ያልተሰጠው መኾኑ፡ ይህን እውነታ ያረጋግጣል።

ሦስተኛውም ምክንያት፡ ትውልዱ፡ በዘመኑ ከሚያውቃቸው፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት መካከል፡ ለዚህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ በጎ አርአያነት፡ ወይም ምሳሌነት ያላቸው ኾነው፡ በጉልህ የሚቀርቡለት፡ ሕያዋን ገጸ ባሕርያትን ለማግኘት፡ ቀላል አለመኾኑ ነው። ቢኖሩም፡ ትውልዱ እንዳያውቃቸው የሚያደርገው፡ ተጻራሪው የባዕዳኑ ሥርዓት፡ ኃይሉ፡ በኢትዮጵያ ምድር እየሰፈነ በመኼድ ላይ ስለሚገኝ፡ እንደ"ሙታን" እንዲቆጠሩ ስላደረጋቸው፡ ሕያው ማንነታቸው፡ ግልጽ ኾኖ ሊወጣ አልቻለም።

ከዚህ የተነሣ፡ በሕይወተ ሥጋ የሚንቀሳቀሱ፡ ሕያዋን ገጸ ባሕርያት ሊታዩ ባይቻልም እንኳ፡ ሙያቸው፡ እየጮኽ፥ ብርሃናቸውም፡ እያንጸባረቀ የሚናገርላቸው፡ በዕረፍተ ሥጋ የተለዩ፡ የቀደሙ፡ ሕያዋን ገጸ ባሕርያት መኖራቸው የተረጋገጠ ሲኾን፡ ነገር ግን፡ ይኸው፡ ምንነታቸውና ማንነታቸው፡ በትውልዱ ዘንድ እንዲታወቅ አልተፈለገም።

የተፈለገው፡ ይኸው ስለኾነ፡ እነዚሁ፡ ስመጥር ባለሙያዎች ጭምር፡ "ሙታን" ተብለው፡ ዜና መዋዕላቸውና ዝክረ ነገራቸው፡ ከሥጋቸው ጋር በመቃብር በስብሶ እንዲጠፋ፥ ያም ባይቻል፡ በመቃብር ውስጥ፡ በብረት መቀርቀሪያ ተቆልፎበት እንዲረሳ ተደረገ።

በክፉው ጊዜ ቀርቶ፡ በሰላሙ ዘመን እንኳ፡ "'ኢትዮጵያዊነታችንን' ከምናጣ፡ ሌላው ባዕድ የኾነው፡ ሥጋዊ ጥጋብና ምቾት፥ ተድላና ደስታ ይቅርብን!" ብለው፡ ጠማቸውን ውለው እያደሩ፥ ቢበዛ፡ ውኃ ጠጥተውና ጥሬ ቆርጥመው፥ ቍራጭ ጨርቅ አጣፍተውና በባዶ እግራቸው ተመላልሰው፥ የሞቀ ትዳራቸውንና ቤተሰባቸውን ትተው፡ በዱር በገደሉና በእየበረሃው እየተዘዋወሩ፡ እንዲያ ባለ ድኅነትና ችግር ተቆራምደው የኖሩት እነማን ናቸው? ወራሪ ጠላት በመጣባቸውም ጊዜ፡ እግራቸውን ለጠጠር፥ ደረታቸውንም ለጦርና ለአረር ሰጥተው በመጋፈጥ፡ ሥጋቸውን ቆራርሰው፥ ደማቸውን አፍስሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው፥ በመጨረሻም፡ ሕይወታቸውን ሠውተው፡ ይህን "ኢትዮጵያዊነት"፡ ለዛሬው ትውልድ ያስረከቡት፡ እኒያ፡ ጀግኖችና ባለሙያዎች አባቶቹና እናቶቹ አይደሉምን? እነርሱንማ፡ ትውልዱ፡ "ሙታን ናቸው" ብሎ እንዲያስባቸው፥ አእምሮው፡ በባዕዳን ሥርዓተ ትምህርት ተቀርያና ታንፆ፥ የእነርሱን፡ የባዕዳኑን ባለሙያዎችና ጀግኖች ብቻ በገናናነት እያወደሰ እንዲያድግ ስለተደረገ፡ አምን፡ እነርሱ፡ የራሱ የኾኑትማ፡ ሕያዋን ገጸ ባሕርያት ኾነው፡ ለዚህ ትውልድ፡ ሊቀርቡለት፡ በእርግጥ አልተቻለም።

"ኢትዮጵያዊነት"፡ ዛሬ፡ በእርግጥ አለ? ወይስ፡ የለም? ካለስ፡ እውነተኛው፡ ከሐሰተኛው በምን ይለያል?

ጥያቄ፡- ታዲያ! ዛሬ፡ በሕይወተ ሥጋ የሚንቀሳቀሱት ኾኑ፡ ቀደም ብለው፡ በሞተ ሥጋ የተለዩት፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፡ እንዲሁ፡ በሓሳውያኑ ወገኖቻቸውና በባዕዳኑ ተጻራሪዎቻቸው ምክንያት፡ "ኢትዮጵያዊነት"ን፡ በኀብረተሰብና በአገር ደረጃ፡ በይፋ፡ ገሃድ አድርገው፡ በምግባር ሊገልጹት ስላልተቻላቸው፡ መልካም የኾነው "ኢትዮጵያዊነት" የለም፥ አይኖርም፥ ጠፍቷል፡ ወይም፡ ይጠፋል ማለት ነውን?

መልስ፡- አይደለም። "እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት"፡ በምንም ምክንያት፥ ምንጊዜም ጠፍቶ አያውቅም፣ በእግዚአብሔር የተመሠረተና የታነፀ፥ የተጠበቀና የሚጠበቅ፡ ዘለዓለማዊ ህልውና ስለኾነ፡ ሊጠፋም ከቶ አይችልም። አዎን! <u>"እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት"፡ ለወንዶቹ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፥ ለሴቶቹም፡ በድንግል ማርያም፡ ሕያው አርአያነት፡ ለዘለዓለም፡ ይኖራል።</u> በሰው ልጆችም ዘንድ፡ ህልውናው፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ በአንድ ግለሰብና በቤተሰብ ደረጃ ይቀጥላል። ለዚህም፡ ከብዙዎች መካከል፡ አንዱ የኾነውን፡ የሩቁንና የጥንቱን፡ ኖኅንና ቤተሰቡን ከነተግባራቸው፡ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል።

ምዕራፍ ፪፤
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤
"ኢትዮጵያዊነት"፡ ዛሬ፡ በእርግጥ አለ? ወይስ፡ የለም?
ካለስ፡ እውነተኛው፡ ከሓሰተኛው በምን ይለያል?

እግዚአብሔር፡ በአዳምና ሔዋን የጋብቻ ሕይወት ላይ መሥርቶት፡ ከወላጆች ወደልጆች፡ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ተያይዞ፡ ለኖኅ ዘመን የደረሰው፡ ይህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ እንደዛሬው ዅሉ፡ በአገር ደረጃ ብቻ ሳይኾን፡ በመላው የዓለም ኅብረተሰብ ደረጃ እንኳ ሳይቀር ተክዶ፡ እንዲጠፋ በተደረገበት ጊዜ፡ ዐኖኅና በቤተሰቡ ዘንድ፡ ተጠብቆ በመቀጠሉ፡ እነሆ፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ ዛሬ ያለነው ኢትዮጵያውያን ተረክበነው፡ ይኸው፡ ልንኖርበትና ልንጋደልለት በቅተናል።

የኖኅ ነገር ከተነሣ ዘንድ፡ በእዅኑ ዘመን፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት" ወይም ስለ"እግዚአብሔር እውነት"፡ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም ሕዝቦች ዘንድ ያለውን የአስተሳሰብ÷ የሃይማኖትና የምግባር አቋም፡ በኖኅ ዘመን ከነበረው ጋር ሲያስተያዩትና ሲያመዛዝኑት፡ ልክ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ዅኖ ስለሚገኝ፡ እንደነቃለን፤ በዚህ ረገድ፡ እኛም፡ በኢትዮጵያዊነታችን፡ የተያያዝነው ተጋድሎ፡ እንደኖኅ ገድል፡ ለመጪረሻው ምዕራፍ ይበቃ ዘንድ፡ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፡ ተስፋችንን ያጠናክርልናል። ይህም፡ እንዲህ በሚለው መለኮታዊ ቃሉ፡ ተብራርቶ ይነበባል፡-

"የኖኅ ዘመን እንደነበረ፡ የሰው ልጅ መምጣት፡ እንዲሁ ይኾናልና። በዚያች ወራት፡ ከጥፋት ውኃ በፊት፡ ኖኅ፡ ወደመርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፡ ሲበሉና ሲጠጡ÷ ሲያገቡና ሲጋቡ እንደነበሩ÷ የጥፋት ውኃም መጥቶ፡ ዅሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፡ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ፡ እንዲሁ ይኾናል። በዚያን ጊዜ፡ ዅለት ሰዎች፡ በእርሻ ይኾናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል÷ አንዱም ይቀራል፤ ዅለት ሴቶች፡ በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች÷ አንዲቱም ትቀራለች። ጌታችሁ፡ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና፡ እንግዲህ ንቁ!

"ያን ግን እወቁ! ባለቤት፡ ከሌሊቱ፡ በየትኛው ክፍል፡ ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፡ በነቃ፤ ቤቱም፡ እንዲቆፈር፡ ባልተወውም ነበር። ስለዚህ፡ እናንተ ደግሞ፡ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ! የሰው ልጅ፡ በማታስቡበት ሰዓት፡ ይመጣልና።"[፬]

መቼም፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ የኾነው እውነተኛው ነገር ዅሉ፡ ዛሬ ባለው የኢትዮጵያና የዓለሙ ትውልድ ዘንድ፡ በግለሰብና በቤተሰብ÷ በብሔረሰብና በዓለም ኅብረተሕዝብ ደረጃ፡ ተንቆ የተተወ ብቻ ሳይኾን፡ የተካደና የታመፀበትም መኾኑ፡ በገሃድ ስለሚታይ፡ ከላይ የተጠቀሰውን መለኮታዊ የማስጠንቀቂያ ቃል፡ ከደርግ በፊትና በኋላ ከደረሰው ግዙፍ ማስረጃ እንኳ ተምሮ፡ ያጤነውና የሚያጤነው፡ ስንቱ እንደኾነ መገመት ያዳግታል። ይኹን እንጂ፡ የአምላክ ቃል ስለማይታበል፡ ግና ቸውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ወገን፡ ከሚመጣው የመጨረሻ ጥፋት፡ እንደኖኅና ቤተሰቡ ይድን ዘንድ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ኪዳነ ምሕረት የተረከበውን፡ ይህን፡ የቅዱሱ ኪዳን "ኢትዮጵያዊነት" ሳያቃልልና ሳይንቅ÷ ቸል ሳይልና ሳይተው፡ በእውነት መንፈስ ጠብቆ እንዲገኝ፡ ሊያሳስበው፡ ይህ ውይይት ተዘጋጅቶ ቀርቦለታል።

ጥያቄ፡- *ለዚህ ጥያቄያችን: የሩቁን: የኖኅን ሃይማኖታዊ ምግባር: በምሳሌነት ጠቅሰህ የሰጠኸንን መልስ የሚመስል: ሌላ: በምሳሌነት የምትጠቅስልን: በአገራችን: በኢትዮጵያ የደረሰ: የቅርብ ጊዜ ዝክረ ነገር ይኖር ይሆን?*

መልስ፡- ሞልቶ!? ከብዙዎቹ መካከል: አንዱ: እነሆ: ይኸውላችሁ! ከዚህ በፊት ግን: አኹን ከማቀርብላችሁ ድርጊት ጋር በተያያዘ መልኩ: ልታውቁት የሚገባችሁ: ቁም ነገር አለ፤ ይህም: ወደፊት: በዚህ ውይይታችን ውስጥ: በስፋት ተዘርዝሮ እንደምታገኙት: "ኢትዮጵያዊነት" ሲባል: "የእነእከሊና የእነእከሊት ነው፤ ወይም: ለእነርሱ ብቻ: በኃላፊነት÷ በባላደራነት: ወይም በባለቤትነት የተሰጠ ስለኾነ: እኔን÷ ወይም እኛን አያመለከተንም: ወይም: አያስጠይቀንም!" ብላችሁ: ሌላው እንደፈለገ ሲያማስነው: እናንተ ግን: እየራሳችሁን: ወደውጭ አግልላችሁ: ከሩቅ: በዝምታ የምትመለከቱት አለመኾኑን ነው። "ኢትዮጵያውያን ነን!" ካላችሁ: እናንተንም ይመለከታችኋል፤ በኃላፊነትም ያስጠይቃችኋል። ይህን የምላችሁ: ለ"እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት" አርአያ አድርጌ: በምሳሌነት እጠቅስላችሁ ዘንድ: ቀጥዬ የማቀርባቸው "ኢትዮጵያዊ": እርሳቸውማ "እንዲያ ስለኾኑ ነው!" ብላችሁ ማመካኘት እንዳትጀምሩብኝ ብዬ ነው።

ድርጊቱ: አንድ ባዕድ ግፈኛ መንግሥት: በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም.: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ያደረገውን ወረራ ተከትሎ የተፈጸመ ነው። በተለይ: ለዛሬው የኢትዮያ ትውልድ: በጎ አርአያነት ስላለው: እዚህ ላይ: ሊጠቀስ ይገባዋል። ይኸውም: ራሱ: ኢትዮጵያዊነቱን ክዶ÷ ለኢትዮጵያ ጠላት: ለፋሺስት ኢጣልያም: በአገልጋይነት አድሮ: በዘብነት ይጠብቃቸው የነበረ: አንድ የወህኒ ቤት መኰንን: እሥረኛው ኢትዮጵያዊ ስማዕት: ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ: እንደእርሱና እርሱን እንደመሰሉት: እንደሌሎቹ: ግብዞች: ኢትዮጵያዊነታቸውን ክደው: የጠላታቸውን አገዛዝ እንዲቀበሉ: ከአለቆቹ: ተልኮ: ያባብላቸው በነበረ ጊዜ: "ባንዳ" የሚባለው: ይኸው ከሃዲው ሹምባሽ: እርሳቸውን ለማሳመን በሚያደርገው አቀራረብ እያዘኑ የሰጡት መልስ ነው።

አቡነ ጴጥሮስ: በተግሣፅ አኒጋገር:-

"አንዴ: እንደኢትዮጵያዊ: አንዴ: እንደሹምባሽ መናገር÷
"ችግር ካልከው: እሱ ይብሳል: ከችግርም ኹሉ መቸገር፣"

ሹምባሹ: በብስጭት አኒጋገር: ፊቱን አኰሳትሮ÷ ዓይኖቹንም አፍጥጦ እያያቸውና ቀኝ እጁን በዛቻ እየሠነዘረ: በውሳኔ የቁጣ ቃል:-

"ይህ አኹን ያለንበት: ዓለም ሌላ ነው: ዓይንዎን አይከፍቱም?
"እንኳንና ኢትዮጵያዊ: 'ኢትዮጵያ' የሚሏት የለችም!"

አቡነ ጴጥሮስ: ረጋ ባለ: የትካዜ ድምፅና የጸና አኒጋገር: አተኵረው እየተመለከቱት: በቁርጥ ቃል:-

"አዎን! አንተ ውስጥ የለችም: ምክንያቱም: አታምንባትም።
"አንተ: በእግዚአብሔር አታምንም:
"ወይም: በአገርህ አታምንም፣ ወይም: በራስህ አታምንም።

"ስለዚህ፡ የእምነት ምስኪን ነህ! መተማመኛ የሌለህ!
"እና፡ ለእኔ ኢታስብ! ቀድሞ፡ ለራስህ አታውቅም፣
"እኔ፡ በኢትዮጵያ ስለማምን፡
እኔ እስካመንሁ፡ እርሷ አትሞትምም!" [፴፩]

ጥያቄ፡- *የእኒህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ሰማዕት ዜና ሕይወት ከተነሣንድ፡ በዚያን ጊዜ፡ እርሳቸው፡ ቀደም ብለው ተቀብለውት የነበረውን ኃላፊነት እንደእርሳቸው የተቀበሉና እርሳቸውን የመሰሉ፥ ዛሬም የሚመስሉ ኢትዮጵያውያን አልነበሩም? የሉምም? ማለት ነውን?*

መልስ፡- አይደለም! ያኔም፡ ብዙዎች ነበሩ፡ ዛሬም፡ ብዙዎች አሉ እንጂ!

ጥያቄ፡- *ታዲያ! ለምን፡ አንድ፡ እርሳቸው ብቻ፡ ለዚህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ በእውነት መስክረው፡ በሰማዕትነት ለመሠዋት በቁ! ለምን፡ ሌሎቹም፡ በእርሳቸው ጊዜ የነበሩትም ኾኑ፡ ዛሬ ያሉት፡ እየራሳቸውን፡ እንደእርሳቸው፡ ለዚህ ምስክርነት፡ በመሥዋዕትነት ሳያቀርቡ ቀሩ? በዚያን ጊዜ፡ አንድ እርሳቸው ባይኖሩ ኖሮ፡ ወይም፡ ባሁኑ ጊዜ፡ እርሳቸውን የሚመስል ኢትዮጵያዊ ባይኖር፡ "ኢትዮጵያዊነት" ይጠፋል ማለት ነውን?*

ከእርሳቸው በኋላ፡ በእርሳቸው ስም፡ የድንጋይ ሐውልት፡ ለመታሰቢያነት ማቆሙ፡ ከዶ ለምን ይጠቅማል? እኛ፡ እንደተረዳነው፡ የሐውልቱ መቆም ዓላማ፡ በየዘመኑ የሚኖሩት ሕያዋን ኢትዮጵያውያን፡ ሊያደርጉ የሚገባቸውን፡ በሕይወት እያሉ እንዲፈጽሙ፡ የእኒያን ጀግና ባለሙያ ጊዶል፡ ሊያስታውሳቸው፡ ሊያነቃቃቸውና ሊያደፋፍራቸው አይደለምን?

መልስ፡- ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ ከጥንት፡ ነበሩ፡ ዛሬም፡ አሉ፡ ወደፊትም፡ በህልውናቸው ይቀጥላሉ፡ ለዚህ እውነታ፡ በዚያ ዘመን፡ ምስክር ሊኾኑ፡ አንድ፡ አቡነ ጴጥሮስ፡ ተገኝተው፡ ራሳቸውን፡ ለዚያ ሰማዕትነት ባያቀርቡ ኖሮ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ ከዶ፡ ምን ይውጣቸው እንደነበረ ለመገመት ያስቸግራል። ያማ ባይኾን ኖሮ፡ "የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ሰዎች፡ በገንዘብ የሚገዙና ደንቆሮዎች ናቸው!" በማለት፡ ኢጣልያውያን ይንቋቸውና ያጥላሏቸው ጀመር፡" ተብሎ፡ በዚያን ዘመን፡ በኢትዮጵያ ላይ ወድቆ ስለነበረው፡ ስለዚያ፡ የፋሺስት አገዛዝ፡ በቅርቡ፡ በአንድ ኢጣልያዊ ታሪክ ጸሓፊ የተመዘገበው፡ የዚያ ኢትዮጵያዊ ትውልድ አሳፋሪ ምግባር፡ እንዴት ሊስተባበልና ሊሻር ይቻል ነበር? [፴፪]

አኹንም፡ እናንተ ያቀረባችሁልኝ፡ ይህ ጥያቄያችሁ፡ እኛው ራሳችን፡ እየራሳችንን እየጠየቅን፡ በእየራሳችን ልንፈጽመው የሚገባን ከመኾኑ በቀር፡ እናንተም ልትጠይቁት፡ እኔም ልመልሰው የሚያስፈልገን አይመስለኝም።

ጥያቄው፡ ዛሬ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ ሥጋ ሣሉ፡ የገዛ ኅሊናቸው እየጠየቀ የሚፈርድባቸው፥ ኋላም፡ በሰማያት፡ በሕይወተ ነፍስ፡ በፈጣሪያቸው ፊት ተጠይቀው፡ ተገቢ ፍርዳቸውን የሚቀበሉበት፡ የቀደሙትንና የዛሬዎቹን፥ እናንተንና እኔን ጨምሮ፡ ኹሉን የሚመለከት ጉዳይ ነው። ይልቅስ፡ ይህን ጥያቄ፡ እናንተና እኔ፡ ኾኑኑ፡ ለእየራሳችን አቅርበን፡ ኾኑኑ፡ በእየራሳችን፡ መልስ ልንሰጥበትና ትክክለኛው ኅሊናችን የነገረንን መልስ፡ በምግባር ልንፈጽመው ይገባናል፤ የሐውልቱ ዓላማና መልእክት፡ እናንተንም፥ እኔንም ይመለከተናልና።

እዚህ ላይ፡ *"እንዳይፈረድባችሁ፡ አትፍረዱ!"*[ፍ] የተባለውን መለኮታዊ መመሪያ እንዳንዘነጋው፡ ላስታውሳችሁ እወድዳለሁ። ራሴን በምሳሌነት አቅርቤ እንድናገር ብትፈቅዱልኝ፡ እኔ፡ ሰው እንደመኾኔ፥ ከዚህም በላይ፡ እንደኢትዮጵያዊነቴ፡ ከእኔ የሚፈለገውን ተግባር፥ ድርሻዬ ኾኖ፡ የተሰጠኝን ግዳጅ መፈጸም እንጂ፡ ስለሌላው ሙያ ወይም ስንፍና፡ ፍርድ ለመስጠት፡ ምንም ዓይነት ሥልጣን የለኝም፤ ምናልባት፡ የማደርገው ነገር ቢኖር፡ እንደሰማዕቱ፡ አቡነ ጴጥሮስ፡ የእግዚአብሔርን እውነት መሠረት በማድረግ፡ ሊኾን የሚገባውን፡ ያለፍርሃት በግልጽ ከመመስከር፥ ከመምከርና ከማስታወስ፥ ከማሳሰብና ከማስጠንቀቅ ሊያልፍ አይችልም። ሌላው ሰው፡ የራሱ የኾነ ድርሻ አለው፤ ያም፡ እርሱ፡ የሚጠየቅበት ነው፤ እኔን አያገባኝም።

ሰጪው፥ ጠያቂው፥ ዋጋ ከፋዩና ፈራጁ፡ ፈጣሪ፡ ራሱ፡ ለእያንዳንዱ ሰው፡ የኃላፊነት ተግባሩን፥ ሙያውንና ግዳጁን ወስኖ ደልድሏል፤ በአደራ ስለሰጠው ሥራም፡ እያንዳንዱ፡ ፍሬውን እንዲያቀርብ በጊዜው ይጠይቃል፤ ዋጋውንም እንደየሥራ ፍሬው፡ ለእያንዳንዱ ይከፍላል፤ በትክክለኛ ዳኝነቱም፡ በእያንዳንዱ ላይ፡ የመጨረሻውን ፍርድ አሰምቶ፡ ፍርዱን ያስፈጽማል።

ጥያቄ፡- እስካኹን ባገኘነው እውቀት፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" በሚለው ዘንድ ቀርቶ፡ "ኢትዮጵያዊ አይደለሁም!" በሚለው ዘንድም እንኳ ቢኾን፡ "እሪ፡ ይህ፡ 'ኢትዮጵያዊነት' የሚባለው ነገር፡ ከቶ፡ ምን ይኾን? እስኪ ልወቀው! እስኪ ልረዳው!" ብሎ፡ በመጠየቅና በመመራመር፡ ከእውነቱ ለመድረስ፡ ፍላጎቱ ሊቀሰቀስበት የማይችል ሰው፥ በተለይም፡ የኖኅና የአቡነ ጴጥሮስ ወገን የኾነ ኢትዮጵያዊ፡ እንዴት ይኖራል?

መልስ፡- እንዳላችሁት፡ "ሊኖር አይችልም፤ ሊኖርም አይገባም፤" ቢባል፡ መልካም በኾነ ነበር። ነገር ግን፡ በብዛት አለ። መኖሩም፡ ይኸው፡ በገሃድ ይታያል። ይኹን እንጂ፡ በዚህ፡ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ላይ፡ ይህ ኹሉ፡ የፈተና መዓትና የመከራ መቅሠፍት እየወረደበት እያለ፡ የትውልዱ አባል የኾነ፡ እያንዳንዱ ግለሰብ፡ "የዚህ ጠንቀኛ ችግር፡ መነሻው ምክንያት፡ ከቶ ምንድር ነው?" ብሎ፡ እንዲህ እንደእናንተ፡ መሠረታዊዉን፡ የ"ኢትዮጵያዊነቱ"ን ጠንቀኛ በሽታ፡ ወደመጠየቁና ወደመመራመሩ የማያተኵር ካለ፡ እርሱ፡ "ከኢትዮጵያዊነት ውጭ የኾነ ሰብአዊ ፍጡር ነው!" ከሚለው ተነሥቶ፡ ስለእርሱ፡ ሌላም፡ ብዙ ነገር ሊባል ይቻላል።

ምዕራፍ ፪፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤
"ኢትዮጵያዊነት"፡ ዛሬ፡ በእርግጥ አለ? ወይስ፡ የለም?
ካለስ፡ እውነተኛው፡ ከሓሰተኛው በምን ይለያል?

እንዲህ ያለው ሰው፡ ራሱን ቄምር ባስጠመደበት፡ በጠላቱ ዲያብሎስ የክፋት መንፈስ፡ ወይም፡ "አፍዝ አደንግዝ" በሚሉት፡ በጠላቶቹ ምናምንቴ ድግምት የተተበተበ፡ ወይም፡ ለከንቱ ጊዜያዊ ጥቅም ሲል፡ ክብሩን አዋርዶና ራሱን ሸጦ፡ የማንነት አስተሳሰቡንም፡ በባዕድ ትምህርት ቤታነህ አእምሮው ውስጥ ለውጠ፡ ለፈቃደ ሥጋው በመገዛት፡ ለደመኞቹ፡ እጁን ሰጥቶ የተማረከ ሊኾን ይችላል። ወይም፡ ለሥጋው ደኅንነትና ምቾት ሲል፡ ምንም ዓይነት መሥዋዕትነት ሳይከፍል፡ በዓለማዊ ተድላ ደስታ ብቻ ቤመኖር፡ ለእነርሱ፡ ለባዕዳኑ፡ ባሪያ ኾኖ ለማገልገል የተስማማ፡ ወይም፡ ከሀገርና ከወገን ፍቅር ተራቁቶ፡ የዜግነት ኃላፊነት የማይሰማው፡ ወይም፡ ቤተፈጥሮው፡ ጅላጅል የኾነ ሰው፡ መኾን አለበት።

ይህን "ኢትዮጵያዊነት" የማሳወቅ ኃላፊነትና ግዴታ ካለበት ወገኑ፡ በዚህ ውይይት አማካይነት የቀረበለትን፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" እውነታ ለማወቅ የማይፈልግ፡ ነገር ግን፡ ይህ "ኢትዮጵያዊነት" እንዲጠፋና እንዲደመሰስ የሚጥረው ጠላቱ እና/ወይም ባዕዱ፡ የሚነግረውን ብቻ፡ በታዛዥነት የሚሰማ፡ ከእነርሱ የሚሰጠውንም መምሪያ ብቻ በተባባሪነት የሚከተል፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚል ወገን ቢኖር፡ ኢትዮጵያዊነቱ አጠያያቂ ከመኾኑ ጋር፡ ከእነዚያ፡ አስጠቂዎችና ደኅማዎች ተለይቶ ሊታይ አይቻልም።

ይህ አባባሌ፡ አንዱ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ፡ ተመሳሳይ ኹኔታ አጋጥሞት፡ የጻፈውን ያስታውሰኛል፡ እርሱም፡ "*እናንት፡ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ! በዓይናችሁ ፊት ተሥሎ የሚታየውን እውነት፡ አምናችሁ እንዳትቀበሉ፡ እንዲህ የሚያቆዝማችሁን አፍዝ አደንግዝ ያደረገባችሁ ከቶ ማነው?*" የሚለው ነው። ይህ፡ አምላካዊ ቃል፡ እኔን ብቻ ሳይኾን፡ "ምን መኾንህ ነው? ምን እስክትኾን ድረስ ነው፡ የምትጠብቀው? ምን መኾንሽ ነው? ምን እስክትኾኚ ድረስ ነው የምትጠብቂው?" እያለ፡ እናንተንና እናንተን የመሰሉትን ኹሉ፡ ጉዳዩ የሚመለከተውን ቄምር፡ በጋለ የብረት ሾተል፡ እየወጋ ሊያስታውስ፡ የተጠቀሰ መኾኑን መገንዘብ ይገባል።

እናንተም፡ "ኢትዮጵያውያን ነን" ካላችሁ፡ ይህም፡ በእውነት፡ ከልባችሁ ከኾነ፡ ስለዚህ፡ ስለምንወያይበት፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ የግድ መጠየቅና ማወቅ አለባችሁ! ይህ ግዳጅ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ፡ የሚለው፡ ወገን ኹሉ፡ በግልም፡ በጋራም፡ ሊጠይቀውና ሊያውቀው የሚገባ መኾኑን፡ እዚህ ላይ አበክሬ መግለጽ እወድዳለሁ።

ጥያቄ፡- የዚህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ እውንነትና እውነተኛነት የሚረጋገጠው፡ እውነተኛውንም፡ ከሓሰተኛው የምትለየው በምንድር ነው?

መልስ፡- <u>ይህ "ኢትዮጵያዊነት"፡ በአንተ፥ በአንቺ፥ ወይም፡ በእኔ ሰውነትና ህልውና፡ ሕያው ኾኖ በመኖሩ፡ እውንነቱና እውነተኛነቱ ይረጋገጣል!</u>" ከሓሰተኛው ተለይቶ የሚታወቀውም፡ ስለእግዚአብሔር እውነት፡ በመንፈስና በብርሃን በመመስከሩ፡ የዲያብሎስንም ሐሰት፡ በመንፈስና በብርሃን በመቃወሙ ነው።

ሐሰተኛው "ኢትዮጵያዊነት"፡ ከእውነተኛው፡ ተለይቶ የሚታወቀው፡ በተቃራኒ ገጽታው ነው፥ ይኸውም፡ "ሐሰተኛው"፡ የዲያብሎስን ሐሰት በመውደዱና ስለእርሱ፡ በጨለማም፡ በይፋም በመመስከሩ፥ የእግዚአብሔርንም እውነት በመጥላቱና እርሷን፡ በጨለማም፥ በይፋም በመቃወሙ ነው።

በዚህ ምክንያት፡ አንድ ሰው፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱን፡ ለራሱም፥ ለሌላውም፥ ለፈጣሪውም የሚያረጋግጠው፡ ከእውነት ለመድረስ፡ ቀናተኛ፥ ደፋርና ቆራጥ ብቻ ሳይኾን፡ በዚህ ውሳኔው፡ ጨካኝም መኾኑን፡ በምግባሩ ጭምር የሚያሳይና በብርሃን የሚመሰክር ሲኾን ነው።

ይህን ተግባሩን ለመፈጸም፡ "እውነት" የኾነው፡ ራሱ እግዚአብሔር፡ ከእርሱ ጋር እንደሚኾን ስለሚያምን፡ ማንንም፥ ምንንም አይፈራም። "ስለኢትዮጵያዊነት"፡ ከእውነቱ ለመድረስ፡ ለአንድ ሰው፡ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ወገን፡ ይህን የመሰለውን አቋም ይዞ የሚገኝ ሊኾን ይገባል።

የዛሬው ትውልድ ግን፡ ባለመታደል፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ባሕርይ፡ የተቃራኒው ክፉ ገጽታ መገለጫ ኾኖ እስኪታይ ድረስ፡ ለውርደትና ለውድቀት ተዳርጎ ይገኛል፤ ይኸውም፡ ከብዙዎቹ፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ባሕርይ መታወቂያ ምልክቶች መካከል፡ ጎልተው ከሚገኙት፡ "ከእውነተኛነት፥ ከታማኝነትና ከጀግንነት" ጸጋ ተራቁቶ፡ "የሐሰተኛነትን፥ የከሃዲነትንና የፈሪነትን" ክል ተላብሶ የሚታይ በመኾኑ ነው።

ስለዚህ፡ "ስለ'ኢትዮጵያዊነት'፡ እውነቱን ለማወቅ፡ ከልቡ ፈልጎ፡ 'ኢትዮጵያዊነት ምንድር ነው?' የሚለውን ጥያቄ ሳይፈራ፡ በይፋ ቀርቶ፡ በግል የሚጠይቅ አለወይ?" ለሚለው ተራ ጥያቄ እንኳ፡ "አዎን! ይኸው፡ እኔ አለሁ!" ብሎ፡ ራሱን፡ ከፈሪዎቹ መካከል፡ በመንፈሳዊ ቅንዓት፡ ብቅ የሚያደርግ፡ እውነተኛና ታማኝ፥ ደፋርና ጀግና ኢትዮጵያዊ እንዳለ ሊዳሰስ፥ ተገቢውንም ምላሽ ሊሰጥ፡ እነሆ፡ ይህ ውይይት፡ "ማሰናከያና እንደገና መፋረጃ" ኾኖ ቀርቧል።

ይህ ትውልድ፡
ኢትዮጵያዊዉን መልእክት ለመቀበል ያለበት ችግር።

ጥያቄ፡- ስለ"ኢትዮጵያ" እና "ኢትዮጵያዊነት"፡ እኛንና ይህን ትውልድ ልታሳውቀን በምታደርገው ጥረትህ አንጻር፡ የሚደነቀሩ፡ እስካሹን ከተጠቃቀሱት ጋር፡ ሌሎችም ችግሮች እንዳሉ፡ በእየጎሊናችን ይሰማናል፤ ፈቀድህ ቢኾን፡ ከእነዚህ መካከል፡ ቀዳሚ ኾኖ የሚገኘውን እንግለጽልህ! ይኸውም፡ የእኛ ትውልድ፡ አእምሮው፡ በዘመናዊው የምዕራባውያን ትምህርት የታነጸ ስለኾነ፡ የሚቀርብለትን ማናቸውንም ሐተታ፡ አዳምጦና በቀላሉ አምኖ ሊቀበል የሚችለው፡ በተለይ፡ ባዕዳን ምሁራንና ሊቃውንት፥ አለዚያ፡ የራሱ ወገኖች ከኾኑ ደግሞ፡ ከእነርሱው፡ ከባዕዳኑ ተምረው፥ ለእነርሱው የማዕርግ ስጦታ በቅተውና በእነርሱው ተመርቀው የወጡት፡ የሚነግሩትን ብቻ መኾኑ ነው።

ምዕራፍ ፪፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፡ ይህ ትውልድ፡ ኢትዮጵያዊዉን መልእክት ለመቀበል ያለበት ችግር።

ትውልዱ፡ የሚቀርብለት ሐተታ፡ በጽሑፍ ከሆነም፡ ያንኑ ሊያነብበውና አምኖ ሊቀበለው የሚፈቅደው፡ እነዚያው ባዕዳኑ ያዘጋጇቸውን መጻሕፍት፡ አለዚያ፡ የራሱ ወገኖች ከሆኑ ደግሞ፡ የባዕዳኑን መጻሕፍት፡ ዋቢ አድርገው እየጠቀሱ የሚያቀርቡለትን ጽሑፍ ብቻ ነው፤ የባዕዳኑ የትምህርት ማዕረግ የሌለውን ግን፡ የራሱንም ወገን አንኳ ቢሆን፡ ንግግሩንም ሆነ ጽሑፉን፡ አምኖ ሊቀበለው ቀርቶ፡ ሊሰማውም እንኳ አይፈልግም።

ታዲያ፡ በዚህ ረገድ፡ ያለውን ችግር ተገንዝበሀ፡ በአንተ በኩል፡ ስላቀራረብህ ያደረግኸው ጥናትና ጥንቃቄ አለወይ?

መልስ፡- እውነተኛውንና ተገቢውን መልስ፡ በማያዳግም መልክ፡ እንደኛዬን አሰባችሁ ዘንድ፡ ጥያቄያችሁን፡ ግልጽና ቀጥተኛ ብታደርጉልኝ እወድዳለሁ።

ጥያቄ፡- *እንዳልኸው፡ ጥያቄያችንን፡ እንዲህ በሚል ቃል ግልጽና ቀጥተኛ እናድርግልህ! ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን በሚመለከተው ጉዳይ ላይ፡ አስካኹን የገለጽህልንና ወደፊት የምታቀርብልን ሐተታዎች፡ የሰጠኸንና ወደፊት የምትሰጠን ማብራሪያዎችም፡ እንደዘመናዊው ሥጋዊ አሠራር፡ በተጨባጭ ማስረጃና በግዙፍ ምስክር የተደገፉ ናቸው ወይ? ለእነዚህም ኹሉ፡ ዋቢ አድርገህ የምትጠቀስልን መጻሕፍት አሉወይ? እነርሱስ የትኞቹ ናቸው? አንተም፡ በትውልዱ ዘንድ፡ ተደማጭነት ይኖርህ ዘንድ፡ ተቀባይነትንም ታገኝ ዘንድ፡ በአገራዊው ሆነ፡ በባዕዳኑ ዘመናዊ ትምህርት ተመርቀህ፡ ለምሁርነት የበቃህበት ማዕረግ፡ አስከምን የደረሰ ነው?*

መልስ፡- ለዚህ ውይይታችን መነሻ ኾኖን፡ እነሆ፡ እየተነጋገርንበት ያለው፡ ይህ፡ የ"ኢትዮጵያ" እና የ"ኢትዮጵያዊነት" ጉዳይ፡ ምሥጢሩ፡ በትውልዱ ዘንድ እንዳይታወቅ ያደረገው ጠንቀኛው ምክንያት፡ ለዚህ ጥያቄያችሁ ምላሽ የኾነው ቁም ነገር ስለኾነ፡ ጥያቄውን ማቅረባችሁ፡ እጅግ የተገባና የሚያስፈልግ ነው፡ እናንተንም፡ "ተባረኩ!" ያሰኛችኋል። ቁም ነገር ላለው፡ ለዚሁ ጥያቄያችሁ፡ የምሰጣችሁን መልስ፡ እንግዲህ፡ በማስተዋል ተመልከቱት!

ዳኛ፡ የ"ኢትዮጵያ" እና የ"ኢትዮጵያዊነት" ነገር፡ ምሥጢሩና ትርጉሙ፡ በእግዚአብሔር መንፈስ፡ በረቂቁ ሰብአዊ የልብ ሰሌዳ ላይ የተጻፈ ስለኾነ፡ የኹለቱንም እውነተኛ መልክ ለማሳየትና ለማሳወቅ፡ ለማየትና ለማወቅም፡ ሥጋዊ ለኾነው ነገር የሚደረገውን የመሰለ ዝግጅትና አሠራር ከቶ አያስፈልገውም፡ ምክንያቱም፡ በሰውኛ ሥርዓት የሚገለጽና የሚታወቅ፡ የሚማሩትና የሚያስተምሩት፡ የሚጠናና የሚዘጋጅ፡ የሚቀርብና የሚወሰድ ባለመኾኑ ነው። ዛሬ እንኳን አታዩትም?! የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጉዳይ፡ ከሥጋው ዐይኑ የትምህርትና የሥነ እውቀት ሊቃውንት ትንታኔና ትንበያ ውጭ በኾነ ኃይል፡ የሕያውነት ህልውናው እየቀጠለ ሲኼድ?!

"ሕዝቧ፡ እርስ በርሳቸው ተፋጅተው ያልቃሉ፡ እርሷም ትጠፋለች!" ያሏት አገር፡ እስካኹን ሳትጠፋ ሲያገኟት፡ ዓለማውያኑ ባዕዳን ሊቃውንት፡ "የዚች አገር ነገር፡ ምሥጢሩ ምንድር ነው?" ብለው፡ እያመነቱ ግራ እስኪገባቸው ድረስ፡ እንዴት፡ እንደሚገረሙ፡ አትመለከቱምን? እነርሱ፡ ኢትዮጵያን የሚያዩበት ዓይን፡ እግዚአብሔርና የእርሱ የኾኑት ሰዎች፡ እርሷን ከሚያዩበት ዓይን፡ ፈጽሞ የተለየ ስለኾነ ነው።

እነርሱ፡ "በምድር አህጉር መካከል፡ የመጨረሻዋ ደሀ!" የሚል ውሳኔያቸውን፡ በእርሷ ላይ ያወጁት፡ በእነርሱ ዘንድ፡ "ማንነት" የሚመዘነው፥ "ምንነት"ም የሚለካው፡ በሥጋዊውና በምድራዊው የሀብት፡ የጥበብና የኃይል ይዞታ መጠን በመኾኑ አይደለምን? ነገር ግን፡ ኢትዮጵያውያን ልጆቿ፡ "መንፈሳዊዉና ሰማያዊው ሀብት፥ ጥበብና ኃይል ይበልጣል!" ብለው፡ ይህን የመሰለውን፡ ሥጋዊና ምድራዊ ሀብት፥ ጥበብና ኃይል፡ ከጥንት ጀምረው፡ ንቀውት፥ በገዛ ፈቃዳቸውም፡ ትተዉት ኖረዋል፤ ይኸውም፡ መብሉን፡ "አንበላውም!" ብለው፡ በ"ጸም"፥ ተድላውንም፡ "አንፈልገውም" ብለው፡ በ"ትሕርምት" በሚፈጽሙት ሃይማኖታዊ ምግባራቸው ተረጋግጧል።

ኢትዮጵያውያን፡ የራሳቸው የኾነውን፥ በመንፈሳዊዉና በሰማያዊው ሀብት፥ ጥበብና ኃይል ላይ የተመሠረተውንም ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ ጠብቀውና አክብረው ሲገኙ፡ ከዓለም ሕዝቦች ኹሉ በልጠውና ቀድመው፡ የላቀውን ደረጃ ይይዛሉ፤ ባሮሩ፡ ቀዳሚነታቸውንና ጥንታዊነታቸውን ያጸናሉ። ነገር ግን፡ ይህን የመሰለውን ኢትዮጵያዊነታቸውን፡ አቅልለውና ክደው፡ የባዕዳን የኾነውን፡ ሥጋዊዉንና ምድራዊዉን ሀብት፥ ጥበብና ኃይል፡ በሚከተሉበት ጊዜ፡ ከዓለም ሕዝቦች ኹሉ አንሰውና ተዋርደው፡ *"ፊተኞች፡ ኋለኞች ይኾናሉ!"* የሚለው ጽዋ፡ ዕድል ፋንታቸው ይኾናል። ይህም ማለት፡ እነርሱ፡ ከዓለም ሕዝቦች መካከል፡ "የመጨረሻዎቹ ደሆች"፥ አገራቸውም፡ በምድር አህጉር መካከል፡ "የመጨረሻዋ ደሀ!" የሚለው፡ የባዕዳኑ ባላንጣዎች ዘለፋ የሚጸናባቸው ይኾናሉ። ይህን እውነታ፡ በበለጠ ግልጽ ላድርግላችሁ! ማንኛውም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚል ሰው፡ "እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት" ይዞ በሚገኝበትና በማይገኝበት ጊዜያት፡ የሚሰማው ስሜትና የሚኖረው ዕድል፡ አንድ ዓይነት አይደለም፤ ይኸውም እንዲህ ነው፡-

<u>"እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት" ይዞ በሚገኝበት ጊዜ፡ በዓለም ላይና በዓለም ሕዝቦች መካከል፡ የቀዳሚነትና የበላይነት፥ የአዋቂነትና የባለጸጋነት፥ የፍቅርና የጨዋነት፥ የጀግንነትና የልበ ሙሉነት፥ የኃላፊነትና የታማኝነት፥ የባለአደራነትና የጽኑነት ስሜት ይሰማዋል፤ ከባ የሚሰጠውም የክብር ቦታ፡ ይኸው ይኾናል፤ ይህም የሚኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን መሠረት፡ መልካሙ የእግዚአብሔር የእውነት መንፈስ፡ በዚህ ኢትዮጵያዊ ላይ ስለሚያድርበት ነው።</u>

<u>"እውነተኛውን ኢትዮጵያዊነት" በሚተውበት ጊዜ ደግሞ፡ የሚደርስበትን ተመልከቱት!</u>

ምዕራፍ ፪፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፡ ይህ ትውልድ፡ ኢትዮጵያዊዉን መልእክት ለመቀበል ያለበት ችግር።

ተቃራኒውና ክፉው የዲያብሎስ የሐሰት መንፈስ ይዋሓደውና፡ ስሜቱ፥ የሚወድቅበት የውርደት ደረጃውም፡ ያው፡ መጨረሻነትና ዝቅተኛነት፥ ድንቍርናና ድህነት፥ ምቀኝነትና ነውረኝነት፥ ፈሪነትና ስስት፥ አጥፊነትና ቅሌት፥ ከሃዲነትና ቅጥፈት፥ አድርባይነትና ተገዢነት ይኾናል፤ በዛሬው ትውልድ ላይ ደርሶ እንደሚታየው ማለት ነው።

፪ኛ፡ የ"ኢትዮጵያ" እና የ"ኢትዮጵያዊነት" ዝክረ ነገር፥ ዝርዝር ሓተታውም ተጽፎና ተመዝግቦ ያለው፡ በግእዝ[፬] ቋንቋችንና በብራና መጻሕፍታችን መኾኑን፡ ዅሉም ያውቀዋል።

የዘመኑ የኢትዮጵያ ትውልድ ደግሞ፡ የግእዝን ቋንቋ እንዳይማርና እንዳያውቅ፡ ከዚህ የተነሣም፡ የብራና መጽሓፎቻችንን፡ እንዳይፈልጋቸው ተደርጓል፤ ምናልባት፡ ሊመለከታቸው የሚፈልግ፡ ቀናተኛ ኢትዮጵያዊ ቢኖር እንኳ፡ በቀላሉ ሊደርስባቸውና ሊያገኛቸው እንዳይችል፡ በእየሰበካ ቤተ ክርስቲያኑ፥ በእየአድባራቱና በእየገዳማቱ ዕቃ ቤቶች ውስጥ፡ በሣጥን ተቆልፎባቸው፡ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። ይህ ድርጊት፡ እርግጥ፡ ክቡራን ቅርሶቻችን የኾኑትን መጻሕፍት፡ ከሠራቂው ሌባ፥ ከወንበዴው ዘራፊና ከወራሪው ጠላት ለማዳን የጠቀመ ተገቢ ጥንቃቄ ቢኾንም፡ የዚሁ ድርጊት ጠንቅ፡ የእግዚአብሔር እውነትና ሥራ ተቃዋሚ ለኾነው፡ ለዲያብሎስና የእርሱ መሣሪያዎች ለኾኑ የአገር ተወላጆች፡ ለታወቁትም፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ተጻራሪዎች፡ ምን ያህል እንደረዳ ልትገነዘቡት ይገባል።

ይህን አባባሌን፡ እኔ ለማስገንዘብ የሚከብደኝ፥ እናንተም ለመገንዘብ፡ የሚከብዳችሁ አይደለም። በአንድ በኩል፡ ግእዝ የተማረና ያወቀ ኢትዮጵያዊ፡ በጎብረተሰቡ ዘንድ የተዋረደ፥ ሙያው የተናቀና አገልግሎቱ፡ በገንዘብ ጥቅም ሲመዘን፡ ዋጋ የሌለው ኾኖ መታየቱን፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ የባዕድ ቋንቋ የተማረውና ያወቀው ግን፡ በጎብረተሰቡ ዘንድ የተከበረ፥ ሙያው፡ የተወደደና በገንዘብ ረገድ፡ ከፍተኛ ጥቅምን የሚያስገኝ ኾኖ መገኘቱን፡ ይኸው፡ እየራሳችሁም ትመለከቱታላችሁ። ይህን ዅኔታ፡ ባለፉት ድርሰቶቼ፡ በሚበቃ የተቸሁበት ስለኾነ፡ እዚህ ላይ፡ ከዚህ ያለፈ ሓተታ ልሰጥበት የሚያስፈልግ አይኾንም።

፫ኛ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ የእግዚአብሔር ኾነው፥ ከእግዚአብሔር ወጥተው፥ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ለእግዚአብሔር ወገኖች የተሰጡ ጸጋዎች ስለኾኑ፡ ህልውናቸው ከታወቀበት፡ ከፍጥረት መጀመሪያ ጊዜ አንሥቶ፡ እስከዛሬ ድረስ፥ ወደፊትም፡ በሰውኛው ላይ ኾን፡ በእግዚአብሔር የአሠራር ሥርዓት የሚገለጹና የሚታወቁ፥ የሚያስተምሩዋቸውና የሚማሩዋቸው፥ የሚያሳውቋቸውና የሚያውቋቸው፡ የሚታደሏቸውና የሚቀበሏቸው ናቸው። የሰውኛው አሠራርና ሥርዓት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ዘንድ፡ ቦታ የለውም። ይህም፡ እርግጥ መኾኑ፡ *"ሕዜን በልቡናቸው አኖራለሁ፥ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። ...ኢያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፥ ኢያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ ኢያስተምርም፥ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ዅሉ ያውቁኛልና!"*

ደግሞም፡ "ልጆችሽም ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ፡" የሚለውን የነቢያትን ቃል በመጥቀስ፡ እውነተኛው መምህርና ምሁር ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "'ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ!' ተብሎ፡ በነቢያት ተጽፏል፡ እንግዲህ፡ ከአብ የሰማ፡ የተማረም ኹሉ፡ ወደእኔ ይመጣል፡"[፴፭] ሲል በተናገረው ቃሉ ይታወቃል።

ይህን የመሰለውን እውነት ስለገለጸው አምላክ፡ በዘመኑ የነበሩት ተቃዋሚዎቹ፡ የአይሁድ ሊቃነ ካህናት፡ የሕግ አዋቂዎችና ምሁራኑ ሊቃውንት፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን፡ ምን ይሉት እንደነበረ፡ እርሱም፡ ምን ምላሽ ይሰጣቸው እንደነበረ፡ ደግሞ ስሙ!

"ኢየሱስ፡ ወደመቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር፡ አይሁድም፡ 'ይህ ሰው ሳይማር፡ መጻሕፍትን፡ እንዴት ያውቃል?' ብለው ይደነቁ ነበር። ስለዚህ፡ ኢየሱስ፡ መለሰ፡ እንዲህም አላቸው፡ 'ትምህርቴስ፡ ከላከኝ ነው እንጂ፡ ከእኔ ሊያደለም፡ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፡ እርሱ፡ ይህ ትምህርት፡ ከእግዚአብሔር ቢኾን፡ ወይም እኔ፡ ከእራሴ የምናገር ብኾን፡ ያውቃል።'" ከዚህ ኢያይዘም፡ "እናንተ፡ በመጻሕፍት፡ የዘለዓለም ሕይወት ልንዳላችሁ ይመስላችኋልና፡ እነርሱን ትመረምራላችሁ፡ እነርሱም፡ ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው። ነገር ግን፡ ሕይወት እንዲኾንላችሁ፡ ወደእኔ ልትመጡ አትወድዱም። ...እኔ፡ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፡ የሚከሳችሁ አለ፡ እርሱም፡ ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው፡ ሙሴንስ ብታምኑት፡ እኔን ባመናችሁ ነበር፡ እርሱ፡ ስለእኔ ጽፏልና። መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን፡ ቃሌን፡ እንዴት ታምናላችሁ?"[፴፮]

ይህን ርእስ በሚመለከት፡ የቅዱስ ኪዳን የመጨረሻ ማጎተም ስለኾነው፡ ስለሰባተኛው የምሕረት ቃል ኪዳን ፊጻሚ፡ ስለኢየሱስ ክርስቶስ፡ በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል እንጂ፡ ከእርሱ በፊት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከእርሱና እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ድረስ፡ የነበሩት የስድስቱ ቃል ኪዳናት ተዋዋዮች፡ ኹሉም፡ ከእግዚአብሔር የተማሩ እንጂ፡ አንዳቸውም፡ በመጻሕፍት አዋቂነት፡ በምሁርነትና በሊቅነት የተጠሩ አልነበሩም። የእግዚአብሔርን ትምህርት፡ ለዓለሙ እንዲያዳርሱለት ለመረጣቸው ደቀ መዛሙርቱ እንኳ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገና በሕይወቱ ሥጋ እያለ፡ ሰጥቷቸው የነበረው መመሪያ፡ እንዲህ ይነበባል፡ "እነሆ፡ እኔ፡ እንደበጎች፡ በተኵላዎች መካከል እልካችኋለሁ፡ ...ከሰዎች ተጠበቁ! ለአገረሱና ለአሕዛብ፡ ምስክር እንዲኾን፡ ስለእኔ፡ ወደገዢዎች፡ ወደነገሥታትም ትመሰዳላችሁ። አሳልፈውም ሲሰጧችሁ፡ የምትናገሩት፡ በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና፡ እንዴት፡ ወይስ ምን፡ እንድትናገሩ አትጨነቁ! በእናንተ የሚናገር፡ የአባታችሁ መንፈስ ነውና እንጂ፡ የምትናገሩ፡ እናንተ አይደላችሁምና።"[፴፯]

መንፈስ ቅዱስ የወረደላቸው ሐዋርያት፡ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አደባባይ ማስተማር እንደጀመሩ፡ ተከሰሰው፡ በአይሁድ ሊቃነ ካህናትና የሕዝብ አለቆች፡ ሸማግሌዎችና ጻፎች ፊት ቀርበው ሲጠየቁ፡ የኾነው ነገር፡ ይህንኑ ያረጋግጣል።

ይኸውም፡ *"ጴጥሮስ፡ መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ፡"* መልሱን ስለሰጣቸው፡ ከሳሾቻቸውና ፈራጆቹ፡ ስለሓዋርያት ሲናገሩ፡ *<u>መጽሐፍን የሚያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ ኾኑ አስተውለው፡ አደነቁ።።"</u>* ማለታቸው ተመዝግቦ መገኘቱ ነው። ደግሞም፡ *"ጠርተው፡ በኢየሱስ ስም፡ ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው።* ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው፡ *'እግዚአብሔርን' ከመሰማት ይልቅ፡ እናንተን እንሰማ ዘንድ፡ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ኾነ፡ ፍረዱ! እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም፤' አሏቸው።።"* ቀጥሎም፡ *"ሰውን፡ ወይስ እግዚአብሔርን፡ አኹን፡ 'እሺ!' አሰኛለሁን? ወይም፡ ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አኹን ሰውን ደስ ባሰኝ፡ የክርስቶስ ባርያ አልኾንሁም።* ወንድሞች ሆይ! በእኔ የተሰበከ ወንጌል፡ እንደሰው እንዳይደለ፡ አስታውቃችኋለሁ፤ *<u>ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ፡ እኔ፡ ከሰው አልተቀበልሁትም፤ አልተማርሁትምም።።"</u>*[፵፩] ሲል፡ ቅዱስ ጳውሎስ፡ ስለራሱ የጻፈውንስ፡ እንዴት አድርጋችሁ ነው የምትተረጉሙት?

እግዚአብሔር፡ ከዚህ ኹሉ ቀደም ብሉ፡ ገና፡ በዘመነ ብሉይ፡ ለነቢይነት ለጠራው፡ አንድ ትንሽ ልጅ፡ የተናገረውን፡ እንዲህ የሚለውን ቃሉን፡ ደግሞ ሳሰማችሁ!

"የእግዚአብሔር ቃል፡ ወደእኔ፡ እንዲህ ሲል መጣ፤" 'በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፤ ከእናትህ ማሕፀን ሳትወጣም ቀድሼሃለሁ፤ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ። እኔም፡- *'ወዮ ጌታ እግዚአብሔር! እነሆ ብላቴና (ትንሽ ልጅ) ነኝና፡ እናገር ዘንድ አላውቅም!' አልሁ።* እግዚአብሔር ግን፡ *እንዲህ አለኝ፡- 'ወደምሰድድህ ኹሉ ዘንድ፡ ትኼዳለህ፤ የማዝዘህንም ኹሉ፡ ትናገራለህና፡ "ብላቴና ነኝ!" አትበል።* እኔ፡ *አድንህ ዘንድ፡ ከአንተ ጋር ነኝና፡ ከፊታቸው አትፍራ!'* ይላል እግዚአብሔር። እግዚአብሔርም፡ *እጁን ዘርግቶ፡ አፌን ዳሰሰ፡ አለኝም፡- 'እነሆ፡ ቃሌን፡ በአፍህ ውስጥ አትሬአለሁ፤ እነሆ፡ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ፥ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ፥ ትሠራና ትተክል ዘንድ፡ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ፡ ዛሬ አድርጌሃለሁ።።"*[፵፪]

እንግዲህ፡ የእግዚአብሔርን ትምህርትና እውቀት ለመማርና ለማስተማር፥ ለማወቅና ለማሳወቅ፡ የሚያስፈልገው ብቅዓት ምን እንደኾነ፡ እነዚህ፡ አኹን የጠቃቀስሁላችሁ፡ የእግዚአብሔር ቃላት፡ በሚበቃ ይገልጡላችኋል። ከዚያ ብቅዓት ለመድረስ፡ በሰው በኩል የሚያስፈልገው ነገር፡ ንጹሕ እውነተኛነትን፡ በውስጥም፥ በውጭም፡ ይዞ መገኘት ብቻ ነው። እንዲያ ሲኾን፡ እግዚአብሔር፡ በዚያ እውነተኛ ሰውነት ውስጥ፡ ቅዱስ መንፈሱን ስለሚያሳድር፡ ያ ሰው፡ ከእግዚአብሔር የተማረና ያወቀ ይኾናል፤ የእግዚአብሔርንም መልእክት ሊያደርስ፥ ትምህርቱን፡ ሊያስተምርና እውቀቱን ሊያሳውቅ የሚችል ይኾናል። መንፈሳዊውና ሰማያዊው የእግዚአብሔር ትምህርት፥ እውቀትና መልእክት፡ እንደሥጋዊዉና ምድራዊው ትምህርት፥ እውቀትና መልእክት፡ የሰው ኃይልና የንብረት ዝግጅት፥ የገንዘብ ዓቅምና የጊዜ ርዝመት አያስፈልገውም። የምታስፈልገው፡ ያች፡ በንስሓ፡ ንጽሕት የኾነች፡ እውነተኛ ልቦና ብቻ ናት።

ከዚያ በኋላ፡ በእርሷ አድሮ የሚናገር÷ የሚያስተምርና የሚሠራ፡ 'የእውነት መንፈስ'÷ 'መንፈስ ቅዱስ' የምንለው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው እንጂ፡ ያ ሰው፡ በሥጋዊው አእምሮው ብቻ አስቦ የሚናገረውና የሚያደርገው አይደለም፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ገና፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ *'እውነት፡ እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፤'*[ፍ፱] ያለው እኮ፡ በዚያ ሰው ላይ፡ በመንፈስ ቅዱስ አድሮ የሚሠራው፡ ራሱ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ፡ ያ ሰው አለመኾኑን፡ አረጋግጦ ለማመልከት መኾኑን ልትገነዘቡት ያስፈልጋል። ደካማው፤ አላዋቂው ሰውማ፡ እንዴት፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሊልቅና የሚበልጠውን ሥራ ሊያደርግ ይችላል? ይህ እውነታ፡ በራሱ ሕይወት ተከሥቶ የታየበት፡ አንዱ፡ ሐዋርያ ሲጽፍ፡- *'ለፍጥረታዊ* (ማለትም፡ ለሥጋዊና ዓለማዊ) *ሰው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ ምንኛት ነውና፡ አይቀበለውም፥ በመንፈስም፡ የሚመረመር ስለኾነ፡ ሊያውቀው አይችልም። መንፈሳዊ* (ማለትም፡ ከእግዚአብሔር የተማረ) *ሰው ግን፡ ሹሉን ይመረምራል፡ ራሱ ግን፡ በማንም አይመረመርም። እንዲያስተምረው፡ የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን፡ የክርስቶስ ልብ አለን።'*[ፍ፲] ያለው ቃል፡ ከእግዚአብሔር ስለተማረና ስላወቀ ሰው ምንነትና ማንነት አስረድቷል።

በዚህ መሠረት፡ የእግዚአብሔር ትምህርት የምትገልጠውን እውነት፡ ለማረጋገጥና ለማመን፡ ሰዎች፡ የሚጠራጠሩ ከኾኑ÷ ወይም፡ ለማመን ቢያቅታቸው፡ ለየራሳቸው ምስክርና ማስረጃ ሊፈልጉ ይገባቸዋል እንጂ፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ ራሷን፡ በራሷ አረጋግጣ ከመግለጥ በቀር፡ ሌላ ምስክር፡ ሌላ ማስረጃ ከቶ አታቀርብም። እነርሱም የሚያደርጉት የምርምራቸውና የጥናታቸው ውጤት፡ የሚመሰክረውና የሚያስረዳው፡ ያንኑ የእግዚአብሔር እውነትነቷን ኾኖ ይገኛል። ይህንኑም፡ እስካኹን፡ በኢትዮጵያም፡ በዓለሙም፡ በኾነውና እየኾነ በምታዩት ኹሉ ተገንዝባችሁታል ይመስለኛል።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን፡ እስከዛሬ፡ በዓለም ላይና በሕዝቦች መካከል፡ እንዲህ፡ ስመጥርና ገናና አድርጎ፡ በተቃዋሚዎቻቸውና በተጻራሪዎቻቸው ዘንድ ሳይቀር፡ በበጎ ገጽታ የሚያስነሣቸው፡ ይኸው፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ጸጋ የተገኘው መልካም ስምና ዝና ብቻ እንጂ፡ ሌላማ፡ ምን የሚጠቀስ፡ ደህና ነገር፡ ወይም፡ የሚቀርብ፡ ሌላ ምን ሀብት አለ? ምንም የለንም። እንደዚሁ ኹሉ፡ ከጥንት ጀምረው፡ እስከዛሬ፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነት፡ በግእዝ ብቻ ሳይኾን፡ በባዕዳን ቋንቋዎች ጭምር የተጻፉትን መጻሕፍት ኹሉ ያዘጋጁ፡ የአገራችንም ኾኑ የውጭ አገሮች ምሁራንና ሊቃውንት ጸሓፊዎች፡ የቱንም ያህል፡ በሌላ ዓላማ ተነሣሥተው የሚጽፉ ቢኾኑም እንኳ፡ በመጨረሻ ዞረው ዞረው የሚደመድሙት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ስለተመሠረቱት፡ ስለእነዚሁ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መኾኑን፡ ወደፊት እናንተም፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ፡ ይህን ጋሻ አንሥታችሁ፡ ጥናታችሁንና ምርምራችሁን በምታካኼዱት ጊዜ፡ ከእውነታው ትደርሱበታላችሁ።

"ይህ ሕዝብ፡ በከንፈሩ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን፡ ከእኔ፡ በጣም የራቀ ነው፣ የሰውም ሥርዓት እያስተማሩ፡ በከንቱ ያመልኩኛል!"[፴፩] ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ በነቢዩ አንደበት፡ አስቀድሞ፡ አስተላልፎት የነበረውን ዘለፋና ተግሣፅ፡ ራሱ፡ ጌታችንም፡ በዘመኑ ለነበረውና ለተከታታዩ ትውልዶች ጠቃቅሶታል። አዎን! በሰዎች ሥርዓት ላይ የተመሠረተው፡ የሰዎች ትምህርት ሲለዋወጥና ሲጠፋ፥ ፈጣሪዎቹንም ሳይቀር ሲያጠፋ፥ የእግዚአብሔር ትምህርት ግን፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ሹሉ፡ የቱን ያህል ጠቀሜታነትና ዘለቂታነት ያለው ኾኖ እንደቀጠለ፡ እንመለከታለን።

ስለዚህ፡ የእግዚአብሔር ሥራዎችና ምሥጢራት፥ ጸጋዎቹም ስለኾኑት፡ ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፡ ለማወቅና ለማሳወቅ፥ ለመማርና ለማስተማር፡ የሰዎች ሥጋዊና ዓለማዊ ትምህርት፥ ማዕርጉም፡ ለማነኛውም ለብአዊ ፍጡር አያስፈልገውም። ለእኔም፡ በዚሁ፡ የእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር፥ ለእግዚአብሔርም በኾነው ተልእኮ ለተጠመድሁት ኢትዮጵያዊ፡ ያ፡ የሰዎች ሥጋዊና ዓለማዊ ትምህርት፥ ማዕርጉም፡ አላስፈለገኝም፣ አያስፈልገኝምም።

እንዲያማ ባይኾን ኖሮ፥ ወይም፡ መልእክቱን፡ የሰዎች በኾነው፡ በሥጋዊው ትምህርቱና ማዕርጌ ተጠቅሜ ያቀረብሁት ቢኾን ኖሮ፡ መልእክቱ፡ የእግዚአብሔር መኾኑ ቀርቶ፡ የሰው በኾነ ነበር፣ ያ ደግሞ፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያዊነት ሊኾን ከቶ አይችልም።

ይህ ርእስ ከተነሣ ዘንድ፡ ስለእግዚአብሔር ማስተማርና ስለሰዎች ትምህርት ልዩነት፡ የኋላ ኋላ ለተገነዘብሁት እውነታ ማረጋገጫ የኾነኝን፡ ገና በሕፃንነቱ ያሳየሁትን ድርጊት፡ ወላጆቼ ሲጨዋወቱት እንደሰማሁት ላውጋችሁ፦ ዕድሜዬ፡ ለትምህርት እንደደረሰ፡ ፊደል መቍጠር እጀምር ዘንድ፡ በሰበካችን ቤተ ክርስቲያን በሚገኘው ትምህርት ቤት፡ ከታላላቅ ወንድሞቼ ጋር እየኼድሁ እንድውል፡ ወላጆቼ ወሰኑ፡ በውሳኔው መሠረት እንድፈጽም፡ መጀመሪያ ወንድሞቼ፥ ኋላም፡ እናቴ ቢጠይቁኝ፥ ቢያባብሉኝም፡ ፈቃደኛ ባለመኾኔ፡ ሳልኼድ ቀረሁ።

ለአባቴ ሳይነገር የሰነበተው እምቢተኝነቴ፡ ከዕለታት አንድ ቀን ተገለጠ፡ ሊገለጥ የቻለውም፡ አባቴ፡ ከሥልጣነ ክህነቱ ጋር፡ በመንግሥቱ የፍርድ ዘርፍ ውስጥ በዳኝነት ወደሚያገለግልበት ሥራው፡ ዘወትር፡ በጧት፡ ቀድሞ ይወጣ ስለነበረ፡ በዚያን ዕለት ግን፡ እንደአጋጣሚ፡ በቤተ ክርስቲያን በመቆየቱ፡ ወደመደበኛ ሥራው ከመኼድ ዘግይቶ፡ ወደቤት ሲመለስ፡ እኔ፡ ወደትምህርት ቤት ሳልኼድ፡ ከእናቴ ጉያ ተሸጉጬ ስላገኘኝ ነበር።

"እንዴ! ይኼ ልጅ፡ ዛሬ ምነው ወደተማሪ ቤት አልኼደ?" ብሎ፡ አባቴ ተገርሞ ጠየቀ። "መቼ ኼዶ ያውቃል? ሊኼድም አይፈልግምና፡ እስቲ ትንሽ ይቆይ! ሕፃንነቱን ይጨርስ! ተወው!" ስትል፡ እናቴ መልስ ሰጠች። "አይ! አይኾንም፣ ዛሬስ አይቀርም፣ የቆየሁ ቆይቻለሁና፡ እኔው፡ ራሴ አድርሼው እመጣለሁ፣" ብሎ፡ አባቴ አቅፎኝ፡ እንደገና ወደቤተ ክርስቲያኑ ትምህርት ቤት ኼደ፡ ለአስተማሪዬም አስረክቦኝ፥ አበረታትቶኝና ስሞኝ ወደቤት ተመለሰ።

እደጃፍ ቆማ ለነበረችው፡ እናቴም፡ ገና ከግቢው፡ የአጥር በር ዘልቆ እንደገባ፡ "ይኼውልሻ! ዛሬ፡ ብዘገይም፡ አንድ ቁም ነገር ሠራሁ!" ብሎ፡ ወደእርሷ እየቀረበ ሲያነጋግራት፡ እርሷ ግን፡ ዝም ብላ፡ ወደእርሱ አግጣጫ እያየች፡ በማሾፍ፡ ትሥቅ ጀመር። አባቴም፡ በእናቴ ኹኔታ ተደንቆ፡ "ምን መኾንሽ ነው!?" ሲላት፡ ወደጀርባው በዓይኗ እያላየች፡ በእፃ ምልክት ሰጠችው። እርሱም፡ 'ምን ነገር ይኾን!? ብሎ፡ ዘወር ሲል፡ እኔን፡ ድክድክ እያልሁ፡ ከኋላው ስከተለው አገኘኝ።

አባቴ፡ በመቆጣት ሩንታ፡ ከት ብሎ በመሣቅ፡ ከምድር፡ ብድግ አድርጎ አቀፈኝ፡ "ይህን ልጅ፡ ምንም ቢኾን፡ ዛሬ ከተማሪ ቤቱ ሳላደርስ ወደሥራዬ አልኼድም!" እያለ ፎክሮ፡ መንገድ ሲጀምር፡ አንዱ የቅርብ ጎረቤታችን፡ ድንገት ደርሶ፡ "ቆይ! ለእኔ ስጠኝ! እኔ አደርስዋለሁ፡ አንተ፡ ወደሥራህ ኺድ!" ብሎት፡ አባቴ፡ ወደሥራው ሲያቀና፡ ያ፡ ጎረቤታችን፡ እኔን፡ ወደተማሪ ቤቱ 'እንደገና እንኮኮ ብሎ ወሰደኝ። እርሱም፡ በደህና ያደረሰኝ መኾኑን፡ ለእናቴ ሊነግራት፡ እየተቻኮለ ወደቤት ሲመለስ፡ እናቴ፡ የሕፃን ልጇን፡ የእልኸኝነት ጠባይ ያወቀች ይመስል፡ እንደበፊቱ፡ ከደጃፍ ኾና ትጠብቅ ኖሮ፡ አኹንም፡ ከኋላው፡ በትናንሾቹ ባዶ እግሮቹ፡ ድምፄን ሳላሰማ እየሮጥሁ ስከተለው አይታ፡ ተንከተከተች።

በነገሩ ለተደናገጠውና ኋላ ለተገረመው ለዚያ፡ ባለውለተኛ ጎረቤታችንም፡ በአባቴ የኾነው፡ በእርሱም ላይ መደገሙን፡ እናቴ ነግራው፡ በቤትና በጎረቤት፡ ይህን ያየ ኹሉ፡ ሲሣሣቅ ዋለ።

ከዚህ በኋላ፡ "እንግዲህ፡ ራሱ፡ ወደተማሪ ቤቱ ለመኼድ ፈቃደኛ እስኪኾን ድረስ፡ ተዉት!" ተብሎልኝ፡ ከእናቴ ጉያ ዐርፌ ሰነበትሁ። ባሰኘኝ ጊዜ ብቻ፡ ወደተማሪ ቤት እኼድ እንደነበረ፡ እዚያም፡ ቀኖጭ ብዬ ከመማር ይልቅ፡ ከሕፃንነቴ የተነሣ፡ በተማሪዎቹ መካከል እየሮጥሁና እየተጫወትሁ፡ ከፊደል ቆጠራው አንሥቶ፡ ለትልልቆቹ ተማሪዎች እስካስቸገረው ዜማ ድረስ፡ ኹሉንም፡ በእየመልኩ፡ እንደዘበት፡ በጆሮዬ ሰምቼና ተቀብዬ፡ መልሼ በማዜም፡ አስተማሪውን ሳስገርም ዕውል እንደነበረ፡ ወላጆቼ፡ በቤተሰብ መካከል በየጊዜው እያነሡ የሚሣሣቁበት ጨዋታ ትዝ ይለኛል።

ጥያቄ፡- የእግዚአብሔር፡ በእግዚአብሔርና ከእግዚአብሔር ስለኾነው ትምህርትና ስለማዕርጉ፡ ይህን ያህል ከነገርኸን፡ እስኪ፡ በሰብአዊው ትምህርትና ማዕርጉ በኩል ስለደረስህበት ደረጃ፡ ስለመምህራንህም ደግሞ፡ ግለጥልንና የጥያቄያችን መልስ ይጠቀለል?!

መልስ፡- የእግዚአብሔር ስለኾነው ተልእኮ፡ "የሰዎች ሥጋዊና ዓለማዊ ትምህርት፡ ማዕርጉም፡ አያስፈልግም!" ብላችሁም፡ በእኔ በኩል፡ መንፈሳዊዉንና የዘሙኑን ሥጋዊ ትምህርት፡ "አላገኘሁም፡ ወይም የለኝም!" ማለቱ አይደለም፡ ያን ትምህርት፡ በሚበቃ አግኝቻለሁ። እርሱም፡ የኋላ ኋላ፡ በኢትዮጵያዊነቴ፡ ለተያያዝሁት፡ ለመንፈሳዊዉና ለሥጋዊው ሥራዬ አገልግሎኛል።

ይኸው፡ በትምህርት የተገኘው እውቀትና ሙያ፡ በመንፈሳዊው፡ እስከንቡረ እድነት÷ በሥጋዊውም፡ እስከሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባልነት ማዕርግ የደረስሁበትን አገልግሎት፡ ለመፈጸም÷ የድርሰት ሥራዎቼንም ለማበርከት፡ በብዙ ረድቶኛል።

ከሕፃንነቴ ጀምሬ፡ ለሥልጣነ ክህነት እስከበቃሁበት ጊዜ ድረስ ያለውን ዕድሜዬን፡ መንፈሳዊዉን እውቀት እየቀሰምሁበት የቆየሁ ስኾን፡ ከዚያ ጋር በማስተባበር፡ ከቤተ ክህነቱ ተለይቶ፡ በተለይ ወደተቋቋመው፡ ወደቤተ ምልክናው ትምህርት ቤት ገብቼ፡ ዘመናዊዉን የ፩ኛ ደረጃ፡ በአዲስ አበባ፡ የገብረ ማርያም÷ የበየነ መርዕድና የዳግማዊ ምኒልክ÷ የ፪ኛውንም ደረጃ፡ ለአንድ ዓመት፡ በሐረር መምህራን ማሠልጠኛ÷ የቀሩትንም፡ ሦስት ዓመታት፡ እንደገና ወደአዲስ አበባ ተመልሼ፡ በዳግማዊ ምኒልክ፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች አከናወንሁ።

በሥራው ዓለም እያለሁ፡ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መካነ አእምሮ፡ በእንግሊዝኛው ክፍል የተከታተልሁትን የሕግ ባለሙያነት ትምህርት፡ ተመርቄበታለሁ። ዕድሉ በተገኘም ጊዜ፡ በባሕር ማዶ አገሮች ባሉ፡ በታወቁ የባዕዳን መካናተ አእምሮ ውስጥ÷ ለምሳሌ፡ በአሜሪካ፡ የዋሽንግተን ዲሲው ሐዋርድ ዩኒቨርሲቲ፡ ተያይዤው የነበረውንና በናሽቪል ቴኔሲው ቫንደርቢልት ዩኒቨርሲቲ፡ በመጀመር ላይ የነበርሁትን፡ የመጨረሻ ትምህርት፡ ከግብ እንዳላደርስ÷ ከያግጣጫው የገጠሙኝን ደባዎችና እንቅፋቶች፡ በዓይነታቸውና በብዛታቸው ሳስታውሳቸው፡ ይገርመኛል።

የሚገርመኝም፡ ለጥናቴ መነሻ አድርጌ፡ እዘጋጅበት የነበረው፡ የምርምር መስክ፡ የተመሠረተውና ያተኰረው፡ በዚሁ፡ ዛሬ በያዝሁት፡ የእግዚአብሔር እውነት ባስገኘችው፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት አቋም ላይ ስለነበረ÷ ይህን የእምነት አቋም ደግሞ፡ ዲያብሎስና ሰዎች፡ ከባዕዳኑ ብቻ ሳይኾን፡ ከወገኑም ጭምር፡ የማይቀበሉት÷ የሚቃወሙትም ከመኾናቸው የተነሣ፡ ደባዎቹና እንቅፋቶቹ ኹሉ፡ ከየት እንደመነጩ ለማረጋገጥ በመቻሌ ነው።

ይህ በመኾኑም፡ አልተደነቅሁም፤ አላዘንሁምም፤ እንዲያውም፡ ለተከተሉት ደቀ መዛሙርት፡ *"ስለእውነት፡ መከራን የሚቀበሉ፡ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የእነርሱ ናትና። ሲነቅፏችሁና ሲያሳድዷችሁ÷ በእኔም ምክንያት፡ ክፉውን ኹሉ፡ በውሸት ሲናገሩባችሁ፡ ብፁዓን ናችሁ። ዋጋችሁ፡ በሰማያት፡ ታላቅ ነውና፡ ደስ ይበላችሁ! ሐሤትም አድርጉ! ከእናንተ በፊት፡ የነበሩትን ነቢያትን፡ እንዲሁ፡ አሳድደዋቸዋልና።"* ለተቃወሙትም አይሁድ፡ *"ንግግሬን የማታስተውሉ፡ ስለምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው፤ እናንተ፡ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወድዳላችሁ። ...እኔ ግን፡ እውነትን የምናገር ስለኾንሁ፡ አታምኑኝም። ...ከእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ፡ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና፡ ስለዚህ አትሰሙም።"* ያለው፡ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ ትዝ ብሎኝ፡ ሐሤትን አደረግሁ፤ ይ፡ የሰዎች ክፉ ድርጊት፡ ለእኔ፡ የመለኮትን ጸጋና በረከት አስገኝቶልኛልና!

ለሓዋርያቱም፡ "ዓለም ቢጠላችሁ፡ ከእናንተ በፊት፡ እኔን እንደጠላኝ እወቁ! ከዓለምስ ብትሾኑ፡ ዓለም፡ የራሱ የሾነውን ይወድድ ነበር፤ ነገር ግን፡ እኔ፡ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ፡ ከዓለም ስላይደላችሁ፡ ስለዚህ፡ ዓለም ይጠላችኋል።"[፴፭] የሚለው የጌታ ቃል፡ ዛሬም፡ ቢያግጫው፡ በበለጠ፡ ገሃድ ኾኖ እየሠራ መኾኑን፡ በዚያን ጊዜ፡ ለማስተዋል ቻልሁ።

በመጨረሻ፡ "እንዲህ ባይኾን ኖሮ፡ ይኼን ጊዜ፡ የሰዎች ትምህርት በቀረጸው፡ በዚያ አእምሮዬ እየተመራሁ፥ በማዕርጉም እየተመካሁና እየታበይሁ፡ ይህን ዛሬ፡ በዓለሙ ብቻ ሳይኾን፡ በአገራችን ትውልድ ዘንድ ጭምር፡ የተናቀውንና የተጠላውን፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ተልእኮ ላገለግል፡ ሕይወቴንም ልኖረው ባልቻልሁ ነበር፤" ብዬ፡ እግዚአብሔርን፡ በበለጠ አመሰግንሁት።

ስለመምህራኖቼና ስለተማርሁባቸው ትምህርት ቤቶች ላቀረባችሁልኝ ጥያቄ፡ መልሴ፡ ቀደም አድርጌ የገለጽሁላችሁ እውነታ እንዳለ ኾኖ፡ "በቅዱሱ ኪዳን ጸጋና በረከት፡ ለኢትዮጵያዊው፡ መምህሩ፥ አስተማሪው፡ ኢያሱስ ክርስቶስ ነው! ትምህርት ቤቱም፡ ኢትዮጵያ፥ እርሷም፡ ድንግል ማርያም ናት!" የሚል ነው። ይህን፡ አረጋግጩ ስገልጽላችሁ፡ እጅግ ደስ ይለኛል።

በዚህ ጉዳይ ላይ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለው መጽሓፌ፡ በገጽ፡ [illegible]፡ ያተትሁትን ተመልከቱት!

በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሠቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ግዴጅና ጥቅም።

ጥያቄ፡- በዚህ ውይይታችን ውስጥ የቀረቡትን ቁም ነገሮች፡ በእየአእምሮአችን ወስጥ በቀላሉ መዝግበን እንይዛቸው ዘንድ፡ እስኪ፡ ስለእነዚሁ ቁም ነገሮች፡ በመልክ በመልኩ፡ አጭር መግለጫን ስጠን?

መልስ፡- "ኢትዮጵያዊነት"፡ መጀመሪያ፡ "ራስን ማወቅ!"፥ ቀጥሎ፡ "እግዚአብሔርን ማወቅ!" እና በመጨረሻ፡ "የተፈጥሮ ባልንጀራን ማወቅ!" ነው፡ ራሱን የማያውቅ፡ ፈጣሪውን የማያውቅና የተፈጥሮ ወገኑን የማያውቅ ግለሰብ፡ "ኢትዮጵያዊ" ሊባል አይቻልም። ይህን ቋሚ እውነት ለማብራራት፡ ይህ ውይይት፡ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት" የተመሠረቱባቸውን፡ ሦስት ቁም ነገሮችን የያዙ፡ ሦስት ክፍሎች እንዲኖሩት ተደርጓል።

ይኸውም፡-

የመጀመሪያው ክፍል፡ "'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?" የሚል ዓቢይ ርእስ ያለው ሲኾን፡ በውስጡ፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን፡ ንዑሳን አርእስት ይዟል፤ እነዚህም፡ ከሦስቱ የሕይወት ምሥጢራት፡ "ሥነ ፍጥረት"፡ ከሦስቱ፡ የሰውነት አካላት፡ "ነፍስ"፥ ከሦስቱ መንፈሳውያን ኃይላት፡ "ጸም"፡ ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ "ቤተ ሕዝብ" እና ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን መደቦች፡ "ኪዳነ ልቦና" ናቸው።

ምዕራፍ ፪፤
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሠቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ግዴጅና ጥቅም።

ኹለተኛው ክፍል፡ *"'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር ማነው?"* የሚል ርእስ ያለው ሲኾን፡ በውስጡ፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን፡ ንዑሳን አርእስት ይሏል፤ እነዚህም፡ ከሦስቱ የሕይወት ምሥጢራት፡ "ሃይማኖት"፥ ከሦስቱ፡ የሰውነት አካል ክፍሎች፡ "መንፈስ"፥ ከሦስቱ ኃይላት፡ "ጸሎት"፥ ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ "ቤተ ክህነት" እና ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን መደቦች፡ "ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ" ናቸው።

ሦስተኛውም ክፍል፡ *"'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?"* የሚል ርእስ ያለው ሲኾን፡ በውስጡ፡ ከእርሱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን፡ ንዑሳን አርእስት ይሏል፤ እነዚህም፡ ከሦስቱ የሕይወት ምሥጢራት፡ "ምግባር"፥ ከሦስቱ፡ የሰውነት አካል ክፍሎች፡ "ሥጋ"፥ ከሦስቱ ኃይላት፡ "ምጽዋት"፥ ከሦስቱ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘርፎች፡ "ቤተ ምልክና" እና ከሦስቱ፡ የቅዱሱ ኪዳን መደቦች፡ "ኪዳነ አሪት" ናቸው።

ይህን አመዳደብ በመከተል፡ በዚህ፡ ቀዳማዊ ውይይታችን የታቀፈው ርእስ፡ አንዱ ብቻ ነው፤ እርሱም፡ *"'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?"* የሚለው፡ የመጀመሪያው ክፍል ነው። ይህንም ያደረግሁት፡ ሦስቱንም ክፍሎች፡ በአንድ ጥራዝ አጠቃልሎ ማቅረቡ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" በሚለውና ፳፪ ገጾችን ባካተተው መጽሓፌ እንደታየው፥ ያውም፡ ያ መጽሓፍ፡ ፲፩ ቍጥር በኾነው፡ በረቀቀው የፊደል አጥቅ የታተመ ሲኾን፡ በማሳተሚያው በኩል ያለው፡ የዋጋው ከባድነትና የዚህም ጠንቅ፡ በዚያው መጠን ወደአንባቢው ተሳልፎ፡ መጽሓፉን በመግዛቱ ዓቅም ላይ ያስከተለው ችግር ቀላል ባለመኾኑ፡ አኹን፡ ያን ችግር፡ በከፊልም ቢኾን፡ ለመቅረፍ፡ ይህ ዘዴ አስተዋጽዖ ይኖረዋል ብዬ በማሰብ ነው።

ጥያቄ፡- *ከላይ በተጠቀሱት ሦስት አርእስት የተከፋፈለውን፡ ይህን፡ "ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን ውይይት፡ በዚህ መልኩ ያዘጋጀኽው ለምንድር እንደኾነ፡ አያይዘህ ብትገልጽልን?*

መልስ፡- ይህን ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዳዘጋጅ ያስገደዱኝ ምክንያቶች፡ ከዚህ በሚከተሉት ተራ ቁጥሮች ይጠቃለላሉ።

፩ኛ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ አብዛኛው ወገን፡ "ስምንተኛው ሺ"፡ ወይም "አሥርረሽ ምቺው!" የሚባለውን፡ በኖኅ ዘመን የደረሰውን፡ የሚመስል ጥፋት፡ በውኃም ባይኾን፡ በሌላ መልክ፡ ሳይመጣ አይቀርም ተብሎ፡ በትውፊት፡ የሚነገረውን ትንቢት፡ እንደተረት ይቆጥረው ነበር። ምናልባት ቢመጣም፡ ወደፊት፡ በዓለሙ ፍጻሜ እንጂ፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ "ይደርሳል!" ብሎ፡ አልጠረጠረም ነበር። ነገር ግን፡ ሳያስበው፡ ድንገት፡ ታላቅ የፈተና እሳትና የመከራ ማዕበል፡ በ፲፱፻፸፯ ዓ. ም. በአገሩ ላይ ፈንድቶ፡ ኹሉን አጥለቀለቀ፤ ኹሉንም አቃጠለ፤ እኔን ጭምር። ስለዚህ፡ *"ይህ፡ ለምን ኾነ?"* የሚለውን ጥያቄ፡ ወደመሠረቱ ኼጀ መመርመርና መልሱን አግኝቼ፡ በመፍትሔው መጠቀም፡ ኢትዮጵያዊ ግዴታዬ ኾኖ አገኘሁት።

የዚህ ጥያቄዬና ምርምሬ ፍለጋም፡ ማንነቴ ወደታወቀበት፡ ወደ"ኢትዮጵያዊነቴ" መሠረት አደረሰኝ! የፈተናው እሳት መነሻና የመከራው ማዕበል ምክንያት፡ እርሱው ራሱ፡ ማለትም፡ ይኸው "ኢትዮጵያዊነት" ሠኾኑንም አረጋገጠልኝ፤ የእሳቱ ማጥፊያና የማዕበሉ ማርመሚያ (ጸጥ ማድረጊያ)÷ የበሽታው መድኃኒትና የችግሮቹ ኹሉ መፍትሔም፡ ሌላ ሳይኾን፡ ይኸው ራሱ፡ "ኢትዮጵያዊነት" መኾኑንም አስገነዘበኝ::

በዚህ መሠረት፡ "'ኢትዮጵያዊነት'፡ 'ኢትዮጵያውያን ነን!' ለሚሉት ኹሉ፡ በቋሚነት የሚያስተላልፈው፡ ሕያው መልእክት አለው፤ መልእክቱም፡ 'ኢትዮጵያዊነት'፡ ዘለዓለማዊ ህልውና ነው!" በሚል አጭር ቃል ይጀምርና፡ እንዲህ እያለ ይቀጥላል:: "ይህ ህልውና፡ በፈጣሪና 'ኢትዮጵያዊ' በተባለው፡ ሰብአዊ ፍጡር መካከል በተደረገ የስምምነት ቃል ኪዳን ላይ ተመሥርቷል:: የስምምነቱ ቃል ኪዳን፡ በምሕረት የተደመደመ ሲኾን፡ በፈጣሪ በኩል፡ ምንጊዜም ተከብሮ ይፈጸማል፤ በሰብአዊው ፍጡር በኩል ግን፡ በዚህ መልክ ተከብሮ ሊጠበቅና ሊፈጸም ባይቻል እንኳ፡ በንስሓ እየነጻ÷ እየተስተካከለና እየታደሰ እንዲኖር፡ የፈጣሪ ፈቃድ ኾኖ፡ በዚህ መልክ፡ የስምምነቱ ቃል ኪዳን፡ ጸንቶ ሲሠራበት፡ ከዛሬው ዘመን ደርሷል::

"በእኹኑ ጊዜ ግን፡ የዚህ ቃል ኪዳን፡ የስምምነት አንቀጾች፡ በኢትዮጵያዊው ትውልድ በኩል፡ በመፍረሳቸው ምክንያት፡ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እየደረሰ ያለው ፈተናና መከራ፡ እነሆ ይታያል፤ ስለዚህ፡ ይኸው 'ኢትዮጵያዊነት'፡ በዚሁ የስምምነት ቃል ኪዳን መሠረት፡ የሚያስገኘውን መልካም ሕይወት መልሶ ለመረከብ ይችል ዘንድ፡ ትውልዱ፡ እንደተለመደው፡ ያፈረሰውን የስምምነቱን ቃል ኪዳን፡ ራሱን፡ በንስሓ አንጽቶና አስተካክሎ፡ ሊያድሰው ያስፈልገዋል!" በሚል ቃል ያበቃል::

እኔም፡ በዚሁ "ኢትዮጵያዊነት" ላይ፡ ቀደም ኻቤዬ፡ ጀምሬው የነበረውን፡ ኢትዮጵያዊ ተልእኮዬን፡ ከዚሁ ግንዛቤዬ የተነሣ፡ በበለጠ እውቀትና ጽናት ቀጠልሁ፤ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"÷ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!" እና Ethiopia: The Classic Case የተባሉት መጻሕፍቴም፡ የዚህ ተልእኮዬ ውጤቶች ናቸው::

በዚህ ተልእኮዬ፡ በአገሬና በመላው ዓለም እየተዘዋወርሁ፡ ሓዋርያዊ ግዳጄን እየፈጸምሁ ሣለሁ፡ አንዳንድ፡ እውነተኞች ኢትዮጵያውያን፡ በእኔ ላይ እየደረሰ ያለውን ከሚመስል፡ የተለያየ ፈተናና መከራ ጋር ሲታገሉና ሲጋደሉ አገኘኋቸው:: እነርሱም፡ *"አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት÷ እውነቱንም ሹ!"* የሚለውን፡ የፈጣሪያችንና የንጉሣችን የኢየሱስ ክርስቶስን÷ ቀጥሎም፡ *"ልጄ ያሚላችሁን ኹሉ አድርጉ!"*[ማቴ] የሚለውን፡ የእናታችንና የንግሥታችን፡ የቅድስት ድንግል ማርያምን መሪ ቃላት ተከትለው በመኖር፡ የሚታገሉትና የሚጋደሉት ናቸው::

ምዕራፍ ፪፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሠቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ግዳጅና ጥቅም።

ያ ፈተናና መከራም፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊነታቸው መታወቂያ በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸው በመጽናታቸው፡ በአገር ውስጥም ኾነ በውጭ አህጉር፡ ለነፍስና ሥጋ ስደትና እሥራት፥ ረሃብና ጥማት፥ ሕመምና ድህነት፥ ጦርነትና እልቂት ሳይቀር አጋልጦ የሰጣቸው፥ እንደመለኮታዊው የትንቢት ቃልም፡ በዘመናችን ከደረሰው የዓመፅ፡ የክህደትና የአመንዝራነት ኃጢኣት የተነሣ፡ በአገራችን፡ ድንገት የፈነዳው፡ የቁጣ እሳትና የቅጣት ማዕበል ነው።

አዎን! በአኹኑ ጊዜ፡ ይህ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በረሀብና በበሽታ፥ በጦርነትና በስደት፡ እየደረሰበት ያለው፡ የዚሁ የፈተናውና የመከራው ዓይነት፡ እስከዛሬ፡ ገዝፎ ከሚታይበት፡ ከሥጋዊነቱና ከዓለማዊነቱ ጕኔታ አልፎ፡ እጅግ ወደረቀቀበት፡ ወደመጨረሻው መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ መልኩ ተሸጋግሮ መክበዱን ተመለከትሁ፤ ከሥጋዊውና ከዓለማዊው ፈተናና መከራ ይልቅ፡ መንፈሳዊውና ሃይማኖታዊው ይጸናልና፡ በነገሩ ተመሠጥሁ።

ሥጋዊውና ዓለማዊው ችግር፡ በሥጋዊውና በዓለማዊው አቅርቦት የሚሻሻል፡ የሚፈወስና የሚወገድ፥ በመጨረሻም፡ በሥጋ ሞት የሚያበቃ ይኾናል፡ መንፈሳዊውና ሃይማኖታዊው ግን፡ እንደዚያኛው፡ በቀላሉ፡ ሊሻሻል፥ ሊፈወስና ሊወገድ የማይችል፥ በመጨረሻም፡ ወደዘለዓለማዊው የነፍስ ሞት የሚያደርስ ስለኾነ፡ እጅግ የተመሠጥሁት፡ ስለዚህ ነበር። <u>የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና፡ ዛሬ የሚገኙበት የፈተናና የመከራ ጕኔታ፡ እጅግ አሳዛኝ፥ እየጸና የሚኼድና ማብቂያ የሌለው የኾነበት ምክንያት፡ የችግሩ መንሥዔና ፍጻሜ፥ መፍትሔውም፡ ሥጋዊና ዓለማዊ ሳይኾን፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ስለኾነ ነው፡ ማለትም፡ ረሀቡ፥ በሽታው፥ ጦርነቱና ስደቱ፡ ከሥጋዊውና ከዓለማዊው ይልቅ፡ የኢትዮጵያዊዉን ነፍስና ዘለዓለማዊ ህልውናውን፡ በይበልጥ የሚመለከትና የሚጎዳ፡ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ መኾኑን፡ እናንተም፡ ከልባችሁ ልትገነዘቡት ይገባል።</u>

ይህን ጽዋ፡ በትእግሥት እየተቀበሉት ያሉት፡ እኒያ፡ የቃል ኪዳን ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ፡ በቁርጠኝነት የጀመሩትንና እስከዚህ ያደረሱትን ገድል፡ ለመጨረሻው የድል አክሊል ያበቁት ዘንድ፡ በተሰለፉበት መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ተጋድሏቸው፡ በትግል መሣሪያነት፡ እስከዛሬ፡ በያሉበት፡ በቅርብ ሲጠቀሙበት የቆዩት ልቦናዊውና ጽሑፋዊው ትጥቃቸው፡ ለአኹኑና ወደፊት ለሚጠብቃቸው ሰልፍ፡ በበለጠ የተጠናከረና የተሟላ ኾኖ እንዲያገለግላቸው፥ ሌላውም፡ በያለበት የሚኖረው፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ኹሉ፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት" በትክክል አውቆ፡ በኢትዮጵያዊነት ጸጋና ኃይል እንዲጠቀም፥ የኢትዮጵያዊነት ግዳጁንም፡ በሚገባ እንዲፈጽም ለማድረግ፡ ይህ ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

፪ኛ፡ እኔ የተገኘሁበት፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ የኢትዮጵያዊነት እውቀትን፡ ከሕፃንነቱ አንሥቶ፡ ሊያውቅና ሊማር ይገባው የነበረው፡ ከጥንት፡ ከመጀመሪያው ተያይዞና ጸንቶ፡ እስካኹን ሲሠራበት በኖረው ኢትዮጵያዊ ሥርዓት፡ በቤተሰብና በቤተ ክህነት ትምህርት ቤት ነበር።

ነገር ግን፡ ባለመታደል፡ ከቀድሞ ጀምሮ፡ እንደዛሬው ጊዜ፡ በአገር ተወላጆች መሣሪያነት÷ እንዲሁም፡ በቤተ ሕዝቡ÷ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ተባባሪነት፡ በባዕዳን ተጠንቶና ታቅዶ በተፈጸመበት ደባ፡ ይህን እውቀት እንዳያገኝ ተፈርዶበት፡ ለዚህ ፍርድ፡ በሰለባነት በመዳረጉ፡ የደረሰበትንና እየወረደበት ያለውን መቅሠፍት፡ አስተዋይ ተመልካች የኾነ ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ እንደተገነዘበው አምናለሁ። ይህን እውነታ፡ ባለፉት ድርሰቶቼ በሚበቃ አብራርቼዋለሁ።

በዚህ ደባ፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ የቀደሙ አባቶቹና እናቶቹ፡ ከአምላካቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር ተማምለውና ጠብቀውት የኖሩትን የቃል ኪዳን ስምምነት፡ ንቆና ክዶ፡ በዓመፅ በማፍረሱ፡ *"ስለዚህ፡ እላችኋለሁ፦ 'የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእናንተ ተነጥቃ ትመሰዳለች፤ ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች!'"*[፴፫] ያለው የፈጣሪው ቃል ደርሶበት፡ እነሆ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ያደረገውን፡ ያን "እውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱን" አጥቶ፡ በባዕዳን እጅ፡ በሥቃይ ሲማቅቅ ይታያል።

ከእውነተኛ ማንነቱ ይልቅ፡ የሐሰት ባዕድነትን፡ ያለፈቃዱ በግድ እንዲቀበል፡ በራሱ ወገኖች ጭምር ተፈርዶበት÷ ፍርዱም እየተፈጸመበት ያለው፡ ይኸው፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ በጠላቶቹ እየተካኼደበት ያለውን ረቂቅና ግዙፍ ዘመቻ፡ ያልተረዳው መኾኑ÷ ተረድቶትም ከኾነ፡ አውቆ በግዴለሽነት እየተቀበለው መቀጠሉ፡ እጅግ ያሳዝናል። ኃይሉ፡ እስከዛሬ ሊበርድ ባልቻለ ጽናት፡ ከጠላቶቹ፡ በየዘመናቱ የሚሠነዘርበትን፡ ይህንኑ፡ የእውነተኛ ማንነቱ መታወቂያ የኾነውን፡ "ኢትዮጵያዊነቱን"፡ ቀስ በቀስ እያጣ እንዲኼድ የማድረጉ ሙከራቸው፡ ምንም እንኳ፡ እርሱ፡ "እምቢ!" ብሎ ቢታገለው፡ ተሳክቶላቸው፡ ትውልዱ፡ በአኹኑ ዘመን፡ ተንኰታኵቶ ከሚገኝበት ውርደትና እየተሠቃየበት ካለው የጥፋት ዝቅጠት መድረሱን፡ ራሱ ትውልዱ ብቻ ሳይኾን፡ መላው የዓለም ሕዝብ ጭምር፡ በገሃድ ስለሚመለከተው፡ መካድና ማስተባበል፡ ከቶ አይቻልም።

ይህ ኹሉ ችግር የተፈጠረው÷ እየተፈጠረም ያለው፡ ከምንም፡ ወይም ከማንም ሳይኾን፡ ቀደም ብዬ፡ ደጋግሜ እንደገለጽሁላችሁ፡ ከዚያው፡ ከታወቀው፡ ከአንዱ የጠላቶቹ ጎራ መኾኑ ሊታወቅ ይገባል፤ ይህም፡ ኢትዮጵያዊው፡ ከእግዚአብሔር፡ በቃል ኪዳን ከተሰጠው "ኢትዮጵያዊነቱ" ይልቅ፡ በሥውር ኃይላትና በገሃድ ጦርነቶች አማካይነት፡ በእጎ ከታታዮቹ ዘመናት እየተገዘገዘ÷ በሰው ሠራሽ የታሪክ ቅርሶች ማስረጃነትም እየተሳበበ፡ የተፈጸመበት ደባ ነው።

ምዕራፍ ፪፤

"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሡቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ጎዳጅና ጥቅም።

ይህም፡ በመጀመሪያ፡ ይሁዲነትን÷ ሳባዊነትንና አረባዊነትን÷ በመካከሉም፡ ግሪካዊነትንና ግብፃዊነትን÷ ኋላም፡ "አርቶዶክስ" በሚል ሃይማኖታዊ ሽፋን፡ የእጅ አዙር ቅኝ ተገዢነትን÷ ከዚያም፡ እስልምናን÷ ተያይዞም፡ ኩትልከናን÷ በመጨረሻም፡ ኤውሮጳዊነትን÷ በቅርቡም፡ እግዚአብሔር አልባነትን÷ ዛሬም፡ አሜሪካዊነትን፡ ወይም እንደገና፡ እስልምናን እንዲቀበል፡ ባለጋራዎቹ÷ ተቃዋሚዎቹና ጠላቶቹ በረቂቅ ባካኼዱበትና በሚያካኺዱበት ሴራና በገሃድ በፈጸሙበትና እየፈጸሙበት ባለው የኃይል ወረራ፡ በግዘፍ ተመስክሩዋል።

ስለዚህ፡ የዛሬው ትውልድ፡ የ"እውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ" መታወቂያ የኾነችውንና በይፋ ያጣትን፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ መልሶ ያገኛት ዘንድ፡ ቢቻል፡ ወደፍጹሙ የንስሓ ምግባሩ መርቶ ለማድረስ ሲኾን÷ ምናልባት፡ ይህ ባይቻል፡ በዚህ "ኢትዮጵያዊነት" ላይ እስከዛሬ ሲካኼድ ለኖረው÷ አኹንም እየተካኼደ ላለውና ወደፊትም መካኼዱ ለማይቀረው ጥቃት፡ ያልተበገረ÷ በኢትዮጵያዊነቱ ፍቅር የሚቃጠል÷ የሚቈረቈርና የሚቀና፡ ሰሚ ወገን፡ በግለሰብ ኾነ በቤተሰብ÷ በጎብረተሰብ ኾነ በብሔር ደረጃ ካለ፡ በዚህ ውይይት የተገለጸውን፡ ይህን "ኢትዮጵያዊነት"፡ ለእርሱና ለልጆቹ÷ ከእነርሱ የሚረከቡ መልካም የልጅ ልጆች ተፈጥረው ከተገኙም፡ ለእነርሱና ለሚቀጥለው ትውልድ ለማትረፍ፡ ይኸው ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

ይኸ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ አባል የኾነ ኹሉ፡ በሕይወተ ሥጋ ዘመኑ የሚደርስበት የኑሮ ጽዋ፡ ምን ዓይነት እንደሚኾን፡ አስቀድሞ የማወቁ ኃይል፡ ያልተሰጠው መኾኑ፡ እስካኹን፡ በእየራሱ በደረሰው ፈተናና መከራ፡ በሚበቃ የተማረ ይመስለኛል።

በቅዱሱ የእግዚአብሔር ኪዳናት በተመሠረተው ኢትዮጵያዊነት ላይ፡ እንደዛሬው ኹሉ፡ አኹንና ወደፊት÷ ለምንጊዜውም፡ የዓመፁና የክህደቱ ኃጢአት እየቀጠለ የኼደ እንደኾነ÷ ያም፡ እንደትንቢቱ፡ ግድ የማይቀር ሊኾን ስለሚችል፡ ምናልባት፡ በዚያን ጊዜ፡ ካህንና መምህር÷ ከእነዚያም ጋር፡ መሥዋዕት የሚቀርብባትና የመለኮት ጸጋዎች የሚሰጡባት ቤተ መቅደስ÷ እንዲሁም፡ የሃይማኖትና የጸሎት መጻሕፍት ሳይቀሩ፡ ይታጡ ይኾናል፤ እጅግ ጽኑ በሚኾነው፡ በዚያን የረሃብና የጥማት÷ የእርዛትና የሕመም÷ የእሥራትና የስደት ጊዜ ደግሞ፡ እነዚያን መንፈሳውያን አገልጋዮችና ቅዱሳት ንዋያት ተክቶ ሊጠቀምበት የሚችል መሣሪያ፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊ እንዲኖረው በግድ ያስፈልጋል።

ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰውና፡ በእነዚያ የመከራ ዓይነቶች ውስጥ የሚገኝ፡ ማናቸውም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ÷ ቤተሰብ÷ ወይም ጎብረተሰብ፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ጸንቶ በመኖሩ ከቀጠለ፡ ይህን የመሰለውን መሣሪያ ለመቀበል እንዲችል ያደረገውን ብቅዓት፡ በአምላካዊው ቸርነትና በኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕትነት በተጎናጸፈው ጸጋ ተቀዳጅቷል።

ይኸውም፡ ቅዱስ ጴጥሮስ፡ ከጌታ ለቀረበለት ጥያቄ፡ *"አንተ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ!"* በማለቱ፥ *"አንተ ዓለት ነህ፡ በዚችም ዓለት ላይ፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ!"*[ፘ] ያሰኘውን፡ የአምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስን የመጨረሻ ሹመት እንደተቀበለ ኹሉ፥ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" የተባለው፡ ያ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባም፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱ በመሰከረበት ጊዜ፡ ያንኑ፡ የቅዱስ ጴጥሮስን ቃል በማጽናቱ፡ ለዚያ መለኮታዊ ሹመት እንደበቃ ኹሉ፡ ያም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ በዚያ ኢትዮጵያዊ ሰውነቱ ላይ፡ ያን ጸጋ ስለሚቀበል ነው።

በዚያን ጊዜ፡ *"በእውነት የሚሰግዱ፡ ለአብ፡ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ እርሷም አኹን ኾናለች፤ አብ ሊሰግዱለት፡ እንደእነዚህ ያሉትን ይሻልና። እግዚአብሔር፡ መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም፡ በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።"*[ፚ] ባለው መለኮታዊ ቃሉ መሠረት፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ፡ ለዚያ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፡ ቤተሰብ ወይም ጎብረተሰብ፡ ካህንና ሊቀ ካህናት ኾኖ፡ በዚያ፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሰውነትም ላይ፡ ቅድስት እናቱን ድንግል ማርያምን፡ ጽላትና ታቦት፥ መንበርና ቤተ መቅደስ አድርጎ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የዚያ ኢትዮጵያዊ ግለሰብ፥ ቤተሰብ ወይም ጎብረተሰብ አምልኮ፡ በእውነትና በመንፈስ ተከናውኖ እንዲፈጸምለት ያደርጋል።

በዚህ ምሥጢር፡ ለፍጹምነት የሚበቃውን፡ የእውነትና የመንፈስ አምልኳችንን በሚመለከት፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ፡ ይህን የጌታ ቃል፡ እንዲህ ሲል አብራርቶታል፡- *"እኛ፡ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነን። ...የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደኾናችሁ፥ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም፡ የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ፡ እግዚአብሔር፡ እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ ቅዱስ ነውና፤ ያውም፡ እናንተ ናችሁ።"*[ፚ]

ስለዚህ፡ በእነዚህ የእግዚአብሔር ቃላት መሠረት፡ በእነዚያ የፈተና ጊዜያትና በተለያዩት የመከራ ዓይነቶች ውስጥ ለሚገኝ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ ከዲያብሎስና የእርሱ ከኾኑት ሠራዊቱ ጋር ለሚገጥመው መንፈሳዊ ውጊያ፡ የተፈተነ መሣሪያና የተሟላ ትጥቅ ኾኖ ያገለግለው ዘንድ፡ ይህን ከመሰለው ውይይት የሚገኘውን የጉያ መጽሐፍ፡ (ምናልባት፡ ይህም መጽሐፍ፡ ከጥፋቱ ማዕበል፡ በእግዚአብሔር ቸርነት ሊተርፍ የቻለ እንደኾነ፡) በእጁ እንዲኖረው ማድረግ፡ አግባብ በመኾኑ፡ ይህንኑ መሣሪያና ትጥቅ፡ ለግለሰቡ፥ ለቤተሰቡና ለጎብረተሰቡ ለማስጨበጥ፡ ይኸው ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

፬ኛ፡ የዘመኑ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ዕድሉ ኾኖ፡ እንዲዘፈቅበት ከተደረገበት፡ ከአዥጉ አሳዛኝ ዅናቴው የተነሣ፡ ሊያውቀውና ሊያስተውለው የሚገባ፥ ነገር ግን፡ ያላወቀውና ያላስተዋለው፡ አንድ ቁም ነገር መኖሩን፡ እንደገና ላስገነዝባችሁ እወድዳለሁ። ይኸውም፡ ከዚህ ጠንቀኛ ችግሩ ተላቅቆ፡ ሰላማዊ ህልውናውን እንዲቀጥል፡ ማለትም፡ ከሚማቅቅበት ሥቃይ ተፈውሶ፡ የጤንነት ልብስን እንዲጐናጸፍ፥ ከወደቀበት የውርደት ዓዘቅትም ወጥቶ፡ የትንሣኤ ሕይወትን እንዲቀዳጅ የሚያስችለው፥ ምንጊዜም የማይለየው መድኃኒትና አስተማማኝ መፍትሔ ኾኖት የኖረ፡ ከፈጣሪው የተሰጠው የቃል ኪዳን ውርስ፡ በአጭ መገኘቱ ነው፤ ይህም ውርስ፡ በትንቢተ ኤርምያስ መጽሐፍ፡ በምዕራፍ ፲፭፥ ቊጥር ፳፫ ላይ ተጽፎ፡ በዓለሙ ዅሉ ይነበባል፤ እርሱም፡ *"ኢትዮጵያዊ መልኩን፥ ወይስ ነብር ዝንጕርጕርነትን ሊለውጥ ይችላልን?"* የሚለው፡ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

የዚህን መለኮታዊ ቃለ መጠይቅ ምላሽ፡ ራሱ ጥያቄው፡ በራሱ መልሶ፡ የሚያስነብብ ከመኾኑ ጋር፡ የእያንዳንዱም ሰው ኅሊና፡ ለባለቤቱ፡ ቀጥተኛውን መልስ፡ በቀላሉ እንደሚሰጥ ግልጽ ነው፤ ይህንኑ መልስ፡ በጽሑፍ መስጠት ቢያስፈልግ፡ ቃሉ፡ ያለውልውል፡ ባጭሩ፡ "ኢትዮጵያዊም፡ መልኩን፥ ነብርም፡ ዝንጕርጕርነቱን አይለውጥም!" የሚል ይኾናል። ስለዚህ፡ ለዚህ ውይይታችን፡ ገና ከመነሻችን፡ መርህ አድርጌ ላቀርበው ባዘጋጀሁት፡ በዚህ፡ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፡ ዓለም አቀፍና ዘለዓለማዊ እውቅና የተሰጠው፡ ይህ "ኢትዮጵያዊነት" ወይም፡ "ኢትዮጵያዊ ማንነት"፡ በባዕዱ ቀርቶ፡ በራሱ በኢትዮጵያዊዉም እንኳ ቢኾን፡ በምንም መንገድ ሊለወጥ፡ ፈጽሞ የማይቻል መኾኑን፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ አበክሬና አጠንክሬ ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ይህ እውነታ ተረጋግጦ የቀረበው፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ ብቻ ሳይኾን፡ ለባዕዳኑም ሲኾን፥ ይዅን እንጂ፡ ይህን መረዳት ያቃታቸውና ከታሪክ መማር የተሣናቸው፡ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ደመኛ ጠላቶች፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ ዛሬም እንደገና፡ "መልክህን ለውጥ!" ብለው፡ በመረባረብ፡ ቁም ስቅሉን እያሳዩ ሲዋጉት ይታያል። ይህን የመሰለውን ለውጥ ማምጣት የሚቻላቸው መኾን ያለመኾኑን፡ እንደሌላው ሥጋዊ ጥበባቸው፡ በቅድሚያ፡ ለምን ወደአውሬው ነብር ዤደው አይሞክሩትም? ሞክረውት ከኾነም፡ ምናልባት፡ የነብሩን፡ የቆዳውን ቀለማት፡ ሊለውጡ ይችሉ ይኾናል፤ የነብርነት የተፈጥሮ ባሕርዩን ግን፡ ሊለውጡት፡ ከቶ አይችሉም።

ታዲያ፡ ያን ማድረግ፡ የማይቻላቸው ከኾነ፡ የኢትዮጵያዊዉን፡ ነፍሳዊና መንፈሳዊ መልኩ የኾነውን፡ እውነተኛ ማንነቱን፡ ግለትም፡ ኢትዮጵያዊነቱን፡ ሊለውጡ ስለማይችሉ፡ ከእግዚአብሔር በተሰጠው፡ በዚሁ የተፈጥሮ መልኩና ባሕርዩ፥ በተፈጠረባት ምድሩና በኖረባት ሃይማኖቱ፡ ህልውናውን እንዲቀጥል ለምን አይተዉትም? ለምን እንደማይተዉት፡ ምናልባት፡ ምሥጢራቸውን ለማያውቅ ሰው፡ ነገሩ፡ እንቆቅልሽ ይኾንበት ይኾናል።

ለእናንተና ለእኔ ግን: እንቆቅልሽ ሊኾንብን አይችልም፤ ምሥጢራቸውን እናውቀዋለንና:: እነርሱ የሚያስቡት: በዛሬው ያልታደለ ትውልድ ላይ እንዳደረጉት: ማለትም: ኢትዮጵያዊዉን: በትምህርታቸው ኃይልና በሥልጣኔያቸው ምትሓታዊ ውበት: አእምሮውን አፍዝዘውና አደንግዘው: በእነርሱ መልክ በመቅረፃቸው: ሥጋዊ አስተሳሰቡን: ወደእነርሱ እንደለወጡት ዅሉ: የነፍሱንና የመንፈሱንም መልክ ሊለውጡ የሚቻላቸው ይመስላቸው ይኾናል፤ ነገር ግን: ይህም: አይቻላቸውም::

ከዚህ ይልቅ: እኛ ያወቅነው: ሌላው: ዋናው ምሥጢራቸው: "በቅድሚያነትና በጥንታዊነት፥ በፍጹምነትና በዘለዓለማዊነት: ከእኛ ልቆና በልጦ፥ እንደሕያው ሐውልትም ከፊታችን ቆሞ ልናየው ስለማንፈልግ: ይህን ኢትዮጵያዊነት' ጨርሰን ማጥፋት አለብን!" ብለው: ጥንቱንም ቆርጠው የተነሡበት: የተደበቀ ዓላማ ያላቸው መኾናቸው ነው:: እነርሱ ያላወቁት: የኢትዮጵያውያን ምሥጢር ደግሞ: በፍጥረት መጀመሪያ: እግዚአብሔር መሥርቶ ያነጸው፥ አባቶቻቸውና እናቶቻቸው: "እምቢ ለሃይማኖቴ! እምቢ ለሀገሬ! እምቢ ለወገኔ!" ብለው: ደማቸውን ያፈሰሱለት፥ ሥጋቸውን የቆራረሱለት፥ አጥንታቸውንም የከሰከሱለት፥ በመጨረሻም: ሕይወታቸውን የሠዉለት: ይህ "ኢትዮጵያዊነት": እነርሱ ቀርተው: አበጋዛቸው: ዲያብሎስ ተጨምሮም እንኳ: ሊያጠፉት ያልተቻላቸውና የማይቻላቸው መኾኑ ነው::

ስለዚህ: መቼም: ጠላቶቻችን: ደመኞቻችን ስለኾኑ: እርም የላቸውምና: ይህን: እኩይ የኾነ: ምሥጢራዊ ዓላማቸውን የማይተዉት ከኾነ: ኢትዮጵያዊው: ዛሬም እንደወትሮው: ለዲያብሎስና የእርሱ መሣሪያዎች ኾነው ለሚያገለግሉት ዅሉ: የሚሰጠው ቁርጥ ምላሽ: ያው የለመዱትን ነው፤ ያም: "የለም! መልኬን አልለውጥም! ይኸው: የማይለወጠው መልኬም: 'ኢትዮጵያዊ' ባሰኘኝና ማንነቴ በታወቀበት: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቴ ላይ የተመሠረተው "ኢትዮጵያዊነቴ" ነው::" የሚለው ይኾናል::

'የማይለወጠው: የኢትዮጵያዊው መልክ' የተባለው: በእርግጥ የትኛው እንደኾነ: ማለትም: ሥጋዊው: ወይስ: ነፍሳዊው እንደኾነ: እዚህ ላይ: በትክክል ለይቶ ማሳወቁና ማወቁ አግባብ ይኾናል:: ሥጋዊዉን ኢትዮጵያዊ መልክማ: ምንም: እርሱም: ሊለወጥ የማይቻል ቢኾን እንኳ: ይኸውና: ሥጋውያን የኾኑት: ባዕዳን ለዋጮች: ሥጋዊ በኾነው ትምህርታቸው፤ ገንዘባቸውና ኃይላቸው አማካይነት: ከዚህ: ከዛሬው ሥጋዊ የኢትዮጵያ ትውልድ የተነሣ: ለዋውጠውት ይታይ የለምን? በእርግጥ: የማይለወጠው: ኢትዮጵያዊ መልክ: ነፍሳዊው ነው፤ እርሱም: *'እግዚአብሔር ሰውን: በመልኩ ፈጠረው፥ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው!'*[ዘፍ] የተሰኘበት: እግዚአብሔርን የሚመስልበት መልኩ ነው::

ምዕራፍ ፪፤
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሡቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ግዳጅና ጥቅም።

አንድ ኢትዮጵያዊ፡ ይህን፡ በምንም መንገድ፡ ሊለወጥ የማይቻለውን፡ የተፈጠረበትን፡ የእግዚአብሔር መልክ፡ በሃይማኖትና በምግባር አጽንቶ በሚገኝበት ጊዜ፡ የእግዚአብሔርን አጋዎች ተጎናጽፎ፡ በክብር÷ በሞገስና በቅድስና ይኖራል። ነገር ግን፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ፡ ማንነቱ የሚታወቅበትን፡ ይህን የማይለወጠውን፡ ከእግዚአብሔር ያገኘውን መልኩን፡ እንደዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በክህደት÷ በዓመፅና በምንዝርና 'ለውጫለሁ!' ብሎ፡ ራሱን በሚለይበት ጊዜ፡ አጋውን ተገፍፎ፡ በውርደት÷ በጉሥቊልናና በርኵሰት ይማቅቃል። የጉሥቊልናው ዓይነትና የርኵሰቱም መጠን፡ የአኹኑ ትውልድ፡ ሲማቅቅ እንደሚታይበት ኹኔታ፡ በሥጋ ብቻ የሚወሰን ሳይኾን፡ ከአምልኮ ባዕዱ መስፈን የተነሣ፡ የመበላሸቱና የመጨማለቁ÷ የመግማቱና የመከርፋቱ ጽናት፡ ወደነፍሱ ዘልቆ÷ ወደመንፈሱ ሳይቀር ጠልቆ ገብቶ የሚያሠቃየው ይኾናል።

ይህን ቁም ነገር፡ በወደፊቱ ውይይታችን ላይ፡ በሰፊው እንነጋገርበታለን። እርሱም፡ እግዚአብሔር፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ በእየልባችሁ ጽላት ላይ፡ የጻፈው÷ ነገር ግን፡ ቀደም ብለው በተወሱት ተቃዋሚ ኃይላት የተጻፈነው፡ ሕያው የእውነት ቃል የሚያረጋግጠው እውነታ መኾኑን፡ በዚያን ጊዜ ትገነዘቡታላችሁ። እስከዚያው፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነታችሁ ለማወቅ፡ እንዲህ፡ ጽኑ ፍላጎት ያላችሁና ከዚሁ የእውቀት ግብ ለመድረስ፡ ብርቱ ጥረት የምታደርጉ፡ እናንተ÷ እናንተንም የመሰሉት ኹሉ፡ ይህን ነገር፡ በማስተዋል ትመለከቱትና ልብ ታደርጉት ዘንድ ላሳስባችሁ እወድዳለሁ። ባዕዳኑና በስም፡ ኢትዮጵያዊ የኾነው ይህም ትውልድ÷ ይህን እውነታ እንዲገነዘቡት ለማድረግ፡ ይህ ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

ዳኛ፡ በተለይ በአኹኑ ጊዜ፡ ስለ"ኢትዮጵያዊነት" የሚሰጠው ትርጉምና ሓተታ፡ የበዛና የተለያየ በመኾኑ፡ ቃሉና ቃሉ የቆመለት ዓላማ፡ እንኳንስ፡ ለባዕዱና ኢትዮጵያዊነቱን ለማያውቀው፡ ለዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ÷ እንዲሁም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ወገን ጭምር ይቅርና፡ ለእውነተኛው ኢትዮጵያዊም ሳይቀር፡ አደናጋሪ እየኾነ በመኼድ ላይ እንደሚገኝ፡ በማንም አስተዋይ ተመልካች ዘንድ በግልጽ ይታወቃል።

ይህ ትውልድ፡ ራሱንና አገሩን፡ ከዚህ የውድቀት ደረጃ ሊያደርስ የቻለው፡ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን ብቻ ሳይኾን፡ ራሱንና የተፈጥሮ ወገኑንም፡ ባለማወቁ መኾኑ፡ ስማቸው፡ በእየቦታው በተጠቀሰው፡ በሌሎቹ፡ ድርሰቶቼ ውስጥ ተመስጧል።

የዚህ የትውልዱ አላዋቂነት ጠንቅ፡ እንዴት÷ መቼና የት እንደተቀፈቀፈ ለመረዳት፡ እጅግም የሚያዳግት አይደለም፡ ለትውልዱ፡ የህልውናው መሠረት የኾነውን፡ ይህን ምሥጢር፡ ሊያሳውቀው የሚችለውን፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ትምህርት፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንዲከታተል በማድረግ ፈንታ፡ ለዚህ እውቀት የሚያበቃው፡ ይኸው ኢትዮጵያዊው ሥርዓት ፈርሶ፡ "ኢትዮጵያዊነት"ን አለማወቅ ብቻ ሳይኾን፡ እንዲጸየፈውና እንዲጠላው÷ እንዲደመሰሰውም በሚያደርገው፡ በባዕዳኑ ትምህርት፡ ተከትኩቶ እንዲያድግና እንዲጎለምስ በመገደዱ መኾኑ፡ ተደጋግሞ ተነግሩዋል።

ከዚህ የተነሣ፡ ትውልዱ፡ እንኳንስ እግዚአብሔርን፥ ከዚያም፡ ኢትዮጵያዊነቱንና ሌላውን የተፈጥሮ ወገኑን ቀርቶ፡ የራሱ ሰውነት፡ ማለትም፡ "ሰው የመኾኑ ዓላማ" ምሥጢሩ ምን እንደኾነ እንኳ፡ ሊያውቅ ያልቻለ፡ ለማወቅም ያልፈለገ፡ ምስኪንና ጉሥቁላ ፍጡር መኾኑ፡ እነሆ፡ ዛሬ፡ ራሱና አገሩ ባለበትና እየተጓዙ በሚገኙበት የውድቀት ኹኔታ በግልጽ ይታያል።

"ታዲያ! በትውልዱ ላይ ለደረሰው፡ ለዚህ ውድቀት፡ መሠረታዊ መነሻው፡ ከቶ ምንድር ነው?" ለሚለው ጥያቄ፡ የሚሰጠው መልስ፡ "ትውልዱን፡ ወደዚህ ውድቀት አምዘግዝጎ የጣለው የጥፋት ምክንያት፡ ወደነበረበት ክብሩም፡ በትንሣኤ የሚመልሰው መፍትሔ መድኃኒት፡ ምን እንደኾነ ገሃድ አድርጎ የሚያሳየውን፡ ይህን፡ 'ኢትዮጵያዊነት' አለማወቁ ነው!" የሚል ይኾናል።

አዎን! ስለ"ኢትዮጵያዊነት" አውቆማ ቢኾን ኖሮ፡ ህልውናው፡ በመልካም ሕይወት ሊቀጥል፡ ከተለያዩ ችግሮቹም ኹሉ ሊድን የሚችልበትን ዕድል ባገኘ ነበር። በዚህም ዕድሉ፡ አባቶቹና እናቶቹ፡ በእርሱ፡ በትውልዱ ስም ቈምሮ፡ ከፈጣሪያቸው ጋር የተጋቡትንና ከባድ መሥዋዕትነትን በመክፈል፡ ጠብቀው ያስረከቡትን፡ ቅዱሱን ኪዳን ለማክበር ስለሚበቃ፡ በለመለመችውና በተዋበችው አገሩ ላይ፡ በፍጹም ፍቅርና በእውነተኛ ሰላም፡ በሙሉ ብልጽግናና በጤናማ ዕረፍት ለመኖር የመቻሉን ጸጋ በተቀዳጀ ነበር፡ ነገር ግን፡ ያን፡ ቃል ኪዳን፡ በሥውር ክህደትም ኾነ በግልጽ ዓመፅ በማፍረሱ፡ ያ ፍቅር፡ በክርክር፡ በፀብና በመለያየት፥ ያ ሰላም፡ በእርስ በርስ ፍጅት፡ በጦርነትና በዕልቂት፡ ያ ብልጽግና፡ በረሃብና ጥማት፥ በማጣትና በድህነት፡ ያ ጤናማ ዕረፍት፡ በቸነፈርና በደዌ፡ በአሥራትና በስደት ተተክቶ፡ ጽዋው፡ ኹሉን ማጣት ኾነ! ከኹሉም ይልቅ፡ ይህን ከመሰለው ሥቃይና መከራ ከዳረገው፡ ከዚያ የከሀደት ኃጢኣቱና ከዓመፅ በደሉ፡ በንስሓ ሲመለስ፡ ወደነበረበት ክብሩ የሚመለስ መኾኑን፡ ይኸው የቃል ኪዳን ዕድል፡ በሚያስተማምን ዋስትና ያረጋገጠለት መኾኑን አለማወቁ፡ አውቆ ከኾነም፡ በዚህ ዕድሉ ለመጠቀም አለመፈለጉ፡ እጅግ ያስገርማል።

ከዚህ አላዋቂነት የተገኘ ትርፍ ቢኖር፡ አገሪቱ፡ ዛሬ፡ ራሱ፡ መራራ ኾኖ፡ ህልውናውን መራራ ያደረገ፥ እርሷንም፡ በዓለሙ ፊት፡ የውርደት ሸማን ተላብሳ እንድትታይ ያደረገ፡ አስጠቂ ትውልድን ማፍራቷ ነው፡ ይህም፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ የዲያብሎስ የኾነውን፥ ከኢትዮጵያዊው እውነት ይልቅ፡ የባዕዳኑን ሓሰት የሚወድድ፥ የሚሰማ፥ የሚከተልና የሚፈጽም፡ የሃይማኖት ቅንዓት፡ የወገን ርኅራኄና የሀገር ፍቅርም የሌለው ትውልድን አስገኝቶ ማለት ነው።

የእርሱ የኾነውን መልካም ውርስ ኹሉ የሚጠላና ለሥጋው ብቻ የሚያስብ ትውልድ በመኾኑ፡ በምሳሌ አነጋገር፡ "ሲመትሩለት ይነጭ!"፥ ወይም፡ "ባለጌን ካሳደገ፡ የገደለ ጸደቀ!" ተብሎ ሊነገርበት የሚገባ ኾነ። ታዲያ፡ እናንተና እኔ፡ እየራሳችንን፡ "እኔ የኢትዮጵያ ልጂ ነኝ!" የምንል ከኾነ፡ በዚህ መልክ ስለታተተው የትውልዱ ኹኔታ፡ የምንሰጠው መልስ፡ ምንድር ሊኾን ነው?

ምዕራፍ ፱፡
"ኢትዮጵያዊነት" ምንድር ነው? ተዘግቶበት የኖረ፡ ምሥጢራዊ ጥያቄ፤ በ"ኢትዮጵያዊነት" የተከሠቱ ምሥጢራትን፡ የማወቁና የማሳወቁ ግዳጅና ጥቅም።

እንኳንስ፡ ለብዙ ሺህ ዓመታት በታወቀው ኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ የኖረው የኢትዮጵያ ትውልድ ይቅርና፡ የየትኛውም አገር ትውልድም ቢኾን፡ በግለሰብ ወይም በሕዝብ ደረጃ፡ ማንነቱን፡ በሃይማኖት ካላወቀና ካልጠበቀ በቀር፡ ህልውናው ሊቀጥል እንደማይችል ተረጋግጧል። ስለዚህ፡ ይህ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ብቻ ሳይኾን፡ ጉዳዩ የሚመለከተውንም ኾነ የማይመለከተውን፥ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ወዳጅ የኾነውንም ኾነ ያልኾነውን፡ ከዚህ ጠንቀኛ ችግር ለማዳን፡ የ"ኢትዮጵያዊነት"ን ትክክለኛ ምንነት፡ ከነባሕርያቱና ገጽታው፡ በግልጽ በመተንተን፡ ለኹሉ ለማሳወቅ፡ ይህ ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

ኧኛ፡ ይህ ውይይታችን እስከተካኼደበት ጊዜ ድረስ፡ "ኢትዮጵያዊነት"፡ ለሰባት ሽህ፡ አራት መቶ ዘጠና አምስት ዓመታት ጸንቶ ሊኖር የቻለ፡ አቻና ተወዳዳሪ የሌለው "ህልውና" ነው።

እርሱንም፡ ኢትዮጵያውያን፡ በሕያው ሰውነታቸው አሳድረውና ለዚህን ያህል ዘመን፡ ሕይወት አድርገውት ኖረውት፡ እነሆ፡ ለዛሬው ትውልዳቸው አስረክበውታል፤ ይህም የኾነው፡ እግዚአብሔር፡ በነቢዩ አንደበት፡ "*ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ።። ...እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!*"[፶፪] ሲል፡ ለመላው የሰው ልጅ ዘር የሰጠውን የተስፋ ቃል፡ ኢትዮጵያውያን፡ ከዓለም ሕዝቦች ኹሉ ተለይተው፡ በሃይማኖት ተቀብለው፡ ለምግባር ስላበቁት ነው።

ኢትዮጵያውያን፡ እንዲህ፡ በልብ፥ በቃልና በምግባር ትውፊት፡ ከትውልድ ወደትውልድ እያስተላለፉና እያወረሱ ያቆዩት፡ ይህ፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" ዘለዓለማዊ ቅርስ፡ ህልውናው፡ ምንም እንኳ፡ በእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ በዚያው ሕያው መልኩ የሚቀጥል መኾኑ የማያጠራጥር ቢኾንም፡ እውነተኛው የ"ኢትዮጵያዊነት" አቋም ርቆት የሚታየውን፡ የዛሬውን ትውልድ ደካማ ጎን በመመልከት፥ "በቃል ያለ ይረሳል፤ በመጽሓፍ ያለ ይወረሳል፤" የሚለውንም የአበው ዘይቤ፡ መርህ በማድረግ፡ የዚህን ውይይት ቁም ነገር፡ እንዲህ በጽሑፍ አሥፍሮና በዕትም ጠርዞ ማስቀመጡ፥ ከዚያም በላይ ማሠራጨቱ፡ በብዙ አግጣጫ እንደሚበጅ፡ በማንም አስተዋይ ተመልካች ዘንድ ይታመናል።

"ኢትዮጵያዊነት" ለዚህን ያህል ዘመን፡ በህልውናው ጸንቶ ሊቆይ የቻለበትን ምሥጢር፡ እንዲህ ተወያየቶ፥ በዝርዝር ገላልጾና አብራርቶ፡ በመጽሓፋዊ ቅጽ፡ ለኢትዮጵያዊው ትውልድ ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር፡ በመልኩ ለፈጠረው፡ ለሰው ልጅ ኹሉ ማሳወቁ፡ አምን፡ በእርግጥ ጠቀሜታ አለው። ከዚህም ጋር፡ እግዚአብሔር፡ ለእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር፡ በግሉም ኾነ በጋራ፥ ለምድራዊዉ ኾነ ለሰማያዊው ኑሮው ያዘጋጀለት፡ ዘለዓለማዊ የሕይወት ዕቅድ፡ "ኢትዮጵያዊነት" መኾኑን ተረድቶ፡ ራሱን፡ ለዚያ፡ ለ"እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት" ዕድል እንዲያበቃ መርዳት፡ አግባብና በጎ ምግባር ይኾናል።

ምናልባትም፡ በእየምክንያቱ፡ ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ፡ በማወቅ ወይም ባለማወቅ፥ በመታለል ወይም በመገደድ፥ በዓመፅ ወይም በከሀደት ተለይቶ የወጣ ወገንም ቢኖር፡ ራሱን ወደዚያ፡ ወደእውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱ ጸጋ፡ በንስሓ እንዲመልስ፡ በአጠቃላይ፡ የ"እውነተኛ ኢትዮጵያዊነት"ን ዝክረ ነገርና ዜና መዋዕል፡ አስተዋይ ለኾነ፡ ለማናቸውም ሰብአዊ ተመልካች፥ በተለይም፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው ግለሰብ፡ አሟልቶ ለማቅረብ፡ ይህ ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

ኧኖ፡ ይህን "ኢትዮጵያዊነት"፡ ከዓፅመ ርስት አገሩ ብቻ ሳይኾን፡ ከዓለምም ምድረ ገጽ ለመደምሰስ፡ ጠላቶቹ፡ ከጥንት ጊዜ ጀምረው፡ በእየዘመናቱ፡ በተናጠልም ኾነ፡ ኃይላቸውን በማቀናጀት እየተነሣሡ፡ በረቂቅና በሥውር ሲያካኼዱ የቆዩትን ጦርነት፡ እነሆ፡ ዛሬም፡ ራሳቸውን፡ የኢትዮጵያን ልጆች መሣሪያ በማድረግ፡ በገሃድ ክህደትና በግዘፍ ዓመፅ፡ አጠናክረው ሊቀጥሉበት ያወጁት፡ በ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. መኾኑ አይዘነጋም።

ታዲያ፡ እስከዚያን የደርግ ዘመን ድረስ፡ በረቂቁ የሃይማኖት ኃይልም ኾነ፡ በግዙፉ የጦር ሠራዊት ተመክቶ፡ ያን፡ የሚያስቀናውን "ኢትዮጵያዊነት" ሊያጠፋ ይመጣበት የነበረውን ወራሪ ጠላት፡ ከሕዝቡ ጋር ተከላክሎ እንዲመልስ፡ የዘመኑ ርእሰ ብሔር የኾነው አጼ፡ ሠራዊቱን፡ ለዘመቻ አስከትቶ ከመነሣቱ በፊት፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ፡ በነጋሪት፡ ያስተላልፍ የነበረው፡ የአዋጅ ቃል፡ ምን የሚል እንደነበረ፡ ይህ የኢትዮጵያ ትውልድ ያውቃልን? ቀደም ብሎ፡ እንዲያውቅ ስላልተደረገ፥ እየፈጸመው ያለው ድርጊቱም፡ አላዋቂነቱን እየመሰከረበት ስለኾነ፡ "የአዋጁን ቃል፡ ሰምቶትም አያውቅ!" ቢባል፡ ከእውነት መራቅ አይኾንም።

እንግዴህ፡ ይህ፡ ያልታደለ ትውልድ፡ ቢያውቅም፥ ባያውቅም፡ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ከእያንዳንዲ ኢትዮጵያዊት ጆሮ እንዲደርስ ይደረግ የነበረው፡ የአዋጁ ቃል፡ የማይለወጥ አንድ ነው፤ እርሱም፡ የ"ኢትዮጵያዊነት" መገለጫ የኾኑትን፡ "ሃይማኖትህን፡ የሚያጠፋ፥ ትዳርህን የሚያፈርስና ርስትህን የሚነቅል ወራሪ ጠላት መጥቶብሃልና፡ ተከተለኝ!" የሚል ነው። በሌላ አገላለጽ፡ "በኢትዮጵያዊነትህ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘሃቸውን ነጻነትህን የሚገፍፍ፥ መንግሥትህን የሚያስወግድና አገርህን የሚወርስ ጠላት መጥቶብሃል!" ማለት ነው።

አኹን ላለው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ በረቂቁ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ የነጋሪት ድምፅ፡ እየተላለፈለት ያለው፡ የዚህ የአዋጅ ቃል፡ ምን ዓይነት ቁም ነገርን ያዘለ ይመስላችኋል? "ይህችን 'ኢትዮጵያን'፥ ይህንም 'ኢትዮጵያዊነት'፡ አባቶችህና እናቶችህ፡ ለዚህን ያህል፡ የረዥም ዘመን ዕድሜ አቆይተው፡ ሊያስረክቡህ የቻሉት እኮ፡ እንዲህ እንደአንተ፡ ቁጭ ብለው ተዝናንተው፡ ወሬ በማውራትና ሥጋዊ ምቾታቸውን በመጠበቅ፥ ዓለማዊዉንም ተድላ ደስታ በማድረግ አይደለም።

"አንተማ፡ ለሰላምታህ እንኳ፡ 'እጅ ንሣ እንጂ፡ እጅህን አትስጥ!' ሲሉ፡ በኑዛዜ የተዉልህን የአደራ ቃላቸውን፡ ንቀህና አቃልለህ፡ እጅህን፡ ሳይጠይቅህ፡ ለጠላትህ እየዘረጋህ በመስጠት፡ ስትማረክ ኖረህ የለምን?

"ይኸው አኹንም፡ ያለአንዳች ተቃውሞና ትግል፡ በቀላሉ፡ ራስህን ለጠላቶችህ ማስረከብ ብቻ ሳይኾን፡ በራስህ መሣሪያነት፡ 'ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት' ጭምር፡ ተደምስሰው እንዲጠፉ ሲያደርጉ፡ እነሆ፡ ዝም ብለህ እያየህ አይደለምን?" የሚል ኾኖ፡ ጩኸቱ ሲያስተጋባ ይሰማል።

የአዋጁ ቁም ነገር፡ በዚህ ብቻ ሳያበቃ፡ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፦ "ከላይ፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፡ አባቶችህና እናቶችህ፡ ይህችን፡ 'ኢትዮጵያ' እና ይህን፡ 'ኢትዮጵያዊነት' ጠብቀው የኖሩትና ለአንተ ያስተላለፉት እኮ፡ በቅዱሱ ቃል ኪዳናቸው ጸንተውና ተማምነው፡ በረሀብና ጥማት፡ በሕማምና እርዛት፡ በእሥራትና ስደት፡ ደማቸውን አፍስሰው፡ ሥጋቸውን ቆርሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው፡ በመጨረሻም፡ የሞት ጽዋቸውን፡ በሃይማኖታዊ ቆራጥነትና በሀገር ፍቅር ጀግንነት በመቀበል ነው።

"ከፈርያን ጀምሮ፡ እስከዛሬ ያሉት ግብፃውያን፡ እንዲሁም፡ ፋርሶች፡ ሕንዶች፡ ዓረቦች፡ አይሁድ፡ የአዳል፡ የሱማሌ፡ የሱዳንና የቱርክ እስላሞች፡ እንግሊዞችና ጣልያኖች፡ አሜሪካኖችና መስኮቦች፡ "ይኸን 'ኢትዮጵያዊነት'፡ ከነአቋሞቹ፡ አፈራርሰንና ደምስሰን፡ 'ኢትዮጵያ' በተባለችው፡ በምድሪቱ ላይ፡ የራሳችንን ሃይማኖት እናስፋፋለን፡ የራሳችንን መንግሥት እንመሠርታለን፡ የራሳችንንም ሕዝብ እናሠፍራለን!" ብለው፡ በቅርበቹም፡ ኾነ በሩቆቹ ዘመናት፡ በሥውርና በግልጽ ጥበብ፡ በረቂቅና በግዙፍ ኃይል በመጡባቸው ጊዜ፡ እነዚህን ኹሉ ተጸራሪዎች፡ ድል ነሥተው፡ በመጡበት መንገድ የመለሷቸው፡ እጅግ ታላቅ መሥዋዕትነትን ከፍለው እኮ ነው፤ እንዲህ ባይኾንማ ኖሮ፡ 'ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት' እንዲህ ተጠብቀው፡ ነጻ ህልውናቸው፡ እንዴት እስከዛሬ ሊቀጥል ይችል ነበር? አይችልም። ለዚህም፡ በጥቂቱ፡ ይሁዲቷን ጉዲት፡ እስላሙን አሕመድ ግራኝንና ካቶሊካዊዉን ፋሺስት ሙሶሎኒን፡ ደግሞም፡ የመቅደላን፡ የጉንዳጉንዲን፡ የጉራዕን፡ የመተማን፡ የአድዋንና የጨለንቆን ድሎች፡ እዚህ ላይ በምሳሌነት መጥቀሱ ይበቃል።"

ታዲያ፡ እናንተስ፡ ይህንኑ፡ የአባቶቻችሁንና የእናቶቻችሁን የአዋጅ ቃል በመከተል፡ ከእነርሱ የተረከባችኋቸውን "ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን"፡ ከመደምሰስ ለማዳን፡ የሚገባችሁን ሃይማኖታዊና ምግባራዊ መሥዋዕትነት እየከፈላችሁ ነውን? ወይስ፡ በዓመፅና በክህደት፡ "እምቢ!" ብላችሁ፡ የሚገባችሁን፡ ይህንኑ መሥዋዕትነት ከመክፈል እየሸሻችሁ ነወይ ያላችሁት? አምን! ከእነርሱ የተረከባችኋቸውን "ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን"፡ በእርግጥ፡ ለልጆቻችሁ፡ በትክክል እያስተላለፋችሁ ነው ያላችሁት? ወይስ፡ ይህን ኃላፊነታችሁን፡ በግዴለሽነት፡ ወይም ስለማታምኑበት፡ ቸል ብላችሁ ትታችሁታል? ለእነዚህና እነዚህን ለመሰሉት ጥያቄዎች፡ ተገቢውን መልስ የመስጠቱ ውዴታም፡ ግዴታም፡ የእናንተው፡ የየግላችሁ ነው።

ከዚሁ ቁም ነገር ጋር ተያይዞ፡ ለዚህ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" ለሚለው፡ ለእያንዳንዱ፡ የዛሬው ትውልድ አባል፡ ለእናንተና ለእኔ ጭምር፡ ከቀደሙት አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ የሚቀርብ፡ ሌላ፡ ተከታይ፡ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ጥያቄ አለ።

አዎን! በአኹኑ ጊዜ፡ የሚገኝበትን አደገኛና አሥጊ ኹናቴ ለመገንዘብ፡ የሚያይበት የሃይማኖት ዓይን፥ የሚሰማበት የሃይማኖት ጆሮና የሚያስተውልበት የሃይማኖት አእምሮ ላጣው ትውልድ፡ የሚቀርበው ጥያቄ "የቀድሞዎቹ ደመኞች ጠላቶችህ፥ የዛሬዎቹ፡ አዲሶቹ ተጨምረው፡ ቀድሞ፡ ራሳቸው፡ ሠራዊታቸውን አሰልፈው መጥተው፡ በገሃድ ያደርጉብህ የነበረውን ወረራ፡ በአኹኑ ዘመን፡ ከደርግ ጀምሮ፡ እየኾነ እንደሚታየው፡ በራስህ ልጆችና ወገኖች መሣሪያነት፡ በእጅ አዙር፡ ወርረው ይዘውህ፡ 'ሃይማኖትህን፡ ሲያጠፉት፥ ትዳርህን ሲያፈራርሱትና ርስትህን ሲቀሙህ፡' ምን እየደረሰብህ መሰለህ? ስለዚህ፡ ከመጨረሻው ሽንፈት ድነህ፡ ለመጨረሻው ድል ትበቃ ዘንድ፡ ማንም ሊቋቋመው በማይቻለው በንስሓ መሣሪያ፡ ራስህን፡ አስታጥቀህ፡ ለመንፈሳዊው ሰልፍ፡ ተነሣ!" የሚል ነው።

የዚህ መንፈሳዊ ጥሪ መልስ፡ ከእያንዳንዱ ተጠሪ የሚሰጥ ቢኾንም፡ በእናንተ በኩል፡ ይህን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳችሁ ዘንድ፡ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ ለልጆቻቸው የሚያጫውቱት፡ አንድ የምሳሌ አነጋገር ስላለ፡ እርሱን ልጥቀስላችሁ! የእናንተ ወላጆች አላጫወቷችሁ እንደኾነ፡ የእኔዎቹ አጫውተውኛልና፡ ልንገራችሁ! ይኸውም፡ "ኹለት ጓደኛሞች፡ ከበረሃ መንገዳቸው ወርፈው ሣለ፡ አንደኛው፡ ከሌሊት እኝቅልፉ፡ በድንጋጤ ነቅቶ፡ 'አንተ ወንድሜ! ይህ የምሰማው ድምፅ፡ ምንድር ነው?' ብሎ፡ ጓደኛውን፡ በጎረነነ ቃል፡ በጨለማው ውስጥ ይጠይቀዋል፥ ፀጥታው፡ በዚያ ንግግር በመታወኩ፡ ተጠያቂው ተደናግጦ፡ በዘረጋው እጁ፡ ጠያቂውን እየጐነተለ፡ በለሳለስ የቍጣ ድምፅ፡ 'ኧረ ተው አንተ!? ዝም ብለህ፡ ወርፈህ ተኛ! ጅብ እኮ፡ አንድ እግሬን እየበላ ነው!' አለው።" የሚለው ነው።

እንግዴህ፡ በረቂቁ ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ የነጋሪት ድምፅ እየተሳለፈ ያለው፡ የዚያ፡ የአባቶቻችንና እናቶቻችን የአዋጅ ቃል ቁም ነገር፡ ለዚህ የኢትዮጵያ ትውልድ ባይሰማው፥ ወይም ሰምቶት ሊገባው ባይችል፥ ወይም ሊቀበለው ባይፈልግ፥ ወይም፡ ቸል ብሎና ንቆ፡ በማፌዝ ቢተወው፥ ከዚያም አልፎ ቢቃወመው፡ የበኩሌን ግዳጅ ልፈጽም ብዬ፡ ከቀደሙት ድርሰቶቼ ጋር፡ በዚህ፡ የአጋጣሚ ውይይት አማካይነት ደግሞ፡ ይህንኑ መልእክት፡ ለእናንተና ለዚሁ ትውልድ ለማሰማት፡ ይህን ዕድል በማግኘቴ፡ እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ። ይህንም ሳደርግ፡ *"ዘበ ዕዝን፡ ሰሚዓ ለይስማዕ!"*[ሚል] ማለትም፡ *የሚሰማ ጆሮ፥ የሚያስተውል አእምሮና የሚቀበል ልቦና ያለው ኹሉ፡ የተነገረውን የእግዚአብሔርን የእውነት ቃል፡ ይስማ! የሰማውን፡ በሃይማኖት አስተውሎ፡ ይቀበል! የተቀበለውንም፡ በምግባር ይፈጽመው!* የሚለውን፡ መለኮታዊ ቃል በመጥቀስ ነው።

በዚህ ረገድ፡ የሚቀረኝ የአገልግሎት ድርሻ ቢኖር፡ ባለኝ ዓቅም፡ ይኸው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ አባቶቹና እናቶቹ፡ እንዲያ የተሠዉላቸውን "ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን"፡ በእውነተኛ ገጽታቸውና ባሕርያቸው፡ እንዲያውቃቸው መርዳት ይኾናል። ካላወቃቸውማ፡ እንደእነርሱ፡ እስከሞት የሚያደርሰውን ሃይማኖታዊ መሥዋዕትነት፡ እንዴት ሊከፍል ይችላል? ስለዚህ "ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን"፡ በእውነተኛ ገጽታቸውና ባሕርያቸው፡ ለትውልዱ ለማሳወቅ፡ ይህ ውይይት፡ በዚህ መልኩ እንዲዘጋጅ አስፈለገ።

ጥያቄ፡- *ቀደም ብለህ ሰላመሳኸው፡ ስለ"ስምንተኛው ሺህ" አባባል፡ ጥቂት ብታስረዳን?*

መልስ፡- "ሰባት" ቁጥር፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል መሠረት፡ እግዚአብሔር፡ የዕቅድ ሥራውን የሚያከናውንበት የጊዜ ዓውድ ነው። ስለዚህ፡ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩበት፡ ሰባተኛው ሺ ዓመተ ዓለም ተፈጽሞ፡ ስምንተኛው የሚጀመርበት ጊዜ፡ 'ስምንተኛው ሺ' ይባላል። እርሱም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ የተከፈተውንና 'በፊተኛው የመንፈስ ትንሣኤ ዕድል ፈንታ ያላቸው'፡ እውነተኞቹ የክርስቶስ አገልጋዮች፡ ከእርሱ ጋር ነግሠው የሚቆዩበትን፥ በመጨረሻም፡ የዓመተ ምሕረቱ ኹለተኛው ሺ ከግብቃቱ በፊት፡ የጌታ ምጽአቱ የሚፈጸምበትን፡ 'ሺህ ዓመት' የተባለውን ቀዳማዊ ዘመን የያዘው ጊዜ ነው።።።

የኢትዮጵያዊነትን ምሥጢር ያወቀ፡
ለፍጹም ሕይወት ይበቃል!

ጥያቄ፡- *ይህን ኹሉ ሳናውቅ ለኖርነው፡ ለእኛ፡ በተለይ፡ ይህኛ ውይይታችንን በሚመለከት፡ እስካኹን ላቀረብናቸው ጥያቄዎቻችን፡ ያገኘነው መልስ አርክቶናል። በውይይታችን መጨረሻ ስለምናገኘው ጠቀሜታ፡ የምታበረክተን አስተያየት አለህ? ካለህ፡ ብታመላክተን?*

መልስ፡- ውይይታችንን፡ በእውነተኛ ሕሊናና በትክክለኛ መንፈስ እያስተዋላችሁ ከተከታተላችሁት፡ በመጨረሻ፡ ስለሚያድርባችሁ ስሜት፡ እኹኑት፡ በእርግጠኛነት ልነግራችሁ እችላለሁ።

ጥያቄ፡- *እዚህ ላይ፡ ቆይ እስኪ! ውይይታችን በሚያበቃበት ጊዜ፡ እኛ፡ በውስጣችን የሚሰማንን፡ አንተ፡ እንዴት፡ ከአኹኑ አውቀህ፡ አስቀድመህ፡ ልትነግረን ትችላለህ?*

መልስ፡- እኔን፡ አኹን እየተሰማኝ ያለውን ስሜት፡ ስለማውቀው ነዋ!

ጥያቄ፡- *አንተን፡ አኹን እየተሰማህ ያለው ስሜት፡ ምንድር ነው? እርሱንም ቢኾን፡ አንተ ማወቅህ፡ ለራስህ እንጂ፡ በእኛ ውስጥ ስለሚኖረው ስሜት፡ እንዴት ሊያሳውቅህ ይችላል?*

መልስ፡- እናንተና እኔ፡ በሰብአዊ ተፈጥሮአችን፡ አንድ ስለኾንን፡ ግለትም፡ በሥጋችን አካልና ባሕርይ፡ አንድ ዓይነት ኾነን እንደምንታይ ኹሉ፡ በነፍሳችን አካልና ባሕርይ፥ እንዲሁም፡ በመንፈሳችን አካልና ባሕርይ፡ አንድ ስለኾን፡ "በፍላጎታችን+ በምርጫችንና በውሳኔያችንም፡ አንድ ኾነን ልንገኝ እንችላለን!" ብዬ ስላሰብሁ ነው፣ ይህም፡ የእናንተ ፍላጎት+ ምርጫና ውሳኔ፡ የእኔን ከመሰለ ማለት ነው። ይህንም፡ ወደፊት በበለጠ ትረዱታላችሁ።

እንዲህ ከኾነ፡ አኹን፡ እኔን እየተሰማኝ ያለው ስሜት፡ እናንተንም፡ በዚያን ጊዜ ይሰማችኋል ማለት ነው። ያም፡ የሚሰማችሁ ስሜት፡ እኔን፡ ለፍጹሙ ሰላም፡ ደስታና ዕረፍት ያበቃኝን እውቀት በማግኘታችሁ የሚከሠት ይኾናል።

ጥያቄ፡- *ታዲያ፡ አንተ፡ ይህን ለመሰለው እውቀት በቅተህ፡ ይህን የመሰለው ስሜት ሊሰማህ እንዴት ቻለ?*

መልስ፡- መልካሙንና ክፉዉን፡ ለይቶ በሚያውቀው ሰብአዊ አእምሮዬ፡ በግሌ የምፈልገውን ለመፍቀድ፥ ለመምረጥና ለመከተል፡ በተፈጥሮ በተሰጠኝ፡ ፍጹም የመወሰን ሥልጣን፡ በበኩሌ፡ "መልካሙን"፡ ማለትም፡ የእግዚአብሔር የኾነውን ፈለግሁት፣ የፈለግሁትንም፡ በገዛ ፈቃዴ መረጥሁት፣ የመረጥሁትንም ልፈጽመው፡ በቁርጥ ወሰንሁ፣ የቈረጥሁበትንም፡ ይህን ውሳኔዬን፡ በሥራ ላይ ስላዋልሁት፡ እነሆ፡ ፍጹም ሰላምና ጸጥታ፥ ደስታና ዕረፍት፡ የእኔ ኾኑ! እዚህ ላይ፡ ይህን ጸጋ ያስገኙልኝ፡ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መኾናቸውን አትዘንጉ!

ስለዚህ፡ እናንተም፡ በዚህ ውይይት አማካይነት፡ የእግዚአብሔርን እውነት ካወቃችሁና ከተገነዘባችሁ በኋላ፡ ፍላጎታችሁ፥ ምርጫችሁና ውሳኔያችሁ፡ ያች እውነት ያስገኘችላችሁን እውቀት መቀበል ከኾነ፡ በዚያ እውቀታችሁ፡ ከወሳኒነት፡ ማለትም፡ ከጀማሪነት ተነሥታችሁ፡ ወደማእከላዊነት፡ ከዚያም፡ ወደፍጹምነት ትደርሳላችሁ፣ አስተሳሰባችሁም፡ ከሥጋዊነት፡ ወደነፍሳዊነት፣ በመጨረሻ፡ ለተቀደሰው መንፈሳዊነት ይበቃል። በዚህ ጊዜ፡ በውስጣችሁ፡ ልዩ የኾነ፡ መልካም ስሜት ይሰማችኋል፣ ያም ስሜት፡ ፍጹም ሰላምና ጸጥታ፥ ደስታና ዕረፍት፡ የእናንተ መኾናቸውን የሚያረጋግጥላችሁ <u>እውቀት</u> ነው።

ለዚህ እውነታ ማረጋገጫ የሚኾን ማስረጃን ለመፈለግ፡ ለምን፡ ሩቅ እንኼዳለን? በቅርብ የተፈጸመውን፡ ይህን የአኹኑን፡ የራሳችሁን አድራጎት ተመልከቱት! ይህ ውይይት፡ ሊከፈት የቻለው ለምንድር ነው? በቅድሚያ፡ እናንተ ወደእኔ ለመምጣት ስለፈለጋችሁ ነው፡ ከዚያም፡ ለመቅረብና ለመተዋወቅ ስለመረጣችሁ ነው፡ በመጨረሻም፡ ውይይቱ እንዲቀጥል ስለወሰናችሁ ነው። በሕይወታችን፡ ኹሉም ነገር፡ ኾኖ የሚገኘው፡ ይህን የኺደት ሥርዓት ስለሚከተል ነው።

እንግዲህ፡ ይህ ውይይታችን፡ በዚህ መልክ እንዲቀጥል የሚፈለገው፡ እናንተ፡ ይህን እውቀት አግኝታችሁ፡ ለዚህ መልካም ሕይወት እንድትበቁ ለማድረግ ነው። የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ያበረከተልኝን፡ ይህን እውቀት፡ ቀደም ብዬ ያገኘሁት እኔማ፡ ይህን እውቀት፡ ሕይወት አድርጌው እየኖርሁት ስለኾነ፡ ውይይቱ፡ ለእኔ ምን ያደርግልኛል፣ ለእኔ አያስፈልገኝም። የሚያስፈልጋችሁ፡ እናንተ ናችሁና፡ በጥያቄና መልስ የጀመርነውን፡ ይህንኑ ውይይታችንን፡ እስከመጨረሻው እንድትዘልቁበት እየመከርኋችሁ፡ መቅድማዊ ትንታኔዬን፡ በዚህ እፈጽማለሁ።

\+ + +

ምዕራፍ ፫

የኢትዮጵያዊነት ጥያቄ: መከፈቻው ቁልፍ፤

ማወቅ::

ጥያቄ:- *ስለ"ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት" ሐተታ: መነሻና መንደርደሪያ÷ መዳረሻም ለኹኑን የመቅድም ጥያቄዎቻችን: ተገቢዎቹን መልሶች: እንዲሀ ካጠቃለልሀልን÷ አኹን ደግሞ: ወደዋናው ትንተና ጠልቀን ገብተን: ምሥጢራቸውን: በበለጠ ለማወቅ የሚያስችለን ፍቱን ዘዴ: ምን እንደኾነ ብታመለክተን እንወድዳለን::*

መልስ:- በዚህ ውይይታችን: ዋና ጥያቄ ኾኖ የቀረበው "የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት" ነገር: በአንድ ትልቅ የተቆለፈ ግምጃ ቤት ውስጥ ታሽጎ እንደተቀመጠ የወርቅ ክምችት÷ ወይም ልዩ ቅርስ: ልናገኘው: በብርቱ የምንፈልገው: የተወደደና የከበረ÷ የተቀደሰና የማያልቅ ዘለዓለማዊ ሀብት ነው፤ ይህንኑም: እስካኹን በተለዋወጥናቸው አሳቦች እንደተረዳችሁትና በበለጠ እንደተገነዘባችሁት ተስፋ አደርጋለሁ:: እንዲህ ከኾነ: ይህን "የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት" ሀብት አግኝቶና ወስዶ: በእርሱ ለመጠቀም: በቅድሚያ: እርሱ ወደተቀመጠበት ግምጃ ቤት ኼዶ: ወደዚያ መግባት ያስፈልጋል፤ ወደግምጃ ቤቱም ለመግባት: የተቆለፈውን ጠንካራ የብረት በር መክፈት: ግድ ይኾናል፤ የተቆለፈውንም በር ለመክፈት: ቁልፉን መያዝ ያስፈልጋል፤ ያ ቁልፍ: "እውቀት" ነው:: ያም የእውቀት ቁልፍ: የራሱ: የመዝጊያው መክፈቻ የኾነው: ትክክለኛው ቁልፍ መኾን አለበት:: አለዚያ: በሩን ሊከፍተው አይችልም::

በዚያ: ትክክለኛ ቁልፍ: ያ: የእውቀት በር በተከፈተ ጊዜ ግን: *"ሕዝቤ: እውቀት ከማጣቱ የተነሣ: ጠፍቷል!"* የሚለው: የእግዚአብሔር የወቀሳ ቃል: ምላሽን ያገኛል፤ ደግሞም: *"የአቴና ሰዎች ሆይ! እናንተ: በኹሉ ነገር: እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ:: የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ: 'ለማይታወቅ አምላክ' የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቻለሁና:: እንግዲህ: ይህን: ሳታውቁ የምታመልኩትን አምላክ: እኔ እነግራችኋለሁ፤ ...እግዚአብሔር: ያለግውትን ወራት አሳልፎ: አኹን: በእየቦታቸው: ንስሓ ይገቡ ዘንድ: ሰውን ኹሉ ያዝዛል!"*[፴፪] የሚለው የሐዋርያው ቃል ይፈጸማል::

እንደማናቸውም ሌላው ነገር ኹሉ: "እውቀት" ወይም: "ማወቅ": ተቃራኒ ገጽታ አለው፤ እርሱም: "ድንቊርና" ወይም: "አለማወቅ" ነው፤ "ድንቊርና" ስል: የ"አእምሮ" ድንቊርና ወይም "አሳዋቂነት" ማለቴ ነው::

"እውቀት" ሲባልም፡ ኹለት ዓይነት ነው፤ ወይም፡ ኹለት መልክ አለው፤ ፩ኛው፡ "እውነተኛው እውቀት" ነው፤ ይኸውም፡ ከእግዚአብሔር የኾነው ነው፤ ፪ኛው፡ "ሓሰተኛው እውቀት" ነው፤ ይኸውም፡ ከዲያብሎስ፡ የኾነው ነው። እንግዲህ፡ "እውነተኛውን እውቀት" ያገኘና የያዘ ሰው፡ ራሱንና ሌላውን፡ እጅግ በጣም ጠቅሞ፡ እግዚአብሔርን ያስደስታል። "እውነተኛው እውቀት" የሌለው፥ ማለትም፡ በ"ድንቊርና" ያለ፥ ወይም፡ "አላዋቂ የኾነ" ደግሞ፡ ራሱን ብቻ ሳይኾን፡ ሌላውንም ጭምር ይጎዳል። ክፋትና ተንኰል የሌለበት "አላዋቂነት" ከኾነም፡ የእግዚአብሔርን ርኅራኄና ምሕረት ያገኛል። ነገር ግን፡ ባለማወቁ፡ እንደሞኝ ተቈጥሮ፡ የ"አዋቂው"ና የ"አዋቂ ነኝ!" ባዩ፡ መጫወቻና መጠቀሚያ ይኾናል። "ሓሰተኛውን እውቀት" ያገኘና የያዘ ሰውማ፡ ራሱንና ሌላውን፡ እጅግ ጎድቶ፡ እግዚአብሔርን ያሳዝናል፤ ዲያብሎስን ግን፡ ያስደስታል።

እንግዲህ፡ እናንተ፡ በየትኛው "የእውቀት ገጽታ" ውስጥ እንዳላችሁና የትኛውን ዓይነት "እውቀት" ይዛችሁ እንዳላችሁ፥ ወይም፡ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ ወደየትኛው እንደኾነ፡ እየራሳችሁን መርምሩ! በማስተዋልም ተመልከቱ! ይህንም፡ ለይታችሁ የምታውቁበት፡ የአእምሮው ኃይል፡ ከፈጣሪያችሁ፡ በተፈጥሮ ስለተሰጣችሁ፡ "አናውቅም!" ወይም፡ "እማወቅ ይሣነናል!" ልትሉ አትችሉም። ይህን ነገር፡ አስተውላችሁ የማመዛዘኑን ተግባር፡ በትክክል ከፈጸማችሁ፡ ማለትም፡ በ"እውነተኛው እውቀታችሁ" ከተጠቀማችሁበት፡ ወደእውነተኛው መልስ ትደርሳላችሁ፤ እውነተኛውም መልስ፡ ዛሬ፡ በእናንተ፥ በእየቤተ ሰባችሁና በአገራችሁ ላይ፡ ይህ ኹሉ የፈተና እሳት የሚነድደው፥ ይህም ኹሉ፡ የመከራ ማዕበል የሚወርደው፡ "ለምን እንደኾነ"፡ በግልጽ ይነግራችኋል፤ ለዚህም፡ ፍቱን መድኃኒቱ፡ ምን እንደኾነም ያስታውቃችኋል።

ከዚህ በኋላ፡ ከሚያቃጥላችሁ እሳትና ከሚያንገላታችሁ ማዕበል ለመዳን፡ መድኃኒቱን ወስዳችሁ፡ በመምሪያው መሠረት፡ መጠቀም፥ ወይም፡ ላለመዳን ከወሰናችሁ ደግሞ፡ መድኃኒቱን አለመውሰድ፡ በእየግላችሁ፡ የእናንተ፥ በጋራም፡ የየቤተ ሰባችሁ፥ ወይም በአገር ደረጃ፡ የሕዝቡ ፍላጎት፥ ምርጫና ውሳኔ ይኾናል። በ"እውነተኛው እውቀት" መጠቀምን ትታችሁ፡ "በአላዋቂነቱ" መጽናትን፥ ወይም፡ ለ"ሓሰተኛው እውቀት" መገዛትን ከመረጣችሁ፡ ጎዳቱና ጥፋቱ እንዲቀጥል መስማማታችሁ ነውና፡ የሚጠብቃችሁ ጽዋ፡ ፈልጋችሁና ወድዳችሁ የመረጣችሁትን፡ የየዕድላችሁን ፍጻሜ መቀበል ብቻ ይኾናል። የማወቅ ወይም የአለማወቅ ጉዳይ፡ በእየግል ሕይወታችሁ፥ በቤተ ሰብ ኑሮአችሁና በአገራችሁ ህልውና ላይ፡ የቱን ያህል፡ ታላቅ ወሳኝነት ያለው፡ የሞት ወይም የሕይወት ቁም ነገር መኾኑን ተገንዝባችሁ፡ አስፈላጊውንና ተገቢውን፡ የማል ውሳኔ፡ በሕይወተ ሥጋ እያላችሁ፡ አኹኑኑ መስጠት፡ የእናንተ ፋንታ ነው።

ይህን እውነታ፡ በተለይ፡ በአለንበት፡ በዚህ ዘመን፡ ለራስ ለመረዳትና ለሌላው ለማስረዳት፡ እጅግ ቀላል ኾኖ ይገኛል፤ ምክንያቱም፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ ላይና በኢትዮጵያውያን ዘንድ፡ እየተካሔደ ባለው ኹኔታ፡ እውነታውን በገሃድ ለማሳየትና በተጨባጭ ለማረጋገጥ ስለሚቻል ነው።

ምዕራፍ ፫
የኢትዮጵያዊነት ጥያቄ፡ መክፈቻው ቍልፍ፡ ማወቅ።

የአኹኑ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ በሥጋዊው ኾነ፡ በመንፈሳዊዉ ረገድ፡ አንዲህ፡ የችግር ዅሉ መከማቻ ኾኖ፥ በመከራ ማጥ ውስጥ ተዘፍቆም፡ ሊማቅቅ የሚታይበት ጠንቅ፡ ከቶ ምን ይመስላችኋል? ደግሞስ፡ የባለጋራዎቹና የጠላቶቹ፡ ጥሩ ዒላማ፥ የባዕዳንና የወገኖቹም መጫወቻ ኳስ የኾነው በምን ምክንያት ይመስላችኋል? አዎን! ጠንቁ፥ ምክንያቱ፡ አንድ ነገር ብቻ ነው፥ እርሱም፡ <u>ድንቍርና፡</u> ወይም፡ <u>***አላዋቂነት*** ነው።</u>

"ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው፡ ይህ ትውልድ፡ <u>***ሃይማኖቱን ስለማያውቅ አይደለምወይ፡*** እንዲህ፡ ዲያብሎስና ሠራዊቱ፡ በአምልኮ ባዕድ እየጠለፉና እያጠመዱ፡ የሚጫወቱበት? የቃል ኪዳን አምላኩ ኾኖነው፡ ከፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስና የቃል ኪዳን እናት አኀሩ ኾኖነችው፡ ቅድስት ድንግል ማርያምም ሊለዩት የቻሉት፥ ባዕዳን ሰባኪዎችም፡ በቀላሉ፡ ከሃይማኖቱ እያነዋወጹ፡ የአነርሱ ጥገኛና ተከታይ ሊያደርጉት የቻሉት፡ ***ሃይማኖቱን ስለማያውቅ አይደለምወይ?*** በረቂቅ እና/ወይም በግዘፍ የሚመጣበትን ወራሪ ጠላት ተቋቁሞ መመለስ ያልቻለው፥ እንዲያውም፡ ራሱን፡ ለጠላቱ አሳልፎ በመስጠትና በማስገዛት፡ የባርነት ቀንበር፡ እንዲህ የሚፈራረቅበት፡ ማንነቱን በትክክል ስለማያውቅ፥ ማለትም፡ <u>***እናቱን ኢትዮጵያንና የሚኖርበትን ኢትዮጵያዊነቱን ስለማያውቅ አይደለምወይ?***</u>

ይኸው፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው ትውልድ፡ ማንነቱን የሚያሳዩትንና የሚያረጋግጡለትን፡ ሃይማኖቱን ኢትዮጵያንና ሕይወቱን ኢትዮጵያዊነትን፡ በእውነት አውቆ ቢኾንማ ኖሮ፡ የእግዚአብሔር፡ ስመ ሳይቀር፡ እንዳይጠራ ከሚያደርጉት፡ capitalism (ካፒታሊዝም = ሥነ ንዋይ) እና democracy (ዲሞክራሲ= ሕዝባዊ አገዛዝ) ከሚሉት አንሥቶ፡ "እግዚአብሔር የለም!" እስከሚለው scientific socialism (ሳይንቲፊክ ሶሻያሊዝም = ሥነ እውቀታዊ ኅብረሰባዊነት) እና communism (ኮሚዩኒዝም = የጋርዮሽ ሥነ ህልውና) ድረስ ያሉትን፡ የባዕዳንን የአገዛዝ ቀንበሮች፡ እንዲህና እንዲያ፡ ሰጥ፡ ለጥ ብሎ፡ በእየተራ ይቀበል ነበርን? አይቀበልም።

ሃይማኖታቸውንና ማንነታቸውን ያወቁት፡ ለምሳሌ፡ ሩቅ ሳንኼድ፡ ከሚዋሰኑን ጎረቤት አገሮች፡ ሱዳንን፡ ኬንያን፡ ጂቡቲንና ሱማልያን፥ ወይም፡ በአካባቢያችን ካሉት አህጉር፡ ዑጋንዳን፡ የመንን፡ ሳዑዲ ዐረቢያን፡ ግብፅን፡ እስራኤልን፡ ወይም፡ በሩቁ፡ ከሚገኙት፡ ሕንድንና ጃፓንን፥ ብራዚልንና አርጀንቲናን ከመሰሉት ሕዝቦች መካከል፡ የትኛው አገር፡ ወይም ሕዝብ ነው፡ እንደሣሬው፡ የኢትዮጵያ ትውልድ፡ ሃይማኖቱንና ማንነቱን ክዶ፡ እነዚያን የአገዛዝ "ሥርዓቶች" የተቀበለ? አንድም የለም። ለምን?

<u>የእነዚህ ዅሉ አገሮች፡ የያንዳንዳቸው ትውልዶች፡ ሃይማኖታቸውንና ማንነታቸውን፡ ከሕማንነታቸው ጀምረው፡ ጠንቅቀው ስለተማሩና ስላወቁ ብቻ ነው። እነርሱ፡ ሃይማኖታቸውንና ማንነታቸውን ሳያስነኩ፡ እንደጠበቁ ይዘው፡ የባዕዳኑን ሥርዓት፡ ለእድገታቸውና ለልማታቸው፡ መሣሪያ አድርገው ተጠቀሙበት እንጂ፡ ሃይማኖታቸውን አልካዱም፥ ማንነታቸውንም፡ አልለወጡም።</u>

ይህ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ግን፡ ሃይማኖቱንና ኢትዮጵያዊነቱን ካለማወቁ የተነሣ፡ በጦር መወረር ሳያስፈልገው፡ በቀላሉ፡ በወሬ ተፈትቶ፥ እኒህን የተቀደሱ ውርሶቹንም አጥፍቶ፥ ራሱንም፡ በክህደትና በዓመፅ ደምስሶ፡ ሰውነቷን፡ ለማንም ወንድ ገልጣ እንደምትሰጥ፥ ማንነቷ እንደማይታወቅ፡ ሃይማኖተ ቢስ ጋለሞታ፡ የባዕዳኑን የአገዛዝ ሥርዓት፡ "አሜን" ብሎ፡ በአመንዝራነት እየቀያየረ የሚቀበል በመኾኑ፡ እነሆ፡ ለችግርና ለድህነት ተዳርጎ ይገኛል። እንዲህ፡ በድንቁርና ወይም በአላዋቂነት ጨለማ ውስጥ ተውጦ፡ የተለያዩ የክፉ ሰዎችንና የሰይጣናትን ቀንበሮች በመሸከሙ፡ በተፈጥሮ የተሰጠው፡ የእውቀት፥ የማስተዋልና የማመዛዘን ኃይሉ ሳይቀር፡ ተለየው። ከዚህ የተነሣ፡ "ከሺ ፈረሰኛ፥ አንድ ወሬኛ!" "ጦር ከፈታው፥ ወሬ የፈታው!" እንደሚባለው፡ በወሬ መፈታት ብቻ ሳይኾን፡ ራሱም፡ ወሬኛና የወሬ ቋት፥ ሓሜተኛና የሓሜት መቀፍቀፊያ ኾኖ፡ ራሱንና ወገኑን፥ የራሱ የኾነውንም ኹሉ በሚጎዳ ግብር ተጠምዶ የሚውል ኾነ። ስለሃይማኖቱና ማንነቱ፡ ለማወቅ የሚያስችለውን ትምህርት፡ በቀለለ መንገድና ዘዴ ለመማር ቀርቶ፥ ወይም፡ ስለዚሁ ቁም ነገር ተዘጋጅቶ የቀረበለትን መጽሓፍ አንሥቶና ገለጥ አድርጎ ለማንበብ ቀርቶ፥ ቍጭ ብሎ፡ በቁም ነገሩ ላይ ለመነጋገር፥ ለመጠያየቅና ለመወያየት እንኳ፡ ያልቻለ፡ ሰነፍ ትውልድ ኾኖ ከመመደብ ደረሰ።

እናንተን ሊጠቅማችሁ ይችላልና፡ <u>በማወቅና በአለማወቅ</u> መካከል ስላለው ልዩነት፡ በራሴ ሕይወት የደረሰውንና በግዙፍ ማስረጃ የተረጋገጠውን እውነታ፡ እስኪ፡ አጠቃልዬ፡ ባጭር ቃል ልግለጽላችሁ! ይህ፡ ዛሬ፡ "አብዮት" ተብሎ፡ ከመስከረም ወር፥ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. አንሥቶ፡ በኢትዮጵያ ምድርና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ፡ እየነደደ ያለው የፈተና እሳትና እየወረደ ያለው የመከራ ማዕበል፡ መቀጣጠልና ማጥለቅለቅ በጀመረበት ጊዜ፡ ከእሳቱና ከማዕበሉ ጽናት ጠርቶ የወጣ፡ አንድ አዲስ ቍምነገር ተከሥቶልኝ አገኘሁ። ይህም የቍምነገር ክሥተት፡ ከፈተናውና ከመከራው በፊት የነበረው **<u>የማወቁ</u> መጠን፡ <u>ከአለማወቁ</u> የሚበልጥ ይመስለኝ የነበረው ቀርቶ፡ ከማወቁ ይልቅ፡ ለካስ በልጦ ይገኝ የነበረው፡ አለማወቁ መኾኑን መረዳቴ ነው።**

ይህ እውነታ፡ ለእኔ የተገለጠበት ኹኔታ፡ እንዲህ ነበር። በመጀመሪያ፡ በሥጋ፡ ከአንድ አብራክና ከአንድ ማሕፀን ከተወለድኋቸው አንሥቶ፡ እስከሰባተኛው የትውልድ ሓረግ ድረስ ከተዛመድኋቸው፡ የሥጋ ዘመዶቼ፥ ቀጥሎ፡ በአንድ ሰበካ ውስጥ፡ አብሬአቸው ተወልጄ፥ አድጌና ተጫውቼ፡ በጉርብትና ከኖርኋቸው ባልንጀሮቼ አንሥቶ፡ በትምህርት ቤትና በሥራው ዓለም እስካፈራኋቸው ጓደኞቼ ድረስ ከተወዳጀኋቸው ወዳጆቼ፥ በመጨረሻ፡ በዘመኑ የመንግሥታችን አስተዳደር፡ ሕዝባዊ፥ ሥጋዊና መንፈሳዊ ዘርፎች ውስጥ፡ አብሬአቸው ካገለገልሁት፡ ከተራ ሠራተኛው አንሥቶ፡ እስከላይኛው ባለሥልጣን ድረስ ካወቅኋቸው የሥራ ባልደረቦቼ መካከል፡ ምናልባት፡ በጣት የሚቈጠሩ፡ እጅግ ጥቂቶች ከሚኖሩ በቀር፡ ኹሉም፡ ከዚያ "አብዮት" ጀምሮ፡ የክህደቱ፥ የዓመፁና የምንዝርናው ኃጢአት ተካፋይነታቸውን፥ በአምልኮ ባዕድ ርኵሰት ሳይቀር መበከላቸውንና ከዚህም ተግባራቸው፡ በንስሓ ለመመለስ፡ እምቢተኝነታቸውን በይፋ መስክረው አገኘኋቸው።

በዚህ ክሥተት፡ በእኔ በኩል፡ እስከዚያን ጊዜ ድረስ፡ "እውቀዋለሁ!" ብዬ ተማምኜበት የነበረው፡ የዘመዶቼ፥ የወዳጆቼና የሥራ ባልደረቦቼ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትና ምግባር፡ ከዚያ በኋላ፡ ፈጽሞ ተለውጦ በማየቴ፡ በእውነት የማውቃቸው መስሎኝ፡ "እንዲህ ናቸው!" ብዬ፡ ራሴ አምኜ፡ ሌሎችን አሳምንበት የነበረው የማወቁ መጠን፡ እውነትና ትክክል መኾኑ ቀርቶ፡ "ለካስ፡ አላውቃቸውም ኖርዋልና!" ብዬ፡ የአስተሳሰቤን ሚዛን፡ ወደአለማወቁ መጠን እንዳዛንፈው ከተገደድሁበት ደረጃ ደረስሁ፥ እነሆም፡ <u>በማወቅና ባለማወቅ</u> መካከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ ቻልሁ። ምናልባት፡ እነርሱም፡ ከዚያን በፊትና በዚያን ጊዜ፥ ከዚያም በኋላ፡ እኔን አውቀውበት የነበረው እውቀታቸው፡ እኔ "ያውቁኛል!" ብዬ በማስበው ግልጽነቱ ሳይኾን፡ በሌላ መልክ ሊኾን እንደሚችልም ገመትሁ። ከዚህ የተነሣ፡ በእነርሱም ዘንድ ያለው፡ እኔን የማወቁና ያለማወቁ መጠንና ዓይነት፡ በዚሁ መልክ ሊዛባ ይችል ይኾናል ብዬ አሰብሁ። "ሰውን፡ ውደደው እንጂ፡ አትመነው!" የሚለው፡ የአበው ይትብሃል፡ ትክክለኛ ትርጉሙ የገባኝም፡ በዚያን ጊዜ ነበር። ይህን በሚመለከት፡ ብዙዉን ሓተታ፡ በሌሎቹ ድርሰቶቼ ውስጥ፡ ገላልጬዋለሁና፡ ያን፡ ልትመለከቱ ትችላላችሁ።

እውነተኛው እውቀትና እውነተኛው አዋቂ!

ጥያቄ፡- "እውነተኛውን እውቀት አግኝተን፡ ከማናቸውም ዓይነት ገሃነት ለመዳን የምንችለው፡ እንዴት እንደኾነ፡ እባክህ፡ መንገዱን ብታሳየን?

መልስ፡- በዚህ፡ ታላቅ ወሳኝነት ባለው፡ የሞት ወይም የሕይወት ቁም ነገር ላይ፡ በጥልቀት ለመነጋገር፡ አንድ *መሠረታዊ* መርህን ልጠቅስላችሁ እሻለሁ፡ እርሱም፡ "ቀዳሚሃ ለጥበብ፡ *ፈሪሃ እግዚአብሔር*!" ማለትም፡ "እግዚአብሔርን *መፍራት*፡ የጥበብ *መጀመሪያ* ነው!"[፵፮] የሚለውን ሕያው ቃል ነው።

ይህ ቃል፡ በሰው ልቦና ሲታሰብ፡ በአንደበት ሲነገርና በብዕር ሲጻፍ፡ ዝንተ ዓለም ተኑሮ፡ ከዛሬዪቱ ጊዜ ተደርሷል። አዎን! በሌላ አቀራረብ፡ "እግዚአብሔርን መፍራት፡ የእውቀት *መጀመሪያ* ነው!" ቢባል፡ ያው ነው፡ "የትምህርትና የእውቀት፡ የብልሃትና የጥበብ፥ በአጠቃላይ፡ የመልካም ሕይወትና የጥሩ ሥልጣኔ ምንጩና መሠረቱ፡ መጓንጎሪውና መዳረሻው፥ መጨረሻውና ገሃላቱም፡ እግዚአብሔርን መፍራት" ማለት መኾኑ፡ በግልጽ ይታወቃል። "እግዚአብሔርን መፍራት" ማለት፡ እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ነው፡ ማንኑቱን፡ በእውነት፡ ስታውቁ፡ ትወድዱታላችሁ፥ ታምኑታላችሁ፡ የምትፈሩት፡ በዚህ ፍቅራችሁና እምነታችሁ ይኾናል።

ታዲያ፡ ከምሁሩና ከደቀ መዝሙሩ÷ ከተናጋሪውና ከአድማጩ÷ ከጸሓፊውና ከአንባቢው መካከል፡ ስንቱ፡ ጎሊና ያለው አእምሮ ነው፡ አስቦ÷ ስንቱ፡ ጆሮ ያለው ሰሚ ነው፡ አዳምጦ÷ ስንቱ፡ ዓይን ያለው ተመልካች ነው፡ አስተውሎ፡ *ለመልካም ሕይወትና ለጥሩ ሥልጣኔ፡ መርህ የሾነውን፡ ይህን፡ "እግዚአብሔርን መፍራት፡ የእውቀት መጀመሪያ ነው!" የሚለውን ኃይለ ቃል* በእውነት ያመነበትና በተግባር ላይ አውሎ፡ ለፍሬ ያበቃው? ይህ ሉዓላዊ ቃል፡ "እግዚአብሔርን *አለመፍራት፡ የጥበብ መጀመሪያ ነው!*" በሚለው፡ በተቃራኒው ሰይጣናዊ ገጽታው እንደተወሰደ በሚያስመስል ይዞታ፡ እስካኹን ሲሠራበት እንደኖረ ኹሉ፡ አኹንም እየተሠራበት ያለ በመኾኑ፡ በይበልጥ ለመራራው እንጂ፡ ለጣፋጭ ፍሬነት አለመብቃቱን፡ ዓለም፡ አኹን የሚገኝበትን፡ ገሃድ የኾነውን አሳዛኝና አስደንጋጭ ኹኔታ የሚከታተል፡ ማናቸውም ቅን ሰው፡ በቀላሉ ይገነዘበዋል፤ ለዚያውም፡ እውነተኛና አስተዋይ ተመልካች ካለ፡ ማለት ነው። አምን÷ በመዝሙረ ዳዊት፡ *"ከሰው ልጆች መካከል፡ የሚያስተውል÷ እርሱንም የሚፈልገው እንዳለ ያይ ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በሰማይ ኾኖ፡ ወደሰው ልጆች ተመለከተ!"*[ሸ] ተብሎ፡ ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ሲነገር የኖረው ብሂል፡ ዛሬም፡ እነሆ፡ በቋኛው ሽህ ቀጥሏልና።

እንዲህ ከኾነ፡ "ያን ኃይለ ቃል፡ በትክክለኛ ገጽታው አምነውበት በሚከተሉት ዘንድ ላይቀር፡ እውነተኛ ትርጉሙና ትክክለኛ ተግባራዊነቱ፡ እንደአዲስ፡ ሊያጠያይቅ ካስፈለገበት ዘመን ላይ ደርሰናል!" ቢባል፡ ከእውነት መራቅ አይኾንም። ይህም አዲሱ አጠያያቂ ርእስ፡ "እግዚአብሔርን ለመፍራት እኮ፡ ያ፡ እርሱን ሊፈራው የሚገባው ፍጡር፡ አስቀድሞ፡ እግዚአብሔርን ሊያውቀው ያስፈልገዋል!" በሚል አጭር ቃል ይጠቃለላል። በተብራራ አገላለጽ፡ "ያ ፍጡር፡ እግዚአብሔርን ይፈራው ዘንድ፡ በቅድሚያ፡ የእግዚአብሔርን መኖር ሊያምንና ከዚያ በኋላም፡ ያ፡ ያመነበት እግዚአብሔር፡ ማ መኾኑን፡ *በእውነት ያወቀ* መኾን አለበት!" ማለት ነው።

ጥያቄ፡- *"ያ ፍጡር" የምትለው፡ እርሱ፡ ማነው?*

መልስ፡- አንተ ነሃ! አንቺ ነሽ!

ጥያቄ፡- *እኛ ከኾንማ፡ "የእግዚአብሔርን መኖርና ማንነቱን፡ በእውነት ማወቅ እንዴት ነው?" ብለን እንጠይቅሃ?! ይህ ነገር፡ ምሥጢሩ ጥልቅ÷ አሳቡ ምጡቅ÷ ምርምሩም ረቂቅ ስለኾነ፡ "እንደእኛ ላለ፡ የማወቅ ኃይሉ፡ ውሱን ለኾነበት ፍጡር፡ ከዚህ ከላቀው እውቀት ለመድረስ፡ እንደምን ይቻለዋል? ከየት ተነሥቶ? በየት በኩልስ አልፎ? የለም! ፈጽሞ አይቻለውም!" ብለን ብንደመድመው ይሻለናል። አንተ፡ ስለዚህ ነገር፡ ምን ትላለህ?*

መልስ፡- በእየጎሊናችሁ ባሕር ውስጥ፡ በተፈጥሮ የተነሣሣውን፡ ይህን ተገቢ የሁከት ማዕበል፡ በዚህ፡ አጉል በኾነው የየግላችሁ ድምዳሜ ለማረጋጋት ለሞከራችሁት፡ ለአንተና ለአንቺ፥ እናንተንም ለመሰለው ሰብአዊ ፍጡር፡ ይህን እላለሁ! "ተሳስተሃል! የሌለ ፍርሃት፥ የሌለ ጭንቀት፥ የሌለ ችግር፡ ራስህ ፈጥረህ፥ በራስህም ላይ የምትሐት ቀንበርን ተብትበህ፡ ራስህን፡ ለዚያ፡ አንተው ለፈጠርኸው ፍርሃት፥ ጭንቀትና ችግር፡ ባሪያ አድርገህ ስላስገዛኸው፡ ይህን ነገር፡ አንተው፡ በገዛ ራስህ አስተሳሰብ፡ በጥልቀት ሠወርኸው፥ በምጥቀት አራቅኸው፥ በምርምር አረቀቅኸው፥ በእውቀትም አከበድኸው እንጂ፡ እጅግ ቀላልና ገሃድ፥ ቅርብም ነው! ስለዚህ፡ ሓትፍራ! ሓትጨነቅ! ሓትሥጋ! ሓትጠበብ! ሓትራቀቅ! ሓትመሣጠር! ሓትፈሳሰፍ! <u>እግዚአብሔርን ለማወቅ፡ መርሁ፡ ብርሃን፥ መንገዱም ቀና ነው፤ እኒህ</u> መርህና መንገድ የተባሉት ይዘቶች፡ በተፈጥሮህ፡ ያንተው ገንዘቦችህ ኾነው፡ በውስጥህ ታገኛቸዋለህ። <u>የራስህን ተፈጥሮ፡ በራስህ በማወቅ፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ እንድትችል፡ ችሎታው፡ በተፈጥሮ ተሰጥቶሃልና።</u> ይህም የኾነው፡ አንተ፡ እርሱን እንድታውቀው በሚፈልገው፡ በእርሱው፡ በራሱ፡ በፈጣሪህ ቸርነት ነው። በተፈጥሮ በተሰጠህ፡ በዚህም ጸጋ፡ እጅግ ደስ ይበልህ!"

ራስን በማወቅ፡ እግዚአብሔርን ማወቅ!

ጥያቄ፡- *ይህ አባባልህ ረቀቀብን! <u>እየራሳችንን በማወቅ፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ስለዚህ ነገር፡ እስኪ፡</u> ጨማምረህ አብራራልን?*

መልስ፡- አዎን! ራስን ማወቅ፡ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ስለዚህ፡ "እግዚአብሔርን ለማወቅ፡ በቅድሚያ፡ ራስን ማወቅ ያስፈልጋል፣" ቢባል እውነት ይኾናል። ራስንም ማወቅ፡ እንዲያውም፡ እግዚአብሔርን ከማወቅ በፊት፡ የተፈጥሮ ወገን የኾነውን፡ ሌላውን ሰው ለማወቅ ያስችላል። ይህም ማለት፡ አንድን ግለሰብ፡ የማወቅ ፍጹም ፍላጎቱን የሚያፈልቀው ምንጭ፥ የሚያፋሰሰው አሸንዳና የሚያጠራቅመው ገንዳ፡ ያው፡ "እኔ" የሚለው ኹለንተናዊ አካሉ ሲኾን፡ ይህን፡ "እኔ" የሚለውን፡ የራሱን ሰብአዊ ህልውና፡ ያ ግለሰብ፡ ራሱን በራሱ ለማወቅ ይችል ዘንድ፡ በቅድሚያ፡ "በመንፈሳዊው የእውቀት ኃይል፡ ራሱን ማንቃት፥ ማነሣሣትና ማንቀሳቀስ ያስፈልገዋል!" ማለት ይኾናል።

በሌላ አባባል ልግለጽላችሁ! እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ በየዕለቱ ሌሊት፡ ወደሥጋዊው የእንቅልፍ ዓለም፡ በጊዜያዊው ሞት እየተወሰደ፡ እንደሬሳ ተዘርግቶ ካደረ በኋላ፡ ከዚያ እንቅልፉ፡ በነፍስ ሕያው ኃይል ተቀስቅሶ እንደሚነቃ ኹሉ፡ እንዲሁ ደግሞ፡ "ይኸው ሰብአዊ ፍጡር፡ ከዚህኛው፡ ከነፍሳዊው የእንቅልፍ ዓለም፡ በመንፈሳዊው የእውቀት ኃይል ተቀስቅሶ፡ መንቃት አለበት፥" ማለት ነው።

በሥጋዊው እንቅልፍና በነፍሳዊው እንቅልፍ መካከል ያለው ልዩነት፡ ሥጋዊው እንቅልፍ፡ በሕልም ጨለማ ተውጦ፡ በጽሙና የሚያሳልፉት ሲኾን፡ ነፍሳዊው እንቅልፍ ግን፡ በእውን ብርሃን ተጋልጦ፡ በገሃድ የሚካሼድ መኾኑ ነው። ይህም፡ "ያ ሰብአዊ ፍጡር፡ በእውን ከሚገኝበት፡ ከዚህ የነፍስ እንቅልፋምነቱ፡ በራሱ መንፈሳዊ የእውቀት ኃይል፡ ራሱን ቀስቅሶ፡ እውነተኛውን ንቃት ማግኘት አለበት፡" ማለት ነው።

ያለዚያ፡ ራሱን፡ ለዚህ ዕድል አስካላበቃ ድረስ፡ ራሱም፡ ገና፡ በጽኑ የድንቁርና ጨለማ ተውጦና የመዋቲ አስከሬኑን ተሸክሞ፡ በቅዠት ድንግዝግዝ ውስጥ እየዳከረ የሚደናበር አሳዛኝ ፍጡር ኾኖ ይቀራል። ለራሱ ግን፡ በእውኑ ያለና የሚያስብ፡ የሚንቀሳቀስም ይመስለዋል፡ ህልውናው ከንቱ፡ ዓለሙም፡ "ምትሐት" መኾኑን አላወቀውም።

ጥያቄ፡- ታዲያ፡ እየራሳቸንን፡ "እኔ" ብለን የምንጠራው እኛ፡ በእየራሳችን እኔነት ብቻ፡ ይህን እውነታ፡ በእርግጥ፡ እውን ማድረግ እንችላለንን? የምንችል ከኾነስ፡ የሚቻለን እንዴት ነው?

መልስ፡- አዎን! ትችላላችሁ። ይህን ለማድረግ የምትችሉት ደግሞ፡ ውሳጣዊዉን እየራሳችሁን፡ በእርሱም አማካይነት፡ አፍአዊ የኾነውን፡ ሌላውን መሰል ፍጡርና የኹሉ ፈጣሪ የኾነውን እግዚአብሔርን ጭምር የማወቁ ችሎታ፡ እንደእሳተ ገሞራ፡ በእየራሳችሁ ሰውነት ውስጥ ተዳፍኖ የሚገኝ መኾኑን፡ በእርግጥ ወደማስተዋሉ መድረሳችሁን ስትገነዘቡ ነው። እየራሳችሁን፡ ለዚህ እውቀት ካበቃችሁ፡ መለኮታዊው የሥነ ፍጥረት ምሥጢር ተከሠተላችሁ ማለት ነው። እንዲህ ከኾነም፡ ይህን ምሥጢር፡ በራስ ብቻ የማወቁ ችሎታ፡ "ዕውቀ ድንቅ" ይባላል። ሌላ አስተማሪ ወይም መሪ ሳይኖር፡ ራስን በራስ የማወቅ፡ ሌላውንም የማወቅ፡ ፈጣሪንም የማወቅ ችሎታ፡ በራስ ሰውነት ውስጥ የመኖሩ ምሥጢር፡ እውን ኾኖ መገለጡ፡ እውነትም፡ እንዴት ዕውቀ ድንቅ ነው!? ለዚህ፡ ከፈጣሪ፡ በጸጋ ለተገኘ የተፈጥሮ ችሎታ፡ ታላቅ አንክሮ ይገባል!?

ያ፡ ራስን በራስ ለማወቅ፡ በዚያም አማካይነት፡ "እግዚአብሔር" የምንለውን የ"ሥነ ፍጥረት" ፈጣሪና ባለቤት፡ ሌላውንም ፍጡር ለማወቅ የሚያበቃችሁ ችሎታ፡ ምን እንደኾነ፡ የት እንደሚገኝና እንዴት እንደሚሠራ፡ ይህንም ኹሉ፡ በተፈጥሮ የታደላችሁ መኾናችሁን የሚነግራችሁ፡ በእየሰውነታችሁ፡ የነፍስ አካል ውስጥ፡ እርሱ እግዚአብሔር፡ በጥበቡ ሠርቶ ያኖረውና ዘወትር የማይለያችሁ፡ "ጎሊና" የሚባለው፡ የየራሳችሁ ረቂቅ ተፈጥሮ ነው።

እርሱም፡ ይህን እውነት፡ ይህን እውቀት፡ በእየጎሊና ጆሮአችሁ ሲያሰማችሁ፡ በእየጎሊና አንደበታችሁ ሲያናግራችሁ፡ በእየጎሊና እጆቻችሁ ሲያስዳስሳችሁና ሲያስጽፋችሁ፡ በእየጎሊና ዓይኖቻችሁ ሲያሳያችሁና ሲያስነብባችሁ፡ በእየጎሊና ምላሳችሁም እንድታጣጥሙ ሲያደርጋችሁ ታገኙታላችሁ።

ምዕራፍ ፫፡
የኢትዮጵያዊነት ጥያቄ፡ መክፈሻው ቍልፍ፡- ማወቅ፤ ራስን በማወቅ፡ እግዚአብሔርን ማወቅ!

ይህ ብቻ አይደለም። ለሰውነታችሁ፡ ውሳጣዊና አፍአዊ ህልውና ተብሎ፡ ለቅጽበት ሳይቋረጥ፡ በምትተነፍሱት አየር÷ በምትጠጡት ውኃ÷ በምትሞቋትና በምታበራላችሁ ፀሓይ÷ በምትኖሩባት መሬት አማካይነት፡ ያለምንም ዋጋ፡ በተፈጥሮ በሚቀርብላችሁ የምግብ ሥርዓት ውስጥ፡ ይህ እውነታ፡ በግዘፍ ተከሥቶ ሲሠራ ይገኛል። ይህም፡ በሚከተሉት ኹኔታዎች ተረጋግጠ ይታወቃል፡-

፩ኛ፡- ሥጋዊው ፍጡር፡ ሕያው ኾኖ፡ በህልውናው እንዲቀጥል የሚያደርገውና ያለማቋረጥ፡ እየጐረፈ፡ በምልዓት ደርሶት የሚተነፍሰው፡ የሕይወት እስትንፋስ በኾነው አየር አማካይነት፡ ያ ፍጡር፡ የሥነ ፍጥረት ምንጭ ከኾነው፡ ከፈጣሪው ጋር፡ በቀጥታ መገናኘቱ÷

፪ኛ፡- ዳርቻውን፡ ሥጋዊ ፍጡር ሊደርስበት በማይቻለው የጠፈር ጎዋ ውስጥ መጥቃ በምትገኘው÷ በአካሏ ክበብ÷ በብርሃኗ ፀዳልና በሙቀቷ ርቅቀትም፡ እያንዳንዱን ፍጡር፡ ወደታች በምትመለከተውና ከኹሉ በምትደርሰው ፀሓይ አማካይነት፡ ያ ፍጡር፡ በሰማይ ዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፈጣሪ ፊት፡ ራሱን፡ ሊሸሽግ በማይቻለው ኹኔታ፡ ተጋልጦ፡ በገሃድ መታየቱ÷ እርሱም፡ ፈጣሪውን፡ በግዘፍ ማየቱና መገናኘቱ÷

፫ኛ፡- ሥጋዊ ፍጡሩ፡ የሚበላውንና የሚጠጣውን÷ የሚለብሰውንና የሚኖርበትን ሲሳይ፡ አሥርፃና አብቅላ÷ በዝናብ አርክታና አሳድጋ÷ በነፋስ ዘርዝራና አለምልማ÷ በፀሓይ አብስላና አጣፍጣ በምትሰጠው÷ በላይዋም ተፈጥሮ በሚኖርባትና ሕያው ኾኖ በቆመባትና በውኃ በእናችው መሬት አማካይነት፡ ያ ፍጡር፡ በሚንቀሳቀስበት ሕይወት፡ ከፈጣሪው ጋር መገናኘቱ ናቸው።

፡ በእነዚህ ኹሉ ሊቋረጡ በማይቻል የሥጋ ግንኙነቶች አማካይነት፡ ፈጣሪ፡ ከሰብአዊ ፍጡሩ ጋር፡ በርቅቀትና በግዘፍ ሳይለየው፡ አብሮት የሚኖር ለመኾኑ በቂ ማስረጃ ነው። ይህም ሲኾን፡ በሥጋዊ ዓይኖቹ፡ ፀሓይን እንኳ፡ ለማየት፡ ዓቅም የሌለው፡ ሥጋዊው ፍጡር፡ በመንፈሳዊ ዓይኑ ካልኾነ በቀር፡ ወደፈጣሪው ደርሶ፡ እግዚአብሔርን ሊያየውና ሊያውቀው የማይቻለው መኾኑ፡ ዛሬ፡ በጠፈር መንኩራኩሮች፡ ቢበርሩት ቢበርሩት ማለቂያ በሌለው÷ ሰማያዊ ቀለም መሰሉ በሚታየው፡ "ሰማይ" ወይም፡ "ጠፈር" በሚባለው ጎዋ፡ ተረጋግጠ ይታወቃል።

እንግዲህ፡ የራስን ምንነትና ማንነት፡ እንዲህ አድርጎ ማወቅ ከተቻለ፡ ይህን ሳያደርጉ፡ እንኳንስ፡ እግዚአብሔርን የሚያህል ፍጹም ምሥጢር ቀርቶ፡ መሰል የኾነውን፡ ሌላውን ሰብአዊ ፍጡር እንኳ፡ እንዴት ማወቅ ይቻላል? አይቻልም። በዚህ መልክ፡ ሌላውን ሰብአዊ ወገንና እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚያስችለውን፡ ራስን፡ በቅድሚያ ***ማወቅ፡*** ለታላቅ የህልውና ክብር ማብቃቱ፡ ማለትም፡ በመልካም ሕይወት የመኖርን ጸጋ፡ በአስተማማኝ ዕድገት እንዲቀጥል ማድረጉ፡ በሚበቃ ተረጋግጧል።

ያን ከመሰለው አዋቂነትም እጅግ ጣፋጭ የኾነው፡ የእውቀትና የእውነት፥ የደግነትና የልማት፥ የብልጽግናና የዕረፍት፥ የሰላምና የደስታ ምንጭ ይፈልቃል፤ ፍጻሜውም፡ ራስን ብቻ ሳይኾን፡ ሌላውን ፍጡር ጭምር፡ ለመልአካዊው ማዕርግ እስከማብቃት በሚያደርስ ርኅራኄ የሚፈጸመው፡ ጊዜያዊውና ዘለዓለማዊው ሕይወት ነው።

በዚህ አንጻር፡ ሌላውን ሰው፥ ከዚያም በላይ፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚያስችለውን፡ ራስን፡ በቅድሚያ <u>*አለማወቅ*</u> ደግሞ፡ ወደታላቅ፡ የህልውና አደጋ ማድረሱ፥ ማለትም፡ በመልካም ሕይወት የመኖርን ጸጋ፡ በአሠቃቂ ጉዳት ወደማጣት ማድረሱ፡ በሚበቃ ተረጋግጧል። ያን ከመሰለው አላዋቂነትም የሚፈልቀው፡ እጅግ መራራ የኾነው፡ የድንቍርናና የሐሰት፥ የክፋትና የጥፋት፤ የችግርና የሥቃይ፥ የትካዜና የኀዘን ምንጭ ነው፤ ፍጻሜውም፡ ሌላውን ፍጡር ብቻ ሳይኾን፡ ራስን ጭምር እስከመግደል በሚያደርስ ጭካኔ የሚያከትመው፡ ጊዜያዊው የሥጋ ሞትና ዘለዓለማዊው የነፍስ ሞት ነው።

እያንዳንዱ ሰው፡ በተፈጥሮ በተሰጠው አእምሮው፡ የራሱን ምንነትና ማንነት፡ እንዲህ አድርጎ ሲያውቅ፡ "እኔ" የሚለውን፡ ራሱን፡ በፍጡርነቱ፡ ማን እንደኾነ አወቀ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ፡ እግዚአብሔርን፡ በፈጣሪነቱ፡ ማን እንደኾነ፤ ሌላውም ሰው፡ በፍጡርነቱ፡ ምን እንደኾነ በትክክል ለማወቅ፡ መንገዱ ቀና ይኾንለታል።

ጥያቄ፡- *ለዚህ እውቀት የሚያበቃው መንገድ፡ ታዲያ የትኛው ነው?*

መልስ፡- እዚህ ላይ፡ "እኔ የማውቀው፡ አላዋቂነቴን ነው!" ያለውን፡ የአንድ የጥንት ሥጋዊ ፈላስፋን ብሂል መጥቀስ፡ አግባብ ይኾናል። አዎን! ሥጋዊው ሥነ እውቀት፡ እየተራቀቁበት በኼዱ መጠን፡ እያሽቆለቆለ የሚወስደውና የሚያደርሰው፡ ወደአላዋቂነት አዘቅት ነው፤ መጨረሻውም፡ ዕብደት፥ ጥፋትና ሞት ነው። ሥጋዊው ሥነ እውቀት፡ ሌላውን የተፈጥሮ ወገንና እግዚአብሔርን ቀርቶ፡ ራስን ወደማወቅ እንኳ ሊያደርስ አይቻለውም፡ ቢችልም፡ አኹን እንደሚታየው፡ ከሥጋዊው አካል አያልፍም፤ የማሰቢያ ዓቅሙም ስለሌለው፡ ወደመንፈሳዊው ይቅርና፡ ወደነፍስ አካልና ባሕርይ እንኳ ሊዘልቅ አይችልም። <u>"በሥጋዊው ሥነ እውቀት፡ የፍጡርን መሰል ማስገኘት ተችሏል!" የሚባለው ፈሊጥ፡ በደመ ነፍስ የሚንቀሳቀሰውን ሥጋን ብቻ እንጂ፡ ነባቢት፤ ለባዊትና ሕያውት ነፍስን አይመለከትም፤</u> ይህን እውነታ፡ ኹሉም ሊገነዘበው ይገባል። ይህንም፡ ወደፊት ባለው የውይይት ኀደታችን ላይ በሚቀርበው ሓተታ ታገኙታላችሁ።

መንፈሳዊው ሥነ እውቀት፥ እርሱም፡ በእውነተኛዋ ሃይማኖትና በመንፈሳዊው አምልኮ የሚገኘው እውቀት ግን፡ ወደእግዚአብሔር ስለሚያደርስ፡ ኹሉንም ነገር፥ ኹሉንም ምሥጢር ለማሳወቅ ያስችላል፤ መጨረሻውም፡ ፍጹም ልማትና መልካም ሕይወት ነው።

"ለሥጋዊው ሰው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር፡ ሞኝነት ነውና፡ አይቀበለውም፣ በመንፈስ የሚመረመር ስለኾነ፡ ሊያውቀው አይችልም፣ መንፈሳዊው ሰው ግን፡ ኹሉን ይመረምራል፣ ራሱም፡ በማንም አይመረመርም።"[፵፫] የሚለው የመጽሐፍ ቃል፡ ይህን ያረጋግጣል። ከዚህ የተነሣ፡ ለመልካም ሕይወት፡ መርህ የኾነውን፡ ይህን፡ *"እግዚአብሔርን መፍራት፡ የእውቀት መጀመሪያ ነው!"* የሚለውን ኃይለ ቃል በማጽናት፡ "እግዚአብሔርን አውቆ፡ እርሱን ለመፍራት፡ በቅድሚያ፡ ራስን ማወቅ ብልህነት ነው!" የሚለውን የትርጓሜ ስልት ተከትሎ፡ ወደእውነተኛው ግብ መገሥገሡ ይመረጣል፤ አዎን! ራስን ከማወቁ መደብ ተነሥቶ፡ ሌላውን ሰብአዊ ፍጡር ወደማወቁ ደረጃ በመዝለቅ፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ መብቃቱ፡ የተሻለውና የቀናው መንገድ ይኾናል። ይህ ብቅዓት የሚያስገኘውም የመጨረሻ ጸጋ፡ ንጹሕ እውቀትንና ሕያውት የኾነችውን፡ እውነትን፥ እንዲሁም፡ በንስሓ የሚታደሱ፡ ደግነትንና ፍቅርን፥ ዕረፍትንና ሰላምን፥ ጤንነትንና ብልጽግናን፥ ተድላንና ደስታን ሲኾን፡ የድል አድራጊነት አክሊልን ከመቀዳጀት ጋር፡ አማናዊዉንና ዘለዓለማዊዉን መልካም ሕይወት መጐናጸፍ ነው።

ይህ እውቀት፡ የአንድነቱና የሦስትነቱ ምሥጢር፡ በተዋሕዶ የሚገለጸውን፡ የ"ኢትዮጵያዊነትን" ህልውና አጉልቶ ያስረዳል።

የኢትዮጵያዊነት አንድነትና ሦስትነት፡ በተዋሕዶ ምሥጢር።

ጥያቄ፡- *በተዋሕዶ የሚገለጸው፡ የ"ኢትዮጵያዊነት"፡ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር ያልከው ነገር፡ ምንድር ነው? ብታብራራልን?*

መልስ፡- በኢትዮጵያዊው ህልውና፡ "ምሥጢረ ሥላሴ" የሚባለው ዘይቤ፡ ስለእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት፡ ማለትም፡ "እግዚአብሔር አንድ ሲኾን፡ አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ተብሎ፡ በሦስትነት ይታወቃል፥ ይጠራል፥ ይሠራል" ብሎ የሚያትት ብቻ ሳይኾን፡ እግዚአብሔር ስለሠራቸው የሥነ ፍጥረት ምሥጢራት ጭምር የሚያብራራ የትርጓሜ ስልት መኾኑን መገንዘቡ ይጠቅማል፤ ይህን፡ የምሥጢረ ሥላሴን ነገር ለማስረዳት፡ ምሳሌ ኾነው የሚቀርቡትን፡ ራሳቸውን፡ የሥነ ፍጥረት ትንግርቶች፡ ለዚህ አባባል፡ ማስረጃ አድርጎ መጠቃቀሱ ይበቃል፡- አንዲቷን ፀሓይ፡ በክበቧ፥ በብርሃኗና በሙቀቷ ሦስትነት፥ አንዱን ሰው፡ በልቡ፥ በቃሉና በእስትንፋሱ ሦስትነት፥ አንድን ዛፍ፡ በቅርንጫፉ፥ በቅጠሉና በፍሬው ሦስትነት፥ አንድ እሳትን፡ በፍሕሙ፥ በነበልባሉና በመላፈኑ ሦስትነት፡ ተንትኖ በማቅረብ ማለት ነው።

ይህን ምሥጢር: ከዚህ በሰፋና በገዘፈ ኹኔታ: አጉልቶ ማሳየት ይቻላል:: ይኸውም: የሰው አንድነት: በነፍስ÷ በሥጋና በመንፈስ ሦስትነት፤ የቤተሰብ አንድነት: በአባት÷ በእናትና በልጅ ሦስትነት፤ የሃይማኖት አንድነት: በጸም÷ በጸሎትና በምጽዋት ምግባራት ሦስትነት፤ የኢትዮጵያዊው ዘር አንድነት: በካማዊነቱ: በሴማዊነቱና በያፌታዊነቱ ሦስትነት፤ የኢትዮጵያ መንግሥት አንድነት: በቤተ ሕዝቡ÷ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ሦስትነት፤ የቅዱሱ ኪዳን አንድነት: በኪዳነ ልቦና÷ በኪዳነ አሪትና በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ሦስትነት መገለጡ ናቸው::

የእግዚአብሔር መንግሥት: በዚህ ዓለም ገዝፋ መታየት የጀመረችው: በቀዳማውያኑ አዳምና ሔዋን ሰውነትና ህልውና ሲኾን: የእርሱ ሥርዓት በኾነው: በ፫ብቻ ቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተው ሕገ መንግሥቷም: በእየልቦናቸው ጽላት ተጽፎ የተሰጣቸው: በዚያኑ ጊዜ ነበር:: ከዚያን ወዲህ: እግዚአብሔር: 'ከወዳጆቹ ጋር በእየዘመናቱ ባደረጋቸውና እንደሰንሰለት በተያያዙት: በስድስቱ ቃል ኪዳኖች ስትጠበቅና ስትጠናከር ከቆየች በኋላ: ለፍጹምነት የበቃችው: በመጨረሻዎቹ አዳምና ሔዋን: በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም በተገኘው: በሰባተኛው የምሕረት ቃል ኪዳን ነው:: ይህች መንግሥትና ሕገ መንግሥቷ: እንዲህ: ከአዳምና ሔዋን ጊዜ ጀምሮ: በዚች ዓለም÷ በምድር ላይ: በሰው ወገኖች መካከል: ተጠብቀው÷ እውንና ሕያዋንም ኾነው የኖሩት: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ዘንድ ብቻ እንደመኾኑ ኹሉ: ዛሬም: መንግሥቷ: በእውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ሰውነት ውስጥ ተመሥርታና በሕይወታቸው ላይ ተገልጻ÷ ሕገ መንግሥቷም: በየልቦናቸው ተጽፎና በምግባራቸው ገዝፎ: እነሆ በገሃድ ሲመሰክር ይታያል::

ከዚህ የተነሣ: ኢትዮጵያ: በቅዱሱ ኪዳን: ከእግዚአብሔር የተቀበለችው÷ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቿም: ሕይወታቸውን የሚመሩበት ሕገ መንግሥት: ምን እንደኾነ: አጠቃልሎ የሚገልጸውን: "ኢትዮጵያዊነት" የሚለውን ስያሜ: "ኢትዮጵያ" ከሚለው ስም ጋር: ለዚህ ውይይታችን: ዓቢይ አርእስት አድርጌ ሰጥቻለሁ::

ዓቢይ አርእስቱም: በውስጡ: ይኸው "ኢትዮጵያዊነት": ምን እንደኾነ የሚያንጸባርቀውን: **"የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊው አንድነት: በሦስትነት የተገለጸበት የተዋሕዶ ምሥጢር!"** የሚለውን ንዑስ አርእስት: እንዲያካትት አድርጌአለሁ:: ይህንም ያደረግሁት: አንድ የኾነውን ኢትዮጵያዊ ህልውና: በተዋሕዶ ምሥጢር ያስገኙትን: "'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?"÷ "'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር ማነው?"÷ "'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?" የሚሉትን: ሦስት እውነታዎች: ከሦስት አግጫዎች እያሳየሁ በማቅረብ ነው:: ስለዚህ: የዚህ ውይይት: የመጀመሪያው ክፍል: ቀደም ብዬ እንደገለጽሁላችሁ: "'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?" የሚለው ሲኾን: ኹለተኛው ክፍል ደግሞ: "'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር ማነው?" የሚለው ነው፤ ሦስተኛውም ክፍል: "'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?" የሚለው ነው::

መወለድ፥ መኖርና መሞት፡ የፍጥረት ወገን በሽነው ላይ ኹሉ፡ በእውን የሚፈጸሙ የማይቀሩ ትንግርቶች መኾናቸውን፡ በተለይ፡ ሰው የሚባለው እያንዳንዱ ፍጡር፡ በነፍስ ወከፍ፡ ደህና አድርጎ ያውቃል። ስለዚህ፡ እነዚህን ትንግርቶች፡ በምር እንጂ በዋዛ ሊያያቸው አይገባም! በፍጡር ላይ፡ ለአንድ ጊዜ ብቻ፡ በልደት ተጀምረው፡ ወይ በሞት የሚያበቁ፥ ወይ በሕይወት የሚዘልቁ ኹነታዎች ናቸው። በልደት ከተጀመሩት፡ ከእነዚህ፡ ኹለት ፍጻሜዎች፡ አንደኛውን ለመምረጥ፡ ለሰብአዊው ፍጡር ኹሉ፡ በተፈጥሮ፡ በእየግሉ፡ ሙሉ ነጻነትና ሥልጣን ተሰጥቶታል። ስለዚህ፡ ማናቸውም ግለሰብ፡ ከኹለት፡ አንዱን ለመምረጥ፡ ለአንዲት ቅጽበት እንኳ ቢኾን፡ "ቆይ!" በሚለው የማዘናጊያ ጠንቅ፡ ሊሰለብ አይገባም፤ ያ ግለሰብ፡ አኹኑኑ፥ በዚች አፍታ፡ ቁርጥ ውሳኔን መስጠት አለበት! የሞት ወይም የሕይወት ጉዳይ ስለኾነ።

ይህን የአሳብ ድምጻሜ፡ መነሻ አድርገን፡ እናንተና እኔ፥ ደግሞም፡ እኛን የመሰሉ፡ ወንዶችና ሴቶች፡ እያንዳንዳችን፡ "'እኔ' የምለው እኔነቴ ማነው?" የሚለውን፡ የነፍስ ጫማ ተጫምተንና "'ባልንጀራዬ' የምለው ፍጡር ማነው?" የሚለውን፡ የሥጋ ልብስ አጥልቀን፥ "'ፈጣሪዬ' የምለው እግዚአብሔር ማነው?" የሚለውንም የመንፈስ ድርብ ተጉናጽፈን፡ በሃይማኖትና ምግባር ፈረስ በሚሳበው፥ በመንፈስ ቅዱስም በሚነዳው የውይይት ሠረገላ ላይ እንቀመጣለን፤ ከዚያ፡ ኢትዮጵያዊዉን፡ የህልውናና የሕይወት ምሥጢር፡ በተፈጥሮአዊውና በመለኮታዊው ፋና፡ ፈልጎ ለማግኘት በሚያስችለን፡ የጥያቄና መልስ ትጥቃችን፡ እንዘጋጃለን፤ በመጪረሻ፡ ረዥሙን የአርበኝነት መንገዳችንን፡ በእውነተኛ ጀግንነት አከናውነን፡ በእግዚአብሔር ግንብ ከተመሸገችው፡ ዘለዓለማዊት ኢትዮጵያችን ለመድረስ፡ የእውቀት ጉዟችንን እንጀምራለን።

እንዲህ ኾነን፡ እናንተና እኔ፥ እኛን የመሰሉትም ኹሉ፡ መንገዳችንን ለመጀመርና ጉዟችንን አከናውነን፡ ካሰብነው ግብ ለመድረስ፡ እያንዳንዳችን፡ ማንን ኾነን መገኘት ያለብን ይመስላችኋል? በእርግጥ፡ ትጥቁን አሟልቶ፥ በውሳኔው፡ ቆራጥ ኾኖና ለሰልፍ ተደራጅቶ፡ ወደሰልፉና ወደጦሩ አውድማ እንደሚገሠግሠው ታማኝ አርበኛ ነዋ!

ታዲያ፥ እናንተንስ ይኹን፡ በፊት ለፊቴ እያነጋገርኋችሁ ስለኾንሁ፡ ይኸው፡ በእውን አያችኋለሁ፤ ሌሎቻችሁን ግን፡ እንዲህ የተዘጋጃችሁ ኾናችሁ መገኘታችሁን፡ እኔ፡ እንዴት ላውቅ እችላለሁ? አልችልም። የምታውቁ፡ እየራሳችሁ፡ በእየኅሊናችሁ፥ ከዚያም፡ ኹሉን የሚያውቅ፡ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ብቻ እንጂ፡ እኔ፡ ላውቅ አልችልም። ይህን በመሰለ፡ መሰናዶና ዝግጅት፡ የተደራጀን ካልኾን በቀር ደግሞ፡ ጉዞውን ከወዲሁ፡ ባንጀምረው ይሻላል፤ ላንጨርሰውና ከግቡ ላንደርስበት፡ መኻላታችን፡ ምንም ዓይነት ዓላማና ጥቅም የለውምና!

እንግዲህ፡ የዚህን ውሳኔ፡ ለእያንዳንዳችሁ ትቼ፡ ውሳኔያችሁ፡ ላምንታዊ እንደኾነ በማመን፡ የእናንተና የእኔ ድርሻ የኾነውን፡ ይህን፡ የጀመርነውን ውይይታችንን፡ እንዲህ እያልን እንቀጥላለን።

\+ + +